

**የብሉይ ኪዳን ታቦት (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ከኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር 1992 ዓ.ም ገጽ 129)**



# ክፍል 7 - መካከለኛ

## 7.1 የብሉይ ኪዳን መካከለኞች

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርና ሕዝቡ ይገናኙ የነበሩት፥ እግዚአብሔር መርጦ በእርሱና በሕዝቡ መካከል ባቆማቸው መካከለኞች አማካይነት ነበር፡፡ በዚህ ክፍል የምናተኩረው የሕዝቡ ነጻ አውጪ በሆነው መካከለኛ ላይ ይሁን እንጂ፥ መካከለኞች የነበሩት ነቢያት፥ ካህናትና ነገሥታት መሆናቸው ይታወቃል፡፡ በተለይም ደግሞ የካህናት መካከለኛነት ጕልህ ስፍራ የሚሰጠውና የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክህነት በምሳሌነት ወይም በንጽጽር የሚያስረዳ ነው፤ ይህንንም በክፍል 10 የምንመለከተው ይሆናል፡፡

እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ የገባውን ቃል ኪዳን ዐስቦ፥ ሕዝቡን ለ400 ዓመታት ያህል ባሪያዎች አድርገው ካስጨነቋቸው ከግብጻውያን እጅ ነጻ የሚያወጣበት ጊዜ ሲደርስ፥ ለሙሴ ተገልጦ ካነጋገረው በኋላ፥ ወደ ግብጽ ልኮ በእርሱ አማካይነት ሕዝቡን ነጻ አወጣ፤ (ዘፀ. 3፥1-10፤ ሆሴ. 12፥14)፡፡

እግዚአብሔር በእርሱና ነጻ ባወጣው ሕዝብ መካከል ሙሴን በነቢይነቱና በነጻ አውጪነቱ መካከለኛ አድርጎ ሲያቆመው፥ ለሕዝበ እስራኤል ሊያስተላልፍ የፈለገውን ትእዛዝና መመሪያ ሁሉ በእርሱ በኩል ለማስተላለፍ፥ ሕዝቡንም ከእርሱ ጋር እንዲያገናኝና የሕዝቡን ችግርና ጥያቄ ለእግዚአብሔር እንዲያቀርብ፥ ስለ ሕዝቡም እንዲጸልይና እንዲማልድ በመሆኑ፥ እነዚህን ተግባራት ሙሴ በሕይወተ ሥጋ ሳለ አከናውኗቸዋል፤ (ዘፀ. 25፥22፤ 19፥7-8፤ 19፤ ዘዳ. 5፥5፤ ዘኍ. 11፥1-35፤ 21፥7፤ ዘፀ. 32፥11-14፤ ዘኍ. 14፥13-19)፡፡

በሲና ተራራ ላይ ሕጉን ለሙሴ ሊሰጠው እግዚአብሔር በእሳት በወረደ ጊዜ፥ የሲና ተራራ በሙሉ ይጤስና ይናወጥ ነበር፤ ከዚህ ቀደም ብሎም ማለዳ ላይ ነጐድጓድና መብረቅ፥ ከባድም ደመና፥ እጅግም የበረታ የቀንደ መለከት ድምፅ በተራራው ላይ በሆነ ጊዜ፥ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ከመፍራታቸው የተነሣ ሙሴን «አንተ ተናገረን እኛም እንሰማለን፤ እንዳንሞት ግን እግዚአብሔር አይናገረን፡፡» በማለታቸው የሙሴን መካከለኛነት ተቀብለዋል፡፡ እግዚአብሔርም ይህ ልብ ሁልጊዜ ለእነርሱ እንዲሆንላቸው መሻቱን ገለጸ፤ (ዘፀ. 19፥16-18፤ 20፥19፤ ዘዳ. 5፥27)፡፡

ከዚህ ጊዜ አስቀድሞም እግዚአብሔር በሙሴ እጅ ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ ስላሻገራቸውና ጠላቶቻቸውን ግብጻውያንን በባሕሩ ስላሰጠመ፥ እግዚአብሔርን እጅግ ፈርተው ሲያምኑበት፥ በባሪያው በሙሴም (በመካከለኛነቱ) አምነዋል፤ (ዘፀ. 14፥31)፡፡

እግዚአብሔር በሙሴ መካከለኛነት ሕግን ሰጥቷል፤ (ዘዳ. 5፥6-21፤ ዮሐ. 1፥17)፡፡ የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን የጻፉት ቅዱሳን ደግሞ

እግዚአብሔር ሕግን በመላእክት ሥርዐት (አጋፋሪነት) ለሙሴ እንደሰጠው ጽፈዋል፤ (የሐዋ. ሥራ 7÷53፤ ገላ. 3÷19)።

የሙሴ መካከለኛነት ጊዜያዊና ወደፊት ለሚመጣው የዐዲስ ኪዳን መካከለኛ ለክርስቶስ ጥላና ምሳሌ ነበር። ሙሴ ከእርሱ ለሚበልጠው ለክርስቶስ ምሳሌ ከሆነባቸው ነገሮች ውስጥ ነቢይ መሆኑ (ዘዳ. 18÷15-19፤ ሆሴ. 12÷14)÷ ታማኝነቱና (ዕብ. 3÷1-6)÷ ወገኖቹን ነጻ ለማውጣት በማሰቡ ምክንያት ከወገኖቹ በኩል የደረሰበት ተቃውሞ (የሐዋ. ሥራ 7÷35-40፤ 52-53) የሚሉት ይገኙበታል።

ሙሴም ቢሆን የእርሱ መካከለኛነት ጊዜያዊ እንጂ ዘላቂነት ያለው እንዳልሆነ ስለተረዳ÷ እግዚአብሔር እንደተናገረው ለእስራኤል ሕዝብ ፡ - «አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል÷ ከወንድሞችህ እንደኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፤ እርሱንም ታዳምጣለህ።» (ዘዳ. 18÷16) በማለት ምስክርነቱን ሰጠ። ይህም ትንቢት የተነገረው ለጊዜው ለኢያሱ ቢሆንም÷ ፍጻሜው ግን ለክርስቶስ ነበር፤ (የሐዋ. ሥራ 3÷22-23)። ሙሴ ይህን ብቻ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ ብዙ ጽፏል (ዘፍ. 3÷15፤ 49÷10፤ ዮሐ. 5÷46)።

በመሆኑም ሙሴ ሲሞት የመካከለኛነቱን ሥራ ለሌላውና በሕይወተ ሥጋ ለነበረው ለነዌ ልጅ ለኢያሱ ለቀቀ (ዘዳ. 31÷1-8፤ 34÷9)። እግዚአብሔርም ቀድሞ ከሙሴ ጋር እንደነበረ÷ አሁን ደግሞ ከሌላው መካከለኛ ከኢያሱ ጋር እንደሚሆን ተናገረ፤ (ኢያ. 1÷5)። ሕዝበ እስራኤልም ለቀድሞው መካከለኛ ለሙሴ እንደታዘዙ ሁሉ÷ አሁንም ዐዲስ ለተሾመው መካከለኛ ለኢያሱ የሚታዘዙ መሆናቸውን ገለጹ፤ (ኢያ. 1÷16-18)። የኢያሱ የመካከለኛነቱ አገልግሎት ያተኮረውም ለሕዝቡ ዕረፍተ ከነዓንን በማውረስ ላይ ነበር፤ (ዕብ. 4÷8)።

ከሙሴና ከኢያሱም ሌላ በሊቀ ካህንነቱ በሕዝቡና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው መካከለኛም አሮን ሲሆን÷ መሥዋዕት በመሠዋትና ስለ ሕዝቡ በማስተስረይ የመካከለኛነቱን ተግባር አከናውኗል።

እስካሁን በዋናነት የተመለከትናቸው መካከለኞች ሙሴ÷ አሮንና ኢያሱ ለክርስቶስ መካከለኛነት ጥላና ምሳሌ በመሆናቸው በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ከክርስቶስ ጋር በንጽጽር ቀርበዋል። ስለ ሙሴ (3÷1-6)÷ ስለ ኢያሱ (4÷1-16)÷ ስለ አሮን (7÷1-28) መመልከት ይቻላል።

እንግዲህ እነዚህ የብሉይ ኪዳን መካከለኞች ሁሉም ሰዎች ብቻ ስለሆኑ የአገልግሎት ዘመናቸው በሞት የተገደበ ነበር። በዚህም ምክንያት ከእነርሱ ጀምሮ አንዱ ሲሞት ሌላው እየተተካ÷ የዐዲስ ኪዳን ብቸኛው መካከለኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ ብዙ መካከለኞች ዐልፈዋል።



## 7.2 የዐዲስ ኪዳን መካከለኛ

ሰው በኀጢአት ከወደቀና ባሕርዩም በኀጢአት እድፍ ከተበላሸ በኋላ÷ ቅዱስ ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የማይሆንለት በመሆኑ÷ ከእግዚአብሔር ፊት መሸሽና መደበቅን እንደ ዋና አማራጭ ለመውሰድ ተገዷል፤ (ዘፍ. 3÷8)። በኋላም ወደ እግዚአብሔር በራሱ ብቻ ሊቀርብ ፈጽሞ የማይችል ሆኗል።

ባለፈው ክፍል እንዳየነው ሕዝበ እስራኤል በሲና ተራራ የእግዚአብሔርን ክብር መውረድና÷ በመውረዱም የተሰማውና የታየው አስፈሪና አስደንጋጭ ክሥተት÷ ከእነርሱ ኀጢአተኝነት አንጻር ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ የሚያበረታታ አልነበረም። ስለዚህ ሌላ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርባቸው በእግዚአብሔርና በእነርሱ መካከል ጣልቃ የሚገባ መካከለኛ ስላስፈለጋቸው÷ ሙሴ ከእርሱ የሰማውን እንዲናገራቸው ጠየቁት፤ (ዘፀ. 20÷19)።

ሙሴ በመዋዕለ ዘመኑ ለክርስቶስ ጥላና ምሳሌ ሆኖ የመካከለኛነትን ሥራ ቢሠራም÷ ብዙ ጉድለቶች የነበሩበት መካከለኛ ነው። ከሁሉም በላይ ሙሴ ሰው ብቻ መሆኑ የተሟላ መካከለኛ ሊሆን አልቻለም። ይኸውም የሰውን ብቻ እንጂ የእግዚአብሔርን ውክልና አልያዘምና ነው።

ሙሴ ምንም እንኳን ስለ ታማኝነቱና ትሑትነቱ ቢመሰከርለት (ዘኍ. 12÷3፤7)÷ ሰው ነውና ከኀጢአት ንጹሕ ነበር ለማለት አይቻልም። እንዲያውም ይህ ጉድለት ስለተገኘበት ሕዝቡን ወደ ተስፋይቱ ምድር ሳያገባ÷ ራሱም ሳይገባ በእግዚአብሔር ምሕረት በዐይኑ ብቻ በርቀት ተመልክቷት ወደ አባቶቹ ተከማቸ፤ (ዘኍ. 20÷12፤ ዘዳ. 32÷48-52፤ 34÷1-5)።

ከሙሴ በኋላ የተነሡትም ቢሆኑ ከሙሴ ያነሰ ቢሆን እንጂ የተሻለ ነገር አልነበራቸውም፤ (ዘዳ. 34÷10)። የነዚህ ሁሉ መካከለኛነት ጥላና ምሳሌ በመሆኑ÷ ቋሚነት ያለው ዘላለማዊ አልነበረም። በሌላ አነጋገር ተስፋው የተገባለት ዘር÷ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዐዲስ ኪዳን መካከለኛ ሆኖ እስኪመጣ ድረስ ሌሎቹ መካከለኛ ሆኑ ማለት ነው፤ (ገላ. 3÷19) ።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መካከለኛነት ለዐዲስ ኪዳን አገልግሎት አስቀድሞ የታለመና ፍጹምነትን የተላበሰ÷ ሌላ ተተኪ የማያስፈልገው ነው። እርሱ የጥላው አካል እንደመሆኑ መጠን÷ በሙሴና ከእርሱ በኋላ በተነሡት መካከለኞች የነበረውን ጉድለት÷ በሁሉም አቅጣጫ አሟልቶ ተገኝቷልና÷ ከቀድሞው ዘመን በተሻለ ሁኔታ በፍርሀትና በድንጋጤ ሳይሆን÷ እንደ ልጆች በፍጹም ደስታ ወደ አብ የምንቀርብበትንና የምንገባበትን÷ በዚያም ለዘላለም የምንኖርበትን ድፍረት ሰጥቶናል፤ (ኤፌ. 2÷18፤ 3÷12፤ ዕብ. 10÷19፤ 12÷18-24)።

ጌታ እንደ ሙሴ ነጻ ያወጣውን ሕዝብ ወደ ርስቱ ሳያገባ የቀረ መካከለኛ አይደለም:: ከአባቱ የተሰጠውን ሥራ ሁሉ ፈጽሞ አብን ያከበረ (ዮሐ. 17÷4)፥ ለሕዝቡ መኖሪያ ያዘጋጅ ዘንድ ወደ አባቱ የሄደ፥ ዳግም ተመልሶ በመምጣትም እርሱ ባለበት ሕዝቡን የሚያኖር ፍጹም መካከለኛ ነው፤ (ዮሐ. 14÷2-3)::

በሙሴ መካከለኛነት ተሰጥቶ የነበረው ሕግ ከሥጋ ዳካማነት የተነሣ ሊፈጽመው የሚችል ባለመገኘቱ፥ ኀጢአትን እያጎላ በሰው ላይ ፍርድንና እርግማንን ከማምጣት በቀር ድኅነትን አላሰጠም፤ (ሮሜ 7÷7፤ 3÷20፤ ገላ. 3÷10፤ ዕብ. 7÷18)::

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መካከለኛነት የተሰጠው ጸጋና የሕይወት መንፈስ ሕግ ግን፥ ከኀጢአትና ከሞት ሕግ፥ እንዲሁም ከሙሴ ሕግ ሕዝቡን ነጻ በማውጣት፥ ከኀጢአት ርቀው ጽድቅን የሚፈጽሙበትን ኀይልና ጉልበት የሚያጐናጽፍ ሆኗል፤ (ዮሐ. 1÷16-17፤ ሮሜ 8÷1-4፤ ገላ. 3÷23-25፤ ሮሜ 6÷14፤ ቲቶ 2÷11-13)::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው:: በፍጹም ሰውነቱም ከኀጢአት የተለየ ንጹሐ ባሕርይ ነው:: መካከለኛነቱም በሞት የማይገደብበት ሕያው ስለሆነ፥ የመካከለኛነትን መስፈርት ሙሉ በሙሉ አሟልቶ ተገኝቷልና፥ በዐዲስ ኪዳን ዘመን «በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው::» ተባለለት፤ (1ጢሞ. 2÷5)::

በዘላለማዊ መካከለኛነቱም በእርሱ በኩል አምነው የሚመጡትን ለማዳን በአብ ቀኝ አለ፤ (ዕብ. 5÷9-10፤ 7÷25):: ያለ እርሱ መካከለኛነትም ወደ አብ መድረስም ሆነ መግባት የማይቻል መሆኑን ራሱ ጌታ በማይታበል ቃሉ ያረጋገጠው እውነት ነው፤ (ዮሐ. 14÷6፤ 10÷9)::

ክርስቶስ በመካከለኛነቱ በሕይወታቸው ሁሉ ስለ ሞት ፍርሀት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ከዲያብሎስ ሥልጣን ነጻ አውጥቷል፤ (ዕብ. 2÷14-15):: ይህንንም ነፍሱን አሳልፎ በመስጠቱና በመሞቱ ያደረገው ነው፤ (ዮሐ. 10÷15፤ 3÷15):: በምድር ላይ ሳለ ከአብ የተሰጡትን ሁሉ ጠብቃቸው፤ ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓቱ ሲደርስም ከአብ የተሰጡትን ሁሉ መልሶ ለአብ በመስጠት ይጠብቃቸው ዘንድ ወደ አብ ጸሎትንና ምልጃን አቀረበላቸው፤ (ዮሐ. 6÷37፤44፤ ይሁ. 1፤ ዮሐ. 17÷6-12)::

በሊቀ ካህንነቱ ያቀረበው ምልጃና ጸሎት ለቀደሙት ደቀ መዛሙርቱ ብቻ ሳይሆን፥ ከእነርሱ በኋላ ትምህርታቸውን ሰምተው በመቀበል በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚያገለግል ነው፤ (ዮሐ. 17÷20-21)::

ስለሆነም ክርስቶስ አስቀድሞ አንድ ጊዜ ባቀረበው ሥሙር (የተወደደ) መሥዋዕትና ምልጃ በአባቱ ፊት ዛሬም መካከለኛችንና አስታራቂያችን ነው::



ይህን እውነት ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ በትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍቻው እንዲህ ሲሉ በግልጽ አስቀምጠውታል: -

> «በአንድ በእግዚአብሔር አብ እንደምናምን ሁሉ፥ በአንድ ጌታ፥ በአንዱ አዳኝ፥ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን፤ አዳኛችን እርሱ አንድ ጌታ ነውና፤ ሁላችን የዳነው በዚህ የአብ አንድያ የባሕርይ ልጅ በሆነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት ነው:: <u>አሁንም ወደ አብ የምንቀርበው አስታራቂያችን በሆነው በዚሁ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ነው:: እርሱ እውነተኛ መንገድ ነውና፤</u> (ዮሐ. 14÷6) ::» (ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ ገጽ32)::

## 7.3 በሰዎች የቆሙ መካከለኞች

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በዐዲስ ኪዳን በእግዚአብሔር ዕቅድና ዐሳብ መሠረት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የቆሙትን መካከለኞች እስካሁን ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ ከዚህ ውጪ ሰዎች በገዛ ፈቃዳቸው ያቆሟቸውን መካከለኞች ሁኔታ እናያለን፡፡

በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ለሕዝቡ የእርሱን ፍርድና ሥርዐት በሚያስተላልፉ፥ መጪውንም በሚገልጡ ነቢያት፥ ስለ ሕዝቡ መሥዋዕትን በመሠዋት በሚጸልዩና በሚያስታርቁ ካህናት፥ እንዲሁም ሕዝቡን ከማናቸውም ክፉ ነገር በሚጠብቁ፥ በሚመሩና በሚያስተዳድሩ ነገሥታት መካከለኛነት ከሕዝቡ ጋር ይገናኝ እንደነበረ ይታወቃል፡፡ ይህም ግንኙነት ቀጣይነት የነበረው መካከለኛው ነቢይ፥ ካህን ወይም ንጉሥ በሕይወተ ሥጋ እስካለ ድረስ ብቻ ነው፡፡ በሞት ሲለይ ግን የመካከለኛነቱ አገልግሎት ስለሚቋረጥ በምትኩ ሌላ በሕይወተ ሥጋ ያለ መካከለኛ ይሾም ዘንድ የግድ ነበር፡፡

አንዱ ሲያልፍ ሌላው የመተካቱ ጉዳይ የመካከለኞቹን ቍጥር አበራክቶታል፤ ከሞት በኋላ የመካከለኛነት ሥራ መቀጠል የሚችል ቢሆን ኖሮ ግን ሌላ በሕይወተ ሥጋ ያለ ምትክ መካከለኛ መሾም ባላስፈለገ ነበር፡፡

የብሉይ ኪዳን ካህናት የመካከለኛነት አገልግሎት እስከ መቼ ድረስ እንደነበር ሐዋርያው በዕብራውያን መልእክቱ እንዲህ ሲል አስረድቷል: - «እነርሱ እንዳይኖሩ ሞት ስለከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው፡፡» (ዕብ. 7÷23) ከዚህ የምንረዳው የነበሩት መካከለኞች ሁሉ፥ ሰዎች ብቻ በመሆናቸው መካከለኛነታቸው ዘላለማዊ እንዳይሆን በሞት መገደቡን ነው፡፡

አሮን በሕይወተ ሥጋ ሳለ በሊቀ ካህንነቱ መካከለኛ ነበር፡፡ ሲሞት ግን በመካከለኛነቱ ሊቀጥል የማይችል በመሆኑ በምትኩ ልጁ አልዓዛር ሊቀ ካህን ሆኖ እንዲሾም እግዚአብሔር አዘዘ፡፡ በአሿሿሙ ሥርዐት ላይ አሮን ቀድሞ በክህነት ሲያገለግል ይለብሰው የነበረውን የተለየ የክህነት ልብስ እንዲያወጣና ልጁ አልዓዛር እንዲለብሰው፥ አሮን ግን ወደ ሞቱት ወገኖቹ እንዲከማች እግዚአብሔር ሲናገርና፥ ነገሩም ሲፈጸም፥ የአሮን ክህነት በሞቱ ጊዜ መሻሩንና በአልዓዛር መተካቱን እንረዳለን፤ (ዘኍ. 20÷24-29)፡፡ የሙሴ በኢያሱ መተካትም እንደዚሁ ነው፡፡

ሕዝበ እስራኤል በታሪካቸው ይህን የእግዚአብሔር አሠራር ተቃውመው የተገኙበት ጊዜ ፈጽሞ የለም፡፡ ምንም እንኳ ለመጀመሪያዎቹ መካከለኞቻቸው ከፍተኛ ግምት ቢኖራቸውም ቅሉ፥ እነርሱ ሲያልፉ ከእነርሱ ውጪ ሌላ መካከለኛ አንቀበልም በማለት አላመፁም፡፡ ይልቁንም ዐዲስ የተሾሙትን ተቀብለው ላለፉት መካከለኞቻቸው ይታዘዙ እንደነበረው ሁሉ፥ አሁን ደግሞ ለነኚህ እንደሚታዘዙ ቃል ሲገቡ እንመለከታለን፡፡ ለምሳሌ: - ታላቁ የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ አንቀላፍቶ ኢያሱ ሲተካ፥ ሕዝበ እስራኤል ሹመቱን ተቃውመው «ዛሬ ቢሞትም፥ ለሁልጊዜ መካከለኛ ችን ሙሴ ብቻ ነው፡፡» በማለት ያንቀላፋውን ሙሴን ለመፈለግ ወይም ወደ እርሱ ጸሎትና ምልጃ ለማቅረብ አልተነሡም፤ (ኢያ. 1÷16-18)፡፡



ሙሴም በሕይወተ ሥጋ ሳለ «... አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል፥ ከወንድሞችህ፥ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፤ እርሱንም ታዳምጣለህ፡፡» (ዘዳ. 18÷16) አለ እንጂ፥ «በሞትም መካከለኛነቴ ይቀጥላልና፥ ወደ እግዚአብሔር የምትቀርቡት በኔ በኩል ስለሆነ፥ ከሞትኩም በኋላ ቢሆን ወደ እኔ ጸልዩ፤ ምልጃም አቅርቡ፡፡» ሲል አላዘዛቸውም፡፡

ይህን ያላስተዋሉ ወገኖቻችን ግን፥ ሌላውን ለማዳን ይቅርና፥ ራሳቸውንም እንኳ ቢሆን ከእግዚአብሔር በቀር በራሳቸው ሊያድኑ ፈጽሞ ያልቻሉትን አዳምና ሔዋንን ጨምሮ፥ አሁን በዐጸደ ነፍስ የሚገኙትን የብሉይ ኪዳንና የዐዲስ ኪዳን ቅዱሳን ነፍሳትን መካከለኛቸው አድርገው በመሾም፥ ሰአሉ ለነ (ለምኑልን አማልዱን) በማለት፥ ወደ እነርሱ ምልጃና ተማጽኖ እያቀረቡና ሌላውም እንዲያቀርብ እያስተማሩ ይገኛሉ፡፡

መቼም ቢሆን ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ዐሳብ አገልግለው በክብር ላለፉ ቅዱሳን ሁሉ  ልዩ ግምት አላቸው፡፡ ሠርተው ባለፉት መልካምና በጎ ሥራ ሁሉ ምሳሌነታቸውን ይከተላሉ፡፡ እነርሱ መንፈሳዊውን ሩጫ በድል አድራጊነት የፈጸሙ በመሆናቸውም፥ ዛሬ በመጋደል ላይ ለሚገኙ ክርስቲያኖች እንደ ደመና በዙሪያቸው ያሉ ምስክሮች ናቸው፤ (ዕብ. 12÷1)፡፡ በምድር ላይ መልካሙን የእምነት ገድል እየተጋደሉ ለሚገኙት ክርስቲያኖች፥ የእነርሱ መልካሙ ሥራና ተጋድሎ በእምነት እያበራ፥ «እነርሱ ከደረሱበት እናንተም ለመድረስ በርቱ ጽኑ!» በሚል ዐይነት የሚያበረታታቸው መሆኑን በእምነት ስለሚገነዘቡ ያከብሯቸዋል፡፡ ከእነርሱ ጋር በዐይን የማይታይ፥ ነገር ግን በእምነት የሆነ መንፈሳዊ ኅብረት እንዳላቸውና ወደዚህ ኅብረት እንደደረሱም ይረዳሉ፤ (ዕብ. 12÷22-24)፡፡

ታዲያ በዚህ መልኩ በእኛና ባንቀላፉት ቅዱሳን መካከል በእምነት የሆነ መንፈሳዊ ኅብረት ቢኖርም፥ እግዚአብሔር እኛን ወደ እነርሱ ጸልዩና ወደ እኔ ትቀርባላችሁ ሲል አላዘዘንም፡፡ አዝዞንስ ቢሆን ኖሮ አንዱ የእግዚአብሔር ሰው፥ ከእርሱ አስቀድሞ ወዳንቀላፉት ቅዱሳን ሲጸልይና ምልጃን ሲጠይቃቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቢያንስ በአንድ ስፍራ ላይ እናነብ ነበር፡፡

እግዚአብሔር ÷ ጻድቃንም ይሁኑ ኀጢአተኞች፥ ከሞቱት ሰዎች መናፍስት ጋር ለመገናኘት በማሰብ፥ የምናደርገውን ጸሎትና ድግምት ሲከለክልና፥ ይህም አድራጎት በእርሱ ዘንድ የተጠላ መሆኑን ሲናገር ከቃሉ እናነባለን፤ (ዘዳ. 18÷10-11)፡፡

የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ሰዎች በሕይወተ ሥጋ ሳሉ፥ እንዲጸልዩለት ከሚፈልገውና እንደ እነርሱ በሕይወተ ሥጋ ካለው ሰው ጋር በአካል ተገናኝተው፥ አሊያም ስለ እርሱ ከየትኛውም አቅጣጫ ተነግሯቸው ይጸልዩ፥ ይማልዱ ነበር፡፡ ዛሬም በዐዲስ ኪዳን ዘመን በሕይወተ ሥጋ ያሉ ቅዱሳን ስለ ሌላው ይጸልያሉ፥ ይማልዳሉ፡፡

የእግዚአብሔር ቃል «ትፈወሱ ዘንድ እያንዳንዱ ስለሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኀይል ታደርጋለች።» (ያዕ. 5÷16)÷ በማለት የሚናገረው በሕይወተ ሥጋ ያሉት ቅዱሳን÷ ለሌሎች በሕይወተ ሥጋ ላሉት መጸለይ እንደሚገባቸው የሚያስረዳ ነው። መልእክቱ የተጻፈው ቀድሞም ቢሆን በዐጸደ ነፍስ ስላሉት ቅዱሳን ሳይሆን÷ በሕይወተ ሥጋ ላሉና በወቅቱ በክርስቶስ ምክንያት ተበትነው ለነበሩ ዐሥራ ሁለቱ ወገኖች ነው። ቃሉ ሕያው በመሆኑ በዘመናት ሁሉ የሚያገለግለው በሕይወተ ሥጋ ላሉት ብቻ ነው።

ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን የሚሰጠውን የቅዱሳን አማላጅነት ትምህርት የተመለከትን እንደሆነ ግን ከዚህ እውነት ጋር ይቃረናል። ለትምህርቱም የሚቀርበው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ በአብዛኛው ቅዱሳን በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ያቀረቡትን ምልጃና ጸሎት የሚመለከት ነው። ቢሆንም ይህ በዐጸደ ነፍስም ሊያማልዱ እንደሚችሉ አይጠቁምም። በዐጸደ ነፍስ ይማልዳሉ ለማለት የሚጠቀሱ አንዳንድ ማስረጃዎች ያሉ ቢመስሉም÷ ያለ ንባባቸው ተተርጉመው÷ የሰዎችን ዐሳብ እንዲደግፉ ሲባል የቃላት ጨዋታ ተካሂዶባቸው÷ ወይም ደግሞ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ እንዲህ ካደረጉ ከሞቱ በኋላማ ከዚህ የበለጠ እንዴት እያደርጉ? በሚል ግምታዊ ስሌት መሠረት ነው።

አንዳንዶች እንዲያውም ይባስ ብለው የእውነት ሽታ ባልዞረበት በልብ ወለድ ድርሰታቸው ውስጥ÷ የቅዱሳንን ነፍሳት ሥጋ አልብሰውና ለአማላጅነት በእግዚአብሔር ፊት አቁመው በዐጸደ ነፍስ የቅዱሳን አማላጅነት እንዲህ ነው ሊሉን ይከጅላሉ። በዚህም የቅዱሳን ሥጋ እስከ ትንሣኤ ዘጉባኤ ድረስ በመቃብር መኖሩን የዘነጉ ይመስላሉ። ሁሉም ግን ተረት ተረት ነው።

የቅዱሳንን የዐጸደ ነፍስ ምልጃ አስመልክቶም ነገሩ ውሸት መሆኑን የተረዱት ወገኖች÷ ከሌሎች ጽንፎች ሊነሣባቸው የሚችለውን ተቃውሞ በመፍራት ይመስላል÷ በማቻቻል ዐይነት መንገድ የሚሰጡት ትርጉም አለ። ለምሳሌ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት በተሰኘው የቤተ ክርስቲያኒቱ መጽሐፍ የተገለጸውን ቀጥሎ እንመልከት: -

> «ቅዱሳን ጻድቃን ያማልዳሉ ስለተባለ ግን ... በሕይወት ሥጋ ሳሉ እግዚአብሔርን አገልግለው የተቀበሉት ቃል ኪዳናቸው እስከ ዕለተ ምጽአት ሲያማልድ ይኖራል ማለት ነው እንጂ÷ እንደ ገና በአካለ ነፍስ መውጣት÷ መውረድ÷ መስገድ÷ መጸለይ÷ መለመን አለባቸው ማለት አይደለም። ... ሊቃውንትም «ሰአሊ ለነ ቅድስት» ያለውን ንባብ ሲተረጉሙ: - በቀደመ ልመናዋ የምታስምር ስለሆነ ነው ይላሉ። ቃል ኪዳን ማለትም «መሐልኩ በርእስየ፤ ሕያው አነ» ያለው ቃሉ÷ ሕያው ሆኖ ከእነርሱ በኋላ ለሚነሡት ትውልዶች የሚያደርገው ይቅርታና ቸርነት በመሐላው እንደጸናላቸው ይኖራል ማለት ነው እንጂ÷ ከሞቱ በኋላ ሲያማልዱ ይኖራሉ ማለት አይደለም።» (ገጽ 125-126)።



በቀደመው ልመናቸው ነው የሚያስምሩት÷ የሚለው አስተምህሮ÷ በቀጥታ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ባቀረበው መሥዋዕትና ምልጃ ዘወትር ያስምራል ከሚለው የተቀዳ (የተኮረጀ) ይመስላል።

በዚህም ተባለ በዚያ የዐዲስ ኪዳን መመካከለኛ አንድ ብቻ÷ እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ በመሲሕነቱ ነቢይነትን÷ ሊቀ ካህንነትንና ንጉሥነትን ገንዘቡ አድርጓል። በሰውነቱ ቢሞትም እንደቀደሙትና አሁንም እንዳሉት ቅዱሳን ሞቶ ባለመቅረቱና÷ ሕያው ስለሆነ መካከለኛነቱ ዘላለማዊ ነው። ይህንንም ሐዋርያው: - «... እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ÷ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና።» በማለት ገልጾታል፤ (ዕብ. 7÷24-25)።

የዐዲስ ኪዳን ቅዱሳንም ቢሆኑ በራሳቸው ጽድቅ ወደ እግዚአብሔር የመቅረቡና ሌላውንም የማቅረቡ ብቃት የላቸውም። በክርስቶስ አስታራቂነት በኩል ብቻ ነው ሊቀርቡ የሚችሉት።

ተመልካች ዐጥቶና በውሸት ትምህርት ተውጦ እንጂ÷ የቀደሙት አበው ይህንን እውነት አብጠርጥረው ተናግረውታል። የዕብራውያንን መልእክት በተረጐመበት ድርሳኑ ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወርቅ÷ የብሉይ ኪዳንን መካከለኞች ከዐዲስ ኪዳን መካከለኛ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በማነጻጸር ሲናገር : -

> «ወበዝየሰ ለእመ ኮነ ሊቀ ካህናት ዐቢይ ውእቱኬ እስከ ጊዜሁ፤ ዘአመ ኮነ ሳሙኤል ወእለ ከማሁ። በደኃሪሰ አልቦ። እስመ እሙንቱ ሞቱ። ወበዝየሰ አኮ ከማሁ። አላ ዘልፈ ያድኅን በኵሉ ጊዜ፤ ... ወከማሁ ውእቱ አኮ ዘያድኅኖሙ ለእለ ይቀርቡ ኀበ እግዚአብሔር ባሕቲቱ እመንገሌሁ በዝየ አላ ወበከሐከኒ፤»
>
> ትርጓሜ : - «በዚህኛው በብሉይ ኪዳን ታላቅ ካህናት ቢኖር÷ ታላቅ መባሉ እስከ ጊዜው ድረስ ነው። ሳሙኤል እስከ ጊዜው ድረስ እንደኖረ÷ እንደርሱ ያሉትም ካህናት እስከ ጊዜው ድረስ እንደኖሩ÷ በኋላ ግን ታላቅ ሊቀ ካህናት መባላቸው የለም ቀርቷል። በዚህኛው በዐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት በኢየሱስ ክርስቶስ ግን እንደዚሁ አይደለም። ሁልጊዜ ለዘላለም ያድናል እንጂ፤ በሱ አስታራቂነት በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን የሚያድናቸውም÷ በዕለተ ዐርብ ብቻ አይደለም፤ ከዚያም በኋላ ባለው ጊዜ ለዘላለምም ነው እንጂ፤» (13ኛ ድርሳን ቍ. 138-144፤ 147-148)።

ጌታችንም በበኩሉ ዘላለማዊ መካከለኛ በመሆኑ÷ ሌላ ተተኪ አላስፈለገውምና እንደ ሙሴ «አምላክህ እግዚአብሔር እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል።» በማለት ስለ ሌላ ተተኪ መካከለኛ አልተናገረም። ወደ አብ የመድረሻው መንገድና÷ የመግቢያው በር እኔ ብቻ ነኝ፤ ወደ እኔ ኑ! በእኔ በኩል ካልሆነ በስተቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም አለ፤ (ዮሐ. 14÷6፤ 10÷9፤ ማቴ. 11÷28)።

# ክፍል 8 - የተቀደሰ ዘይት

## 8.1 የተቀደሰ ዘይት በብሉይ ኪዳን

ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚለዩ አገልጋዮችም ሆኑ መገልገያ ዕቃዎች፥ ለእርሱ አገልግሎት ብቻ ይውሉ ዘንድ መቀደስ አለባቸው::

ከሙሴ ሕግ መሰጠት አስቀድሞ በዘመነ አበው የነበረው እስራኤል የተባለው ያዕቆብ፥ ከኤሳው ፊት ሲኮበልል በጉዞው ላይ መሽቶበት በአንድ ስፍራ ዐደረ:: በዚያም ስፍራ ተኝቶ ሳለ አስደናቂ ራእይን ተመልክቷል:: ሲነጋም ራእዩን ባየበት በዚያ ስፍራ ተንተርሶ ያደረውን ደንጊያ እንደ ሐውልት አቁሞ በላዩ ላይ ዘይት አፈሰሰበት:: ይህን ያደረገው ያን ስፍራ ለእግዚአብሔር ቤትነት ለመቀደስ መሆኑ ግልጽ ነው፤ (ዘፍ. 28፥10-22) ::

የሙሴ ሕግ ሲሰጥ ይህ አበው ሲጠቀሙበት የነበረው ሥርዐት በሕጉ ውስጥ እንዲካተትና የመቀደሻው ዘይትም በልዩ ጥንቃቄ ከተለያዩ ቅመማ ቅመሞች እንዲዘጋጅ እግዚአብሔር ለሙሴ መመሪያ አስተላልፏል:: በመመሪያውም መሠረት የመቀደሻው ዘይት ከርቤ፥ ጠጅ ሣር፥ ቀረፋ፥ ብርጉድና የወይራ ዘይት ከተባሉ ቅመሞች በልዩ ባለሙያ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ እንዲዘጋጅ ታዟል፤ (ዘፀ. 30፥23-24)::

በዚህ ሁኔታ በተዘጋጀው የተቀደሰ ዘይት አሮንና ልጆቹ፥ ከዚያን ጊዜ አንሥቶም የብሉይ ኪዳን ካህናት ሁሉ ተቀብተው ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተክነዋል፤ (ዘፀ. 30፥30፤ 28፥41፤ 29፥7፤ ዘሌ. 8፥12፤ 30፤ 10፥7፤ 16፥32)::

ነቢያትና ነገሥታትም እንደዚሁ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የተሾሙ አገልጋዮች እንደመሆናቸው ለአገልግሎት የሚሾሙት በዚሁ የተቀደሰ ዘይት ተቀብተው ነበር፤ (1ነገ. 19፥16፤ 1ሳሙ. 9፥16፤ 10፥1፤ 16፥12-13፤ 1ነገ. 9፥6፤)::

ከአገልጋይ ካህናት፥ ነቢያትና ነገሥታት በተጨማሪም፥ የማደሪያው ድንኳንና በውስጡ የሚገኙት ንዋያተ ቅድሳት በአጠቃላይ፥ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ አገልግሎት መስጠት ከመጀመራቸው በፊት በተቀደሰው ዘይት መቀባትና መቀደስ ነበረባቸው፤ (ዘፀ. 29፥30፤ 30፥26-29፤ 40፥9-16፤ ዘሌ. 8፥10-11፤ ዘኍ. 7፥1)::

ካህናት ነቢያትና ነገሥታት እንደዚሁም የቤተ መቅደሱ መገልገያ ዕቃዎች (ንዋያተ ቅድሳት) በተቀደሰው ዘይት መቀባታቸውና መቀደሳቸው፥ በመንፈስ ቅዱስ መቀባታቸውንና መቀደሳቸውን የሚያመለክት ሥርዐት ነው:: በጥላው ዘመን የተቀደሰው ዘይት፥ ወደፊት በዘመነ ወንጌል ምእመናንን ለመቀባትና ለመቀደስ ይገለጽ ዘንድ ላለው ለመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነውና:: በዘይቱ መቀባትም በመንፈስ ቅዱስ ነጽቶና ተቀድሶ ለእግዚአብሔር አገልግሎት መለየትን የሚያሳይ ክንውን ነው::



## 8.2 ቅዱሱ ቅባት በዐዲስ ኪዳን ዘመን

ምእመናነ ወንጌል እግዚአብሔርን ለማገልገል ከኀጢአታቸው እድፍ ታጥበውና ነጽተው የሚቀደሱበት ቅባት፥ እንደ ብሉይ ኪዳኑ ያለ የቅመማ ቅመሞች ውሑድ የሆነውና ለመንፈስ ቅዱስ ጥላ የነበረው ዘይት ሳይሆን፥ ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው::

የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመሲሕነቱ ሊቀ ካህናት ነውና፥ እንደ መልከ ጼዴቅ ባለ ሹመት በዘላለማዊ ተክህኖ ለማገልገል፥ እንደ አሮን በሰው እጅ የተቀመመውን ዘይት ተቀብቶ አልተካነም:: ቅብዐ መንፈስ ቅዱስን በመቀባት ተካነ እንጂ፤ (ኢሳ. 61፥1፤ ሉቃ. 4፥17-19፤ የሐዋ. ሥራ 10፥38)::

በዕብራይስጥ «መሲሕ»፥ በግሪክ «ክርስቶስ» የሚለው የጌታችን የሹመት ስሙ በግእዙ ቅቡዕ (የተቀባ) የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን፥ ቅቡዕነቱም የተከናወነው በመንፈስ ቅዱስ ለመሆኑ የላይኞቹ ጥቅሶች በግልጽ ያስረዳሉ::

ይህም ማለት ክርስቶስ አምላክነት ጐድሎት፥ እንደ ፍጡራን ክብርን ሽቶ ተቀባ ማለት አይደለም:: ሰውን ለማዳን በፈቃዱ ራሱን ዝቅ በማድረጉና ሁሉን ትቶ ከኀጢአት በቀር የሆነውን የሰውን ሁለንተና በተዋሕዶ ምስጢር ገንዘብ በማደረጉ የተከናወነ ነው:: በዚህም ምክንያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: - ዳግማይ አዳም (1ቆሮ. 15፥45)፥ በኵረ ምእመናን (ሮሜ 8፥29)፥ ካህን፥ ሊቀ ካህናት (ዕብ. 7፥20-24)፥ ንጉሥ (ቈላ. 1፥13-14)፥ ነቢይ (ሉቃ. 13፥33)፥ ሐዋርያ (ዕብ. 3፥1) ወዘተ... ሊባል ተገብቶታል::

በዚህ ሁኔታ አገልግሎቱን የጀመረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች የሚሆኑ ደቀ መዛሙርትን ሲጠራ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብተው እንዲያገለግሉ ነው፤ (የሐዋ. ሥራ 1፥8):: ይሁን እንጂ በተለይም የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት ይህን ባለመረዳት ምድራዊ ሹመት ሽልማትን ተስፋ ባደረግ ልብ ነበር የተከተሉት፤ (የሐዋ. ሥራ 1፥6፤ ሉቃ. 24፥21)::

መንፈስ ቅዱስ ጌታ ከሙታን ተለይቶ በተነሣ በኀምሳኛው ቀን፥ ወደ ሰማይ ባረገ በዐሥረኛው ቀን በሐዋርያት ላይ ወረደ:: የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ሲቀበሉም፥ ከብልየት ታድሰው፥ በዕውቀት ጐልምሰው፥ በእምነት ጠንክረው የእግዚአብሔርን መንግሥት የማስፋፋት ሥራቸውን ቀጠሉ::

ስለሆነም የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንደሚመሰክሩት ከሐዋርያት ጀምሮ ያሉ ምእመናን ሁሉ እግዚአብሔርን ለማገልገልም ሆነ እግዚአብሔር የሚያድርባቸው ሕያዋን ቤተ መቅደስ ይሆኑ ዘንድ፥ ከዕፅዋት በተቀመመ ዘይት ፈጽሞ አልተቀቡም፤ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብተው ተሾሙ፥ ተቀደሱ እንጂ፤ (2ቆሮ. 1፥21፤ 1ዮሐ. 2፥20፤27)::

በዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ «ቅዱሱ ቅባት» እየተባለ የተጠራው ያው ራሱ መንፈስ ቅዱስ መሆኑ አያጠራጥርም:: ጌታ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሕያው ቤተ መቅደስ በሆነው በምእመናን ሰውነት ውስጥ ስለማደሩ ሲናገር: - «እርሱም (መንፈስ ቅዱስ) ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ÷ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው:: ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር÷ በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ::» (ዮሐ. 14÷16)::

ሐዋርያው ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ ደግሞ በመልእክቱ ይህን የጌታን ትምህርት በማብራራት ሲጽፍና መንፈስ ቅዱስን ቅዱሱ ቅባት በማለት ሲገልጸው እንዲህ ብሏል: - «እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፤ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም:: ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ÷ እውነተኛም እንደሆነ ውሸትም እንዳልሆነ÷ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ::» (1ዮሐ. 2÷27)::

እንግዲህ ከቤተ ክርስቲያን ልደት አንሥቶ ቤተ ክርስቲያንን እየመራ÷ በስደት ውስጥ በምትሆንበት ወቅትም እያጸና÷ የገሃነም ደጆች እንዳይችሏት በማድረግ÷ አገልግሎቷን በድንቅና በተኣምራት እያስደገፈ ያስፋፋላት መንፈስ ቅዱስ ነው::

ይሁን እንጂ ከጊዜ በኋላ በአንድ የታሪክ አጋጣሚ ቤተ ክርስቲያን ከመሪዋ ከመንፈስ ቅዱስ ተለይታ ራሷ በመረጠችው መንገድ መጓዝ ጀመረች:: ስደትና መከራ እሷን ለማጥፋት በፈተኗት የቀድሞ ዘመናት÷ በዚያው ልክ ጽናቷንና አሸናፊነቷን ያሳየችበት መሪዋን መንፈስ ቅዱስን ከተለየችው በኋላም÷ ፊት ጠላቷ ከነበሩት ከዓለምና ከገዢዋ ጋር በረቀቀ መንገድ ተወዳጀች:: በዚህ ሁሉ ውስጥ ከጌታ ወደተሰጣትና እሷ ግን በፈቃዷ ወደ ተወችው መሪዋ ለመመለስ ፈቃደኝነቷን አንድም ጊዜ ሳታሳይ መንፈስ ቅዱስን እንደተለየችው ቀረች::

ከዚህ በኋላ ነበር በፈቃዷ ያጣችውን መንፈስ ቅዱስን ይተካልኛል ብላ ወደ ዘይት ማንጠር ተግባር ፊቷን ያዞረችው::

ከሐዋርያት አገልግሎት እንደምንረዳው ለአይሁድ ሕዝብ ወንጌልን ሲመሰክሩ ዋና ማእከል አድርገው የተንቀሳቀሱት ክርስቶስን በመሆኑ÷ ከጥላው ወደ አካሉ ዘወር ይሉ ዘንድ አጽንተው ተናገሩ:: እነርሱ ካለፉ ከብዙ ዘመን በኋላ ያለ መሪ የቀረችው ቤተ ክርስቲያን ግን ተቃራኒውን ተግባር ፈጸመች፤ ከአካሉ ወደ ጥላው ዘወር አለች:: በመንፈስ ቅዱስ መመራትን ትታ የእሱ ጥላና ምሳሌ የነበረውን ዘይት መቀመምንም ሥራዬ ብላ ተያያዘችው:: ወደ ኦሪት ሥርዐት የኋሊት ተመልሳለች ላለመባልም ማንጠር ለጀመረችው ዘይት ዐዲስ ታሪክ ፈጠረችለት፤ «ሜሮን» የሚል ስምም አወጣችለት:: በመጨረሻም ስለ መንፈስ ቅዱስ «ቅዱሱ ቅባት» እያሉ የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ያስረዱትን ሁሉ ለዐዲሱ ዘይቷ አወረሰችውና ዐረፈች::

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ይህ አሳዛኝ ሁኔታ የተፈጠረው÷ ብዙዎች ባለማስተዋል ቤተ ክርስቲያን ዕረፍትና ሰላም አገኘች ብለው ከሚናገሩለት ከቈስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት ወዲህ ነው::



በስደት ውስጥ ስታልፍ ቤተ ክርስቲያን ኀይለኛና ድል አድራጊ ነበረች:: ዮሐንስ አፈ ወርቅ የተባለው አባት ይህንን ሲገልጽ በማቴ.16÷18 ላይ ያለውን ቃል ባብራራበት ክፍል እንዲህ ብሏል: - «ሰውን ብትታገልና ብትዋጋ ታሸንፈዋለህ ወይም ያሸንፍሃል፤ ቤተ ክርስቲያንን ግን ፈጽሞ ለማሸነፍ አይቻልም:: ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ ትዋጋለች፤ ተሸንፋ ግን አታውቅም:: ዲያብሎስ ዝናሩን አራገፈ፤ ቀስቱን ጨረሰ:: ቤተ ክርስቲያንን ግን አልጎዳትም::» (የቤ/ክ ታሪክ በዓለም መድረክ ከአባ ጎርጎርዮስ ገጽ 48)::

ይሁን እንጂ ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ የነበራት ኀይልና ጥንካሬ ሁሉ ወደ ቈስጠንጢኖስ ጉያ መሸጐጥ ስትጀምር ተዳከመ፤ ባለፉት ዘመናት ፊት ለፊት ተዋግቶ ሊያሸንፋት ያልቻለው ጠላቷ በረቀቀ መንገድ መጣባት:: ብርቱ የሚያደርጋትን መንፈስ ቅዱስንም አሳድዳ በዘይት ተክታው ስለነበር በዘር÷ በሥልጣንና በመሳሰለው ሥጋዊ ነገር ለመጠላለፍ ተገደደች፤ አንዲት የነበረችው እርስ በርሷ መከፋፈልና መለያየት ነገሠባት::

ወደ ተነሣንበት ነጥብ እንመለስና መንፈስ ቅዱስን «ሜሮን» በተሰኘ ዘይት ከለወጡት ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል ቤተ ክርስቲያናችን አንዷ ናት:: ስለ ሜሮን የፈጠረችውና ተኣምረ ማርያም፤ ስንክሳር (የግንቦት 24 ምንባብ) ማኅሌተ ጽጌ፤ ሰቈቃወ ድንግል፤ በተሰኙትና በሌሎችም አዋልድ መጻሕፍት የተፈጠረው ታሪክም ይዘቱ የሚከተለው ነው: -

«ሄሮድስ ባስነሣው ስደት ምክንያት ድንግል ማርያም ልጇን ኢየሱስን ይዛ÷ ዮሴፍና ሰሎሜን አስከትላ ተሰድዳ ሳለ÷ ሕፃኑ ዕረፍት አስፈልጎት ከአንድ ስፍራ ዐረፉ:: ከዚያም ሕፃኑ ኢየሱስ የዮሴፍን በትር ሰባብሮ ስብርባሪዎቹን ተከለ:: መሬቱንም ቆፍሮ ውሃ አፈለቀና ቢያጠጣቸው ወዲያው በቅለው ትልቅ ዛፍ ሆኑ:: ከዛፎቹም እስከዚያን ጊዜ ድረስ ያልታወቀ ልዩ መዓዛ ያንን ስፍራ ያውደው ጀመር:: ዛፎቹንም ጌታ በለሳን ብሎ ሰየማቸው:: ወደፊት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ለሚጠመቁ ሁሉ ማኅተም የሚሆን ቅብዐ ሜሮን ከነዚህ ዛፎች እንደሚወጣ ለእናቱ ነገራት:: ዛሬም ሜሮን የሚባለው ዘይት የሚዘጋጀው ከነዚሁ የበለሳን ዛፎች ነው::»

መቼም ሜሮን በትክክል የመንፈስ ቅዱስ ምትክ ሆኖ የተሰጠ ቢሆን ኖሮ÷ በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም በዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ትልቅ ስፍራ ተሰጥቷቸው ሊመዘገቡ ከተገባቸው እውነቶች መካከል አንዱ መሆን በቻለ ነበር:: ነገር ግን ስለ ኦሪቱ የተቀደሰ ዘይት ካልሆነ በስተቀር÷ ስለ ሜሮን የተጻፈ አንድም ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ አናገኝም::

ምናልባት አንዳንዶች÷ ሐዋርያት ዘይት እየቀቡ ድዉያንን ስለ መፈወሳቸው የተጻፈውን÷ ከዚህ ጋር ለማጣጋት ያስቡ ይሆናል፤ (ማር. 6÷13፤ ያዕ. 5÷14):: ይህ ግን በቤተ ክርስቲያናችን ምስጢረ ቀንዲል ተብሎ ለሕሙማን የሚፈጸም የፈውስ አገልግሎት ነው:: ዛሬ ዛሬ እንዲያውም ጸበል ስፍራውን እያስለቀቀው ይገኛል::

ሜሮን ግን ከዚህ በተለየ መንገድ የመንፈስ ቅዱስን ስፍራ ተክቶ አገልግሎት የሚሰጥ ነው። ከጥምቀት በኋላ መንፈስ ቅዱስን ስለ መቀበል ተጠማቂው ሜሮን የተባለውን ዘይት ይቀባል፤ ከዚህም በተጨማሪ ዐዳዲስ ንዋያተ ቅድሳት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ተባርከው ሜሮን ይቀባሉ። ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ በሜሮን ተቀብቶ ይከበራል፤ (ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ ገጽ 122)።

ይህ ሁሉ የሚያሳየው በቤተ ክርስቲያናችን የመንፈስ ቅዱስን ስፍራና የሚሰጠውን የመቀደስና የማክበር አገልግሎት ሜሮን እንደ ቀማው ነው፤ (ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቁ.12 ገጽ 5-6)።



# ክፍል 9 - ቤተ መቅደስ

## 9.1 ቤተ መቅደስና አገልግሎቱ በዘመነ ኦሪት

ሰው ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሆን ስለ ተፈጠረ እግዚአብሔርን ያመልክና ከእርሱ ጋር ይገናኝ ዘንድ ተገቢው ነው። ለዚህም ደግሞ አንድ የተወሰነ ስፍራ ይመርጥ ዘንድ አስፈላጊነት ነበረው። ሕገ ኦሪት ከመስጠቱ በፊት ባሉት ዘመናት የነበሩት አበው፥ እግዚአብሔር አምላክ ለነርሱ በተገለጠበትና ተስፋ በሰጠበት ስፍራ መሠዊያ ሠርተው እግዚአብሔርን ያመልኩ የነበረው ለዚህ ነበር፤ (ዘፍ. 8፥20፤ 12፥6-8፤ 13፥18፤ 22፥9፤ 26፥25፤ 33፥20፤ 35፥1-7፤ ዘፀ. 17፥15)።

ሕገ ኦሪት ሲሰጥ ግን ለእግዚአብሔር ሕዝብ የአምልኮ ማእከል የሚሆን አንድ ስፍራ በማስፈለጉ፥ እግዚአብሔር ለዚህ አገልግሎት እንድትውል ኢየሩሳሌምን ቅድስት ሀገሩ አድርጎ መረጣት፤ (ዘዳ. 12፥11፤1ነገ. 8፥15-16፤ 11፥13)። በውስጧም ስሙ የሚጠራበት መቅደስ እንዲሠሩ የእስራኤልን ልጆች አዘዘ፤ (ዘፀ. 25፥8)። ኢየሩሳሌም ራሷም የእግዚአብሔር ቤት ተብላ ትጠራለች፤ (መዝ. 121(122)፥1-4)። ስለሆነም በዚያ ዘመን ከኢየሩሳሌምና በውስጧ ከሚገኘው መቅደስ ውጪ፥ በሌላ ስፍራ መሥዋዕት እንዲሠዋም ሆነ አምልኮ እንዲፈጸም አልተፈቀደም፤ (ዘዳ. 12፥13-14)።

ከኢየሩሳሌም ውጪ በሌሎች አውራጃዎች ያሉ አይሁድ የእግዚአብሔርን ስም ያመሰግኑ ዘንድ፥ ለእስራኤል ምስክር ሊሆኑ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲወጡ ታዘዋል፤ (መዝ. 121(122)፥4)። በተለይም ደግሞ እስራኤላውያን ወንዶች በዓመት ሦስት ጊዜ ማለትም በቂጣ በዓል፥ በሰባቱ ሱባዔ በዓል፥ (በዓለ ኀምሳ) እና በዳስ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም የመውጣት ግዴታ ነበረባቸው፤ (ዘፀ. 23፥17፤ ዘፀ. 34፥23፤ ዘዳ. 10፥16)። ከዚህ ውጪ በግል ጉዳያቸው መሥዋዕት ማቅረብ ቢፈልጉም ወደ ኢየሩሳሌም መውጣታቸው የግድ ነበር። በተለያየ መንገድ የአይሁድን እምነት የተቀበሉ ከአሕዛብ ወገን የሆኑ መጻተኞችና ጃንደረቦችም በዚሁ ሁኔታ ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ እንደ ነበረ ተጽፏል፤ (የሐዋ. ሥራ 8፥27)።

ወደ ኢየሩሳሌም መምጣት ያልቻሉና በተለይም ደግሞ በስደት አገር የነበሩት ደግሞ እግዚአብሔርን ለማምለክና ወደ እርሱ ለመጸለይ ሲፈልጉ፥ እግዚአብሔር መቅደሱ ወዳደረጋትና ያድርባት ዘንድ ተስፋ ወደሰጠባት ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ ዞረው ይጸልዩ ነበር። ለዚህም እንዲረዳቸው የጸሎት እልፍኛቸውን መስኮት ኢየሩሳሌምን ማግኘት በሚቻልበት አቅጣጫ በኩል ይሠሩ ነበር። ይኸውም በመስኮታቸው አሻግረው በመማተር ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ ለመጸለይ ነው፤ (ዳን. 6፥10፤ 1ነገ. 8፥46-49)።

ይህ ሁሉ እንዲያው በከንቱ የሆነ አይደለም፤ እግዚአብሔር ማደሪያው ትሆን ዘንድ ኢየሩሳሌምን በመምረጡና በዚያ ወይም

ወደዚያ ቤተ መቅደስ የሚቀርበውን ልመናና ጸሎት ለመቀበል በመውደዱ ነው፤ (መዝ. 131(132)÷13-16፤ 1ነገ. 9÷3)፡፡ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ለማደሩ የቤተ መቅደስ መኖር ወሳኝ ነገር ነበርና፤ (ዘፀ. 25÷8)፡፡

በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ ከመታነጹ አስቀድሞ፥ አምልኮተ እግዚአብሔር ይፈጸም የነበረው ከአንድ ስፍራ ተነቅሎ ሌላ ስፍራ ላይ በሚተከል ድንኳን ውስጥ ነበር፡፡ ይህም ድንኳን የማደሪያው ድንኳን (ደብተራ ኦሪት) በመባል ይታወቃል፤ (ዘፀ. 26፤ 36÷8-58፤ 2ሳሙ. 7÷5-6)፡፡

ማደሪያው፥ ድንኳን እንዲሆን ያስፈለገበት ምክንያት እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው በምድረ በዳ ተጓዦች ስለነበሩ ነው፡፡ ወደ ርስታቸው ገብተው ከወረሱ በኋላም ቢሆን አገልግሎቱ የቀጠለው በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ነበር፡፡ ንጉሡ ዳዊት ድንኳኑን በቤተ መቅደስ ለመተካት ዐሰበ፡፡ ሆኖም እርሱ ሊሠራ እንደማይችልና፥ ልጁ ሰሎሞን ቤትን እንደሚሠራለት እግዚአብሔር አመለከተው፡፡ ዳዊትም ለቤተ መቅደሱ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለልጁ ለሰሎሞን ሰጥቶ ቤተ መቅደስን እንዲሠራ አዘዘው፤ (2ሳሙ. 7÷5-12፤ 1ዜና. 22÷3-5)፡፡

ሰሎሞንም የእግዚአብሔርን ቤት እጅግ ውብና ድንቅ አድርጎ ሠራው፡፡ ቤተ መቅደሱ ሁለት ውስጣዊ ክፍል ነበረው፡፡ የመጀመሪያው መቅደስ (ቅድስት) የሚባለው ሲሆን፥ ውስጠኛው ክፍል ደግሞ ቅድስተ ቅዱሳን ይባል ነበር፤ (ዘፀ. 26÷33፤ 1ነገ. 8÷6፤ 10፤ ዕብ. 9÷1-7)፡፡

በመቅደሱ ወስጥ ከወርቅ የተሠሩ ዐሥር መቅረዞች፥ የወርቅ መሠዊያና ኅብስት የነበረበት የወርቅ ገበታ ነበሩ፤ (1ነገ. 7÷48-49፤ ዕብ. 9÷2)፡፡ በቅድስተ ቅድሳኑ ውስጥ ደግሞ የኪዳኑ ታቦትና የወርቅ ማዕጠንት ነበሩ፤ (ዕብ. 9÷3-4፤ ዘሌ. 16÷12-13)፡፡

ካህናት ወደ መቅደሱ ለአገልግሎት ዘወትር ሲገቡ፥ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ግን ሊቀ ካህናት ብቻ በዓመት አንድ ጊዜ ለራሱና ለሕዝቡ ኀጢአት የሚያቀርበውን ደም ይዞ ይገባል፤ ሕዝቡም በውጪ ሆነው ይጠባበቃሉ፤ (ዕብ. 9÷6-7)፡፡

በዚህ ሁኔታ የቆመው ቤተ መቅደስ እስከ መታደስ ዘመን ድረስ ምድራዊ አገልግሎት የሚፈጸምበት፥ ለሚመጣው ሰማያዊ መቅደስ ጥላና ምሳሌ ሆኖ የሚያገለግል እንጂ ለዘላለማዊ አገልግሎት የተዘጋጀ አልነበረም፤ (ዕብ. 9÷9-10)፡፡

ነገር ሁሉ የሚታደስበት ዘመነ ክርስቶስ ሲመጣ (የሐዋ. ሥራ 3÷21)፥ ቤተ መቅደሱ የተቀጠረለት የአገልግሎት ዘመን ስለተፈጸመና ስላበቃ፥ ጌታ ክርስቶስ ስለኛ ነፍሱን በመስጠት መታረቂያችን የሚሆን ደሙን ባፈሰሰ ሰዓት፥ የኦሪት ሊቀ ካህናት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚገባበት ቅድስተ ቅዱሳን ተጋርዶበት የነበረው መጋረጃ ለሁለት ተቀደደ፡፡

ይህም በክርስቶስ ቤዛነት የሚያምኑ ሁሉ፥ ከምድራዊ አገልግሎት ወደ ሰማያዊ አገልግሎት መሸጋገራቸውን ያበሠረ ዜና ነበር፡፡ ይሁን እንጂ



መልካሙ ዜና ጆሮአቸውን ያሳከካቸው አይሁድና ተረፎቻቸው የተቀዳደደውን መጋረጃ ጥፈውና ደርተው አሁንም ጊዜ ያለፈበትን ምድራዊ የመቅደስ አገልግሎት እያከናወኑ በመንፈሳዊ ባርነት ሥር አሉ፡፡

የመጋረጃው መቀደድ የአገልግሎቱ ዘመን በማብቃቱ ሳይሆን፥ በስሕተት ወይም በአንድ የተቈጣ መልአክ ሰይፍ እንደተከናወነ የሚያስቡ ኦሪታውያንም በቤተ ክርስቲያናችን አሉ፡፡ እነዚህ ክፍሎች ማቴ. 27÷51ን በተረጐሙበት አንድምታቸው ጠቅሰው እንዲህ ብለዋል:-

« ወመጽአ መልአክ ኀሩይ እማእከለ ኵሎሙ መላእክት፥ እንዘ ይእኀዝ በእዴሁ ሰይፎ ክሡተ፤ ከመያጥፍኦሙ ለዐላውያን ፍጡነ፥ ወሶበ ከልአቶ ምሕረቱ ለክርስቶስ፥ ዘበጦ ለመንጦላዕተ ምኵራብ ወሠጠጦ፤ ወረሰዮ ፪ተ እምላዕሉ እስከ ታሕቱ፡፡»

ትርጓሜ: - «ከመላእክት መካከልም አንዱ የተመረጠ መልአክ፥ በእጁ የተመዘዘ ሰይፍ ይዞ ዐመፀኞች አይሁድን ፈጥኖ ያጠፋ ዘንድ መጣ፡፡ ነገር ግን የክርስቶስ ምሕረቱ በከለከለችው ጊዜ፥ ይህ መልአክ የምኵራቡን መጋረጃ ቀደደው፡፡ ከላይ እስከ ታችም ለሁለት ከፈለው፡፡» (አንድምታ ወንጌል ማቴ. 27÷51ን ተመልከት)፡፡

ይህን መነሻ ያደረጉ ተከታዮቻቸውም በዚህ ውሸት ላይ ሌላ ውሸት ጨምረውና አስፋፍተው «መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ጌታ በተሰቀለ ዕለት በአይሁድ ሥራ ተናዶ፥ ላጥፋቸው ሲል የጌታ ምሕረት ከለከለቸው፡፡ ከዚያም በእጁ የያዘውን ሰይፍ ቢወረውረው የቤተ መቅደሱን መጋረጃ ከሁለት ከፈለው፡፡ ሰይፉ አሁንም ድረስ እየሄደ ይገኛል፡፡ ሰይፉ መሬት ካረፈ ምጽአት ይሆናል፡፡» እያሉ በአፍም በመጣፍም ይሰብካሉ፡፡

በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሲመረመር ግን ከሐሰት በቀር አንድም እውነትነት የለውም፡፡ ትረካውም ሌላ መጋረጃ ሰቅሎ ሕዝባችንን ወደ ኦሪት ሥርዐት የኋሊት ከመመለስ በቀር አንዳች አልጠቀመም፡፡

ወንጌልን አለአግባቡ እንተረጕማለን ለማለትና የምስጢሩ ቊልፍ ሁሉ በእጃችን ነው ለማሰኘት ብለው የፈጠሩት ይህ የአሮጊቶች ተረት፥ የእግዚአብሔርን ቃል ፊት ለፊት ተቃውሞ ይገኛል፡፡

ቅዱሳን መላእክት የቃሉን ድምፅ ሰምተው ቃሉን የሚፈጽሙና ፈቃዱን የሚያደርጉ አገልጋዮቹ ናቸው፤ (መዝ. 101(102)÷20-21)፡፡ የክርስቶስ መሞትም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ታላቅ ፍቅር የገለጸበትና በበጎ ፈቃዱ የተከናወነ ዘላለማዊ ዕቅዱ ነው፤ (ዮሐ. 3÷16፤ ሮሜ 5÷8፤ የሐዋ. ሥራ 2÷23)፡፡

ቅዱሳን መላእክት ፈቃደ እግዚአብሔርን ለመፈጸም ብርቱዎችና ኀያላን እንደ መሆናቸው፥ ለሰው የተደረገው ይህ ታላቅ ማዳን በእነርሱ ዘንድ መታወቁ፥ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዐሳብ

ልቡናችንን አነሣን፤ ኅሊናችንንም ከፍ ከፍ አደረገን» (ቅዳ. ዮሐ. ወልደ ነጐድጓድ ቍ. 3)::

እዚህ ላይ የምናስተውለው ቁም ነገር÷ ክርስቲያኖች በአምልኮ ጊዜ በመንፈስና በእውነት ሆነው በሰማይ የመገኘታቸው ምክንያት÷ በሰው እጅ የታነጸችና በምድራዊ ቍሳቍሶች የተሞላችዋ ሳትሆን በእግዚአብሔር የተተከለችው ሰማያዊት መቅደሳቸው በዚያ ስላለች ነው:: የዐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስም በዚያ አለ፤ (ዕብ. 8÷1-2)::

የብሉይ ኪዳን ሰዎች በምድራዊቱ መቅደስ ተገኝተው÷ ወይም በርቀት ያሉ ወደ ምድራዊቱ መቅደስ አቅጣጫ ዞረው ይጸልዩ እንደነበረ ሁሉ÷ ከላይ እንደቀረቡት ማስረጃዎች ክርስቲያኖችም በሰማያዊቱ መቅደስ ውስጥ በእምነት ተገኝተው ይጸልያሉ ማለት ነው::

ምድራዊቷ መቅደስ ለሰማያዊቷ መቅደስ ምሳሌና ጥላ በመሆኗ÷ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናት ሆኖ ለማገልገል ወደ እርስዋ አልገባም፤ ወደምትበልጠውና ወደምትሻለው መቅደስ ገባ እንጂ፤ (ዕብ. 9÷11፤24)::

በምድራዊቷ መቅደስ ውስጥ ካሉትና በኦሪቱ ሥርዐት መሠረት አምልኮተ እግዚአብሔር ይፈጸምባቸው ከነበሩት ንዋያተ ቅድሳት መካከል÷ ምንም ምን በሰማያዊቷ መቅደስ ውስጥ የለም:: ሁሉ ነገር ዐዲስ÷ መንፈሳዊና ሰማያዊ ነው::

አንዳንዶች ይህን እውነት ለመቃወም በማሰብ በራእ. 11÷19 ያለውን በመጥቀስ÷ በሰማይ ባለው መቅደስ ውስጥ እንደ ብሉይ ኪዳን ያለ ታቦት አለ ሊሉ ይችሉ ይሆናል:: መቼም በራእየ ዮሐንስ ውስጥ የተገለጹትን ሁኔታዎች ሁሉ ቃል በቃል መተርጐም አይቻልም::

እያንዳንዱ በተለያዩ ነገሮች የተገለጸው ሥዕላዊ የሚመስለው መግለጫ÷ ሌላን ነገር ሊያመለክት የገባ መሆኑ ግልጽ ሲሆን÷ ለሰው በሚገባ መንገድ ተገልጸ እንደተጻፈም ማስተዋል አያዳግትም::

ለምሳሌ ዲያብሎስ ግዙፍ የሆነ÷ የሚታይና የሚዳሰስ አካል ያለው ሳይሆን መንፈስ ነው:: በራእ. 20÷1-3 ላይ ግን ዲያብሎስን የእግዚአብሔር መልእክ በሰንሰለት እንዳሰረው ተገልጸል:: በውኑ መንፈስ በሰንሰለት ይታሰራልን? ስለዚህ ሰንሰለቱንስ ሰንሰለት ነው ብለን ልንተረጕመው እንችላለን? በፍጹም! ይህ ለሰው በሚገባው ቋንቋ ለማስረዳት የቀረበ ገለጻ ነው፤ ወንጀለኛ በሰንሰለት ወይም በእግር ብረት መታሰሩን ሰው ሁሉ ያውቀዋል:: በሺሁ ዓመት መንግሥት ወቅት የዲያብሎስን መታሰር ለሰው በሚገባው ሁኔታ ለመግለጽ ሲባል በሰንሰለት ታሰረ ተባለ::

እንደዚሁም ሁሉ በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ሲከፈት÷ የኪዳኑ ታቦት በመቅደስ ውስጥ መታየቱ ለእስራኤል ሕዝብ በድንጋይ ጽላት ጽፎ የገባውንና÷ ለክርስቲያኖችም በልባቸው ጽላትነት ላይ በመንፈስ የተጻፈውን ዘላለማዊ ቃል ኪዳኑን÷ ዛሬም በታማኝነት እንደሚጠብቅ ለማመልከት÷ ወይም ደግሞ ሰውና እግዚአብሔር የተገናኙበትን አማናዊ



የዐዲስ ኪዳን ታቦት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማሳየት ካልሆነ በቀር÷ ታቦቱ ታቦት ነው ተብሎ ቃል በቃል ለመተርጐም ያዳግታል::

ስለዚህ በሰማይ ባለችው የዐዲስ ኪዳን መቅደስ ውስጥ ምንም ዐይነት ምድራዊ ቍሳቍስና ሥርዐት የለም፤ ሁሉ ነገር መንፈሳዊ ነው:: ይህንንም እውነት የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ያረጋግጡልናል:

-

> «ብፁዕ ጳውሎስ ናሁ ከሠተ ይእዜ ከመ ሐዳስ ሕግ÷ ትጌይስ እም ሕገ ብሊት፤ እስመ አልቦ ውስተ ሐዳስ ሕግ ምንትኒ ሥርዐተ ሥጋ÷ ወኢግብረ ትእዛዝ÷ ኢምኵራብ÷ ወኢቅድስተ ቅዱሳን÷ ኢካህን ÷ ዘከመዝ ሥርዐተ ክህነቱ÷ ወኢትእዛዘ ኦሪት ዘይትዐቀብ በከርሠ ታቦት:: አላ ኵሉ ትእዛዛቲሁ ሉዓላዊ ወፍጹም፤ ወአልቦ ውስቴቱ ምንትኒ ሕገ ሥጋ አላ መንፈሳዊ ኵለንታሁ፤»
>
> ትርጓሜ: - «ብፁዕ ጳውሎስ እነሆ አሁን ዐዲሲቱ ሕግ እንደምትሻል አስረዳ፤ በወንጌል ምንም ምን የሥጋ ሥርዐት የለም:: የትእዛዝ ሥራ የለም፤ ምኵራብ የለም፤ ቅድስተ ቅዱሳን የለም፤ የክህነቱ ሥርዐት እንደ ኦሪቱ የሆነ ካህንም የለም፤ በድንጋይ ጽላት ተጽፎ በታቦቱ ውስጥ ተቀምጦ የሚጠበቅ የኦሪት ትእዛዝም የለም:: ሥርዐቱ ሁሉ ሰማያዊና ፍጹም ነው እንጂ÷ በውስጡም የሥጋ ሕግ ምንም ምን የለም:: ሁለንተናው መንፈሳዊ የሆነ ሕግ ነው እንጂ፤» (8ኛ ድር. ዘዮሐ. አፈ ወርቅ ቍ. 2፤5-12)::

ወደ ተነሣንበት ርእሰ ጉዳይ ስንመለስ በኦሪቱ ቤተ መቅደስ ካህናት÷ በተለይም ሊቀ ካህኑ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በብዙ የሞት ፍርሀት ተይዞ ይገባ እንደነበር ግልጽ ነው:: ምክንያቱም ከተሰጠው የቤተ መቅደስ ሕግና ሥርዐት አንዲቱን ቢያዛንፍ ሊቀሥፍ ይችላልና::

በሰማያዊቱ መቅደስ ግን እንዲህ የለም:: የመቅደሲቱ አገልጋይ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞቱ እንዲሽር÷ በሕይታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሀት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ የተገባው ሊቀ ካህናት በመሆኑ (ዕብ. 2÷14-15)÷ የሞት ፍርሀት ተወግዷል::

ይህም ብቻ አይደለም÷ ወደ ሰማያዊቱ መቅደስ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ በዓመት አንድ ቀን ብቻ ገብቶ የሚወጣ ሳይሆን÷ አንድ ጊዜ ገብቶ ሳይወጣ በዚያ ለዘላለም ተቀምጧል፤ (ዕብ. 6÷19-20)::

ከእርሱ የተነሣም ክርስቲያኖች እንደ ሕዝበ እስራኤል ከመቅደስ ውጪ መቆም የለባቸውም:: ኢየሱስ ክርስቶስን ተከትለው እርሱ በመረቀላቸው በዐዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም÷ በሥጋው መጋረጃነት በኩል የመግባት ድፍረት ተሰጥቷቸዋል::

(ዕብ. 10፥19-20)፤ ይህንንም ሲያስረዳ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ ብሏል፡ -

> «እስመ ዝኩ ካህን ኮነ ይትከሀን በውሳጤ፤ ወኵሉ ሕዝብ ይቀውሙ በአፍአ፤ ወሥርዐትሰ ዘእንቲአነ አኮ ዘይበውእ ካህን ባሕቲቱ ውስተ መቃድስ፥ አላ ንሕነኒ ንበውእ ከማሁ፡፡»

> ትርጓሜ፡ - «የኦሪቱ ሊቀ ካህናት በውስጥ ሆኖ፥ ሕዝቡ ሁሉ ግን በውጪ ይቆም ነበር፤ የኛ የክርስቲያኖች ሥርዐት ግን ሊቀ ካህናቱ ብቻ ወደ መቅደስ የሚገባበት አይደለም፤ እኛም እንደርሱ እንገባለን እንጂ፡፡» (13ኛ ድር. ዘዮሐ. አፈ. ቍ. 61-64)፡፡

ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን እግራቸውን በወንጌል ላይ ያቆሙ አስመስለው ልባቸውን ከኦሪት ጋር ያደረጉ ብዙ ወገኖች አሉ፡፡ እኒህ ወገኖች ከጥላው ወደ አካሉ ዘወር በማለት፥ ወደ ሰማያዊቱ ቅድስተ ቅዱሳን ቀዳሚ ሆኖ የገባውን ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተከትለው በእምነት በመግባት፥ በዚያ የሚገኙት ቅዱሳን እግዚአብሔርን የሚያመልኩበትን ዐዲስ ሥርዐት ማየት ተስኗቸዋል፡፡ በመሆኑም በምንም መንገድ የአካሉ ጥላ እንኳ ሊሆን ፈጽሞ የማይችለውን በሰው የተሠራ መቅደስ አቁመው፥ የመቅደሳቸው አገልጋዮች የሆኑትን ሰዎች ብቻ በማስገባት ሕዝቡን በውጪ የሚያቆሙበት ሁኔታ መኖሩን ሁሉም ያውቀዋል፡፡

እነዚሁ ወገኖች በአጠቃላይ ምድራዊውን መቅደስ ለቅቀን አንወጣም በሚል ዐይነት ፈሊጥ ስለተያዙ፥ በሰማይ ያለችውን መቅደስ ላለመቀበል በማሰብ ይመስላል፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናት ሆኖ በእጅ ወዳልተሠራችውና እግዚአብሔር በተከላት ድንኳን ማገልገሉ የተነገረበትን ክፍል በማስተባበል፥ በሰማይ ያለው መቅደስ የተባለው «መቅደስ» ሳይሆን «መስቀል» ነውና ወደ መስቀል ለማገልገል ገባ የሚል ትርጓሜ ሰጥተውታል፡፡

ዕብ.8፥2 ላይ ለተጻፈው ቃል የተሰጠው ባለአንድም ትርጓሜ እንዲህ ይላል፡ - «በሰው ፈቃድ ያይደለ በሱ ፈቃድ በተተከለች በደብተራ መስቀል ለቅዱሳን ሲያገለግል ኖሮ ነበር፡፡» (ከቅ/ጳውሎስ መልእክታት አንድምታ የዕብ. 8፥2 አንድምታን ተመልከት)፡፡

ወደፊት እንደምናየው በኦሪቱ ሥርዐት መሠረት መሥዋዕት ከሰፈር ውጪ ከተሠዋ በኋላ፥ ሊቀ ካህኑ የራሱንና የሕዝቡን ኀጢአት ለማስተስረይ የሚሆነውን ደም ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ በዚያ ያስተሰርይ ነበር፡፡

በዚሁ አምሳል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም፥ የዓለሙን ኀጢአት የሚያስተሰርይ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ቀርቧል፡፡ በመሥዋዕትነቱም የሕዝቡን ኀጢአት ተሸክሞ ከኢየሩሳሌም ከተማ ወጣ ባለ ስፍራ በመስቀል ላይ ተሠውቷል፤ (ዘሌ. 16፥27፤ ዕብ. 13፥11-12፤ ዮሐ. 19፥17፤20)፡፡

በሊቀ ካህንነቱ ደግሞ የገዛ ደሙን ይዞ ወደሚያገለግልባት ሰማያዊት መቅደስ ውስጥ ገብቷል፤ (ዕብ. 9፥11-12)፡፡

ስለሆነም መስቀል ላይ የተከናወነው ሥራ ሊወክል ወይም ሊያሳይ የሚችለው፥ ከሰፈር ውጪ ይከናውን የነበረውን ተግባር ነው፡፡



የእግዚአብሔር ቃል መቅደስና እውነተኛይቱ ድንኳን (ዕብ. 8፥2) የሚላት መስቀልን ሳይሆን፥ በሰማይ ያለችውንና ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናት ሆኖ የገባባትን መቅደስ መሆኑን ሲያስረዳ ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ ብሏል፡ -

> «ወከማሁ ለሰማይኒ ሰመዮ ደብተራ፤ እስመ ህየ ቦአ ሊቀ ካህናት ዘውእቱ ባሕቲቱ»

> ትርጓሜ፡ - «እንደዚሁም ሰማይን እውነተኛቱ ድንኳን /መቅደስ/ አለው፤ እርሱ ብቻውን ሊቀ ከህናት የሚሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚያ ገብቷልና፡፡» (15ኛ ድር. ቍ. 100-101)፡፡

በዐዲስ ኪዳን ሌላውና ትልቁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሕዝቡ ራሱ ነው (1ቆሮ. 3፥16-17፤2ቆሮ. 6፥16፤ ራእ. 21፥3)፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሥጋውን ቤተ መቅደስ ብሎ ጠርቶታል፤ (ዮሐ. 2፥19-21)፤ በራእይ መጽሐፍም፥ በፍጻሜ ዘመን ይመጣ ዘንድ ባለው ዓለም፥ ሌላ ቤተ መቅደስ እንደማይኖርና ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደስ እንደሚሆኑ ተጽፏል፤ (ራእ. 21፥22)፡፡

## 9.3 ቤተ መቅደስና ሌሎች ኢየሩሳሌሞች በቤ/ክ ዘመን

ወደ ምድራችን ቅድመ ክርስትና ገብተው በሕዝባችን ባህልና አኗኗር ውስጥ ሥር የሰደዱት የአይሁድ ሥርዐቶችና ወጎች፥ በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን አማካይነት የተሰበከውን ወንጌል ብዙም አላራመዱትም። በእሾኽ መኻል እንደወደቀው ዘር አድርገውታል። ስለዚህ ክርስትናው በኦሪት ነገሮች ታንቆ ተይዟልና፥ ሕዝባችን ወደ እውነት ሙሉ በሙሉ ዘወር ለማለት መንፈሳዊ ዐቅም ዐጥቷል።

በቤተ ክርስቲያናችን ከሚታዩት ኦሪታዊ ነገሮች መካከል ጎላ ያለ ቦታ ያለውና፥ የሕንጻ ቤተ ክርስቲያንን ስፍራ በውስጠ ታዋቂነት አስለቅቆ የሚገኘው ቤተ መቅደስ ነው ቢባል የተጋነነ አገላለጽ ሊሆን አይችልም። ለዚህም አሁን የምናየውን የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ውስጣዊ ይዘት፥ አሠራር፥ በውስጡ ያሉት ንዋያተ ቅድሳት፥ አገልጋዮቹና የሚሰጡት አገልግሎት ማስረጃ ሊሆኑን ይችላሉ።

እንዲህ ማለት ግን ዛሬ በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ ኦሪታዊ ነው ወደ ማለት አያደርሰንም። ከኦሪት በተወሰዱ ንዋያተ ቅድሳትና ሥርዐቶች በመጠቀም የዐዲስ ኪዳን ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎች አገልግሎቶች መከናዎናቸው አልቀረምና።

ዐዲስ ኪዳን በክርስቶስ ደም ከጸናበት ጊዜ አንሥቶ ጌታም ሆነ ሐዋርያቱ፥ የኦሪት ንዋያተ ቅድሳትና ሥርዐቱን ጭምር ተጠቅመው ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የሚፈጸመውን ድብልቅልቅ ሥርዐት ሲፈጽሙ አናይም። ይህም ሊታወቅ፥ ጌታ ሥርዐተ ቊርባንን ሲመሠርት የኦሪቱን ቤተ መቅደስም ሆነ ከንዋያተ ቅድሳቱ መካከል አንዱን እንኳ አልተጠቀመም፤ (ሉቃ. 22÷7-13)።

ታዲያ ይህ ትውፊት ከወዴት መጣ? እነማንስ አስተላለፉልን? የሚል ጥያቄ ቢነሣ ምላሽ ሊሆን የሚችለው፥ በቀጥታ ከኦሪቱ ሥርዐት ወይም ደግሞ በዘመነ ወንጌል ኦሪታዊነትን ደባልቀው እያራመዱ ቤተ ክርስቲያንን ገና ከመመሥረቷ ጊዜ ጀምሮ ሲያውኳት ከነበሩት ኦሪታውያን ክርስቲያኖች ነው የሚለው ነው።

ነገር ግን ከዚህ ሐቅ ለመሸሽ በማሰብ ይመስላል «ክርስቲያን» የሚለውን ስም ሽፋን ያደረጉና በውስጣዊ ማንነታቸው በሥርዐተ ኦሪት ውስጥ የሚገኙት ወገኖች፥ የዚህ ኦሪታዊ ትውፊታቸው ጀማሪ የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ተከታዮቹ ሐዋርያት እንደሆኑ አድርገው ያቀረቡበት ሁኔታ አለ።

ከልባቸው አንቅተው ስለ ድንግል ማርያም ትንሣኤና ዕርገት በፈጠሩት ታሪክ ውስጥ፥ ጌታ ማርያምን መንበር፥ ጴጥሮስን የሚራዳ ቄስ፥ እስጢፋኖስን ዲያቆን፥ ራሱ ዋና ቄስ ሆኖ ቅዳሴ ቀድሶ እንዳቈረባቸው ጽፈዋል፤ (የእሑድ ውዳሴ ማርያም አንድምታ መጨረሻ ላይ ያለውን የዕረፍቷን ታሪክ ተመልከት)።

መቼም ይህ ከመጀመሪያ ያልነበረውንና የኋላ አበው የሠሩትን የቅዳሴ ሥርዐት ጥንታዊና በጌታ የተጀመረ ለማስመሰል የቀረበ ትረካ



መሆኑ ግልጽ ነው። ጊዜ የወለዳቸው የስሕተት ትምህርቶችና ሥርዐቶች ተአማኒነት እንዲያጡ፥ ወይም ደግሞ ተቀባይ እንዲኖራቸው ከተፈለገ በጌታና በሐዋርያቱ እንደ ተጀመሩ ተደርገው መቅረባቸው በተለይ በቤተ ክርስቲያናችን የተለመደ ነገር ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ በተለይም ደግሞ ቅዱሳን ሐዋርያቱ ካለፉ በኋላ በስማቸው እየተደረሰ ወደ ቤተ ክርስቲያን በገፍ የገባውን ትክክለኛ ያልሆነ አስተምህሮ፥ እነርሱ እንዳላስተማሩትና እንዳላደረጉትም ግልጽ ነው። ቤተ መቅደሱንና በውስጡ የሚከናወነውን ኦሪታዊ አገልግሎት በሚመለከትም፥ ይህን ኦሪታዊ ነገር በክርስትና መንፈስ ተርጕመን እንገልገልበት የሚል አቋምም አልነበራቸውም።

እንደ ገናም እነርሱ እንኳንስ የምድራዊቱ መቅደስ አገልጋዮች ሊሆኑ ይቅርና፥ በነቢያት የተነገረውን ቃል በማስተዋልና የእግዚአብሔርን የዐዲስ ኪዳን ዕቅድ በመረዳት፥ ልዑል፥ ዛሬ በምእመናን በራሳቸው አድሮ ከሚኖር በቀር፥ የሰው እጅ በሠራው ሕንጻ ውስጥ እንደማያድር ደጋግመው ተናግረዋል፤ (ኢሳ. 66÷1-2፤ የሐዋ.ሥራ 7÷48-50፤ 17÷24)።

ምድራዊው መቅደስ የተወሰነለት የአገልግሎት ዘመን በማብቃቱ ዛሬ በነበረበት ሁኔታ ወይም ሌሎች መሻሻሎች ተደርገውበት ሊቀጥል የማይችል መሆኑ ቢታወቅም፥ የአገልግሎቱን መቋረጥ የማይፈልጉ ወገኖች በነበረበት ሁኔታ ሳይሆን፥ ተሻሽሎና በክርስትና መንፈስ ተተርጕሞ አገልግሎቱን መቀጠል እንዳለበት ያምናሉ። ለዚህም ድጋፍ ይሆኑናል የሚሏቸውን ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳሉ። ከሚጠቀሱትም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፤ (ዮሐ. 2÷13-17፤ ማቴ. 21÷12-13፤ ሉቃ. 24÷53፤ ሐዋ. ሥራ 2÷46፤ 3÷1)።

ከራስ ሐሳብ በመጀመር ሳይሆን ቃሉ ከተጻፈበት ዐላማ ተነሥተን እነኚህን ጥቅሶች ብንመረምራቸው፥ የቤተ መቅደሱ አገልግሎት ዛሬም ቀጣይነት አለው የሚል ፍቺ የላቸውም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ መቅደሱን ከንግድ ቤትነት ማጽዳቱ፥ ተገቢነት የነበረውና በመዝሙር መጽሐፍ የተጻፈው ይፈጸም ዘንድ የሆነ ነው፤ (መዝ. 68 (69)÷9፤ ዮሐ. 2÷17)። ምድራዊው መቅደስ በሰማያዊው መቅደስ እስኪተካ ድረስ በጥላነት ያገለገለ የእግዚአብሔር ቤት መሆኑንም ማንም ሊያስተባብል አይችልም፤ መቅደሱ ገና በአገልግሎት ላይ እያለ ሰዎች የጸሎት ቤትነቱን ከቁብ ሳይቈጥሩት፥ መገበያያና መለዋወጫ፥ እንዲሁም የወንበዴዎች ዋሻ ስላደረጉት፥ ጌታ ጅራፍ አበጅቶ እንዲህ ያደረጉትን ክፍሎች ከመቅደስ በማባረርና በማስወጣት፥ ሸቀጣቸውንም በመገለባበጥ ለአባቱ ቤት የነበረውን ቅንአት አሳይቷል። በቃ ይህ ሊያሳይ የሚችለው ይህን ብቻ ነው።

እነርሱ ለገዛ ጥቅማቸው ብቻ ሲሉ የሚፈልጉትን ትርጉም እናገኝበታለን ብለው ቃሉን ቢሰነጣጥቁትም፥ እንኳ ፈጽሞ የማያስኬድ ነው:: ለዚህም ከላይ ያየነው ሥርዐተ ቍርባንን በግለሰብ ቤት ውስጥ ማድረጉ አመልካች ነው::

ሐዋርያትንም የተመለከትን እንደ ሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ፥ ካረገና የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ካፈሰሰላቸው በኋላም ባለው ጊዜ፥ በመቅደስ የመገኘታቸው ዋናው ምክንያት ሥርዐተ ኦሪትን ለመፈጸምና ከዚያ ስፍራ ውጪ መጸለይ ስለ ተከለከለ፥ ወይም ደግሞ ቤተ መቅደሱ በዐዲስ ኪዳን ዘመን የሚኖረውን ቀጣይ አገልግሎት፥ መጪው ክርስቲያን ትውልድ እንዳይዘነጋው ለማሳወቅ አልነበረም:: ምክንያቱም ሐዋርያት ይህን ዐደራ ከጌታ አልተቀበሉም::

ጌታ ሕግን ከመፈጸም አንጻር በሕግ ውስጥ ያለፈ ቢሆንም፥ በቤተ መቅደስ ይገኝ የነበረበት ዋናው ዐላማ ግን፥ ወገኖቹ አይሁድ በዚያ ስለሚሰበሰቡ እነርሱን ለማስተማርና የእግዚአብሔር መንግሥት በልጅነት ልትሰጥ መቅረቧን ለማወጅ ነበር፤ (ሉቃ. 21÷37)::

ሐዋርያትም በዚያ የመገኘታቸው ምክንያት ይኸው ነበር:: «ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ፥ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ማስተማርና መስበክን አይተውም ነበር::» (የሐዋ. ሥራ 5÷42)::

ሐዋርያት እስከ ጊዜው ድረስ፥ ወደ መቅደስ ይውጡ እንጂ መውጣታቸው እስከ መጨረሻው ቀጣይነት አልነበረውም:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተከታዮቹ ላይ ከመቅደስና ከምኵራብ የመሰደድ ዕጣ ፈንታ እንደሚገጥማቸው አስቀድሞ በተነበየው መሠረት፥ ሰዓቱ ሲደርስ መገረፍና መታሰር፥ ብዙ ዛቻና ማስፈራራት፥ እስከ ሞት የደረሰ ብዙ ቅጣትና እንግልት ደርሶባቸው፥ መቅደሱንና ምኩራቡን ጥለው ለመሰደድ ተገድደዋል:: ለዚህ መላውን የሐዋርያትን ሥራ መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማንበቡ ብቻ በቂ ነው:: ለማስረጃ ያህል ግን እነዚህን ጥቅሶች ተመልከት፤ (የሐዋ. ሥራ 4÷1-3፤ 21፤ 5÷17-18፤ 40፤ 6÷11-14፤ 7÷57)::

ለወንጌል አገልግሎት በመቅደስ መገኘታቸው በአንድ ወገን ይነገር እንጂ፥ ሐዋርያትና በእነርሱ ስብከት በክርስቶስ ኢየሱስ አዳኝነት እያመኑ ወደ ኅብረታቸው ይቀላቀሉ የነበሩት ክርስቲያኖች፥ በሌላ ወገን ከመቅደስ ውጪ የግለሰቦችን ቤት የጸሎት ቤት አድርገው በመሰባሰብ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር፤ (የሐዋ. ሥራ 2÷46፤ 4÷23):: ይህም ስሟን ሕንጻ ሳይቀማው በፊት፥ ክርስቶስ በገዛ ደሙ የዋጃቸውና ለርስቱ የመረጣቸው የምእመናን አንድነት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ከመጀመሪያው ጀምሮ ከመቅደስ በተለየ ሁኔታ የተቋቋመች መሆኑን ያስረዳል::

መቼም ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ሲነገር በቶሎ ወደ አእምሮአችን የሚመጣው ሕንጻው ነው:: ይህም በአንድነት ላሉ ምእመናን የተሰጠውን ስያሜ፥ ሕንጻው በኋላ መጥቶ ምን ያህል የራሱ ገንዘብ እንዳደረገው ያሳያል:: ሕንጻው በተለምዶ ቢጠራበትም ቤተ ክርስቲያን ምእመናኑ ራሳቸው መሆናቸው የታወቀ ጉዳይ ነው:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እንደ



ደረሱት በሚነገረው ሰላምታ ላይም «ቤተ ክርስቲያን ብሂል ነፍስ ክርስቲያን ብሂል» «ቤተ ክርስቲያን ማለት የክርስቲያን ሰውነት ማለት ነው» የሚል እናነባለን::

አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህም (ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ) በበኩላቸው «ትምህርተ አበ ነፍስ» በተሰኘው መጽሐፋቸው «ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን ስያሜ ለሕንጻውም በማጋራት ጭምር ጽፈዋል::

«ቤተ ክርስቲያን ስንልም በልማድ ወይም በማደሪያው የተጠራ ሆኖ፥ ግንቡን ቤተ ክርስቲያን እንላለን እንጂ ግንቡ ብቻ አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን የሚባለው የካህናቱና የሕዝቡ አንድነት፥ እንደ አንድ ልብ መካሪ፥ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው አንድ እምነት፥ አንድ ሥርዐትና አስተያየት ያላቸው በክርስቶስ አምነው ክርስቲያን የተባሉ ሁሉ ናቸው:: ይህንም ከዚህ የሚከተለው የክርስቶስ ንግግርና ሌላውም አገላለጽ ያስረዳናል:: "እርሳቸውንም ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት ከአረማዊና ካጣሪ ቍጠረው" (ማቴ. 18÷17፤ ሮሜ 16÷20፤ የሐዋ. ሥራ 2÷16፤ 11÷22-26)» (ትምህርተ አበ ነፍስ ገጽ 24)::

ቤተ ክርስቲያን የምእመናኑ ስብስብ እንጂ ሕንጻ አለመሆኑንና፥ እንዲያው በተለምዶ ሕንጻውም ቤተ ክርስቲያን ተብሎ መጠራቱን ተመልክተናል::

ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተችበት ዘመን አካባቢ ያለውን ሁኔታ ካየን ግን፥ የምእመናን ስብስብ ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን የተወሰነ ቦታና ሕንጻ የግድ ባለማስፈለጉ፥ ከላይ እንዳየነው በግለሰቦች ቤት እንዲሁም ለእርሷ አመቺ ሆኖ በተገኘው ስፍራ፥ በባሕርና በወንዝ ዳር ሁሉ ሳይቀር ተሰብስባ እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ታመልክ ነበር፤ (የሐዋ. ሥራ 12÷5፤ 12፤ ሮሜ 16÷5፤ 1ቆሮ. 16÷19፤ የሐዋ. ሥራ 16÷13-14፤ 21÷5)::

ቤተ ክርስቲያን በዚህ ሁኔታ ስትሰበሰብ መሠረታዊ ነገር ያደረገችው ቦታን፥ አገርንና ሕንጻን ሳይሆን፥ በጌታ ስም መሰብሰቧን ብቻ ነው:: ራሷ የሆነው ክርስቶስ በዚህ አገር በዚህ ከተማ፥ እንደዚህ ባለ ሕንጻ ውስጥ ሳይል፥ ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና በማለት ብቻ የሰጠውን ተስፋ ተረድታ በልቧ ተቀብላዋለችና (ማቴ. 18÷20)፥ ስለዚህ የትም መሆኗ ክርስቶስ ከእርሷ ጋር እንዳይሆን አላገደውም::

የት መጸለይ እንደሚገባ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል: -

> «የት መጸለይ እንደሚገባ (እንደምንችል) ማወቅ አለብን፤ በአንድ በኩል ዓለም ሁሉ የእግዚአብሔር ስለሆነ፥ በሁሉ ቦታ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት፥ ስሙን መቀደስ፥ ምስጋና ማቅረብ ተገቢ ነው:: በየስፍራው፥ በየቦታው ሁሉ መጸለይ

እንዲገባ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያዛል: - "እኔም እወዳለሁ፤ ወንዶች ሁሉ ይጸልዩ ዘንድ፥ በየስፍራው የተቀደሰም እጅ ወደ ላይ ይዘረጉ ዘንድ" (1ጢሞ. 2፥8)::

ጌታም በተራራ ላይ ጸልይዋል፤ በቤተ መቅደስም ጸልይዋል፤ በምድረ በዳም ጸልይዋል፤ በአትክልት ቦታም ጸልይዋል፤ በመስቀል ላይ ሰላም እንዲሆን ጸልይዋል፤ እንዲሁም በተለያዩም ቦታዎች ጸልይዋል:: ዳንኤል በአንበሳ ጉድጓድ፥ ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሳለ፥ ጳውሎስና ሲላስ በእስር ቤት ሳሉ ጸልየዋል:: ሌሎችም ደጋግ ሰዎች በተለያዩ ቦታዎች ጸልየዋል፤ ምድር ሙላቷም የእግዚአብሔር ናትና፤ ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ (መዝ. 23 (24)፥1):: በየትም ቦታ ሁነን እግዚአብሔርን እንድናነጋግረው፥ ስሙን እንድንቀድሰው ምስጋናም እንድናቀርብለት አምላክ ይፈቅዳልና፤ (የሐዋ. ሥራ 17፥24)::

ክርስቶስም ሲያስተምር ሳምራዊቲቱን ሴት በየትም ቦታ ሁኖ መጸለይ፥ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ እንደሚገባ ነግሯታል፤ (ዮሐ. 4፥23):: የሚፈለገው ነገር ቦታ ሳይሆን የሰውዬው ንጽሕና፥ ቅን ሰብእና፥ ትሑት ኅሊና ነው::» (ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ ገጽ 195)::

እኚሁ አባት በየትም ስፍራ የመጸለያችን ጉዳይ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፥ በሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለይም የማኅበር ጸሎት መደረግ እንዳለበት በማከል ጽፈዋል::

ከቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ታሪክ ለመረዳት እንደሚቻለው፥ ቤተ ክርስቲያን ፍጹም የሚሆን ሰውን በእግዚአብሔር ቃል እየገሠጸችና በጥበብ እያስተማረች ለክርስቶስ የማቅረብ ሥራዋን ትታ፥ ፊቷን ወደ ሕንጻ ግንባታ የመለሰችው፥ ብዙ የስደትና የመከራ ዘመናትን አሳልፋና እየተስፋፋች መጥታ አብዛኛውን የዓለም ክፍል በሸፈነችበት፥ በአንጻሩ ደግሞ መንፈሳዊ ተልእኮዋን መዘንጋት በጀመረችበት ወቅት ነው::

ምናልባትም እዚህ ላይ የምእመናን ቊጥር መጨመርም ሕንጻ ለመገንባት እንደ አንድ ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ ይችላል:: እርግጥ ዛሬም እንደምናየው የምእመናን ቁጥር ከመበራከቱ የተነሣ፥ እንደ መጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ምእመናን በግለሰቦች ቤት ይሰብሰቡ አይባልም:: እግዚአብሔርን በኅብረት የሚያመልኩበትና ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የሚፈጽሙበት አንድ የተወሰነ ስፍራ ያስፈልጋቸዋል::

ችግሩ ግን የስፍራው መወሰን ወይም የሕንጻው መቆም አይደለም:: ለሕንጻውና ለስፍራው የምንሰጠው የተሳሳተ ግምት ነው:: ዛሬ በተለይም በእኛ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ውስጥ የሚመለከው እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ሕንጻውም ጭምር ነው ለማለት የሚያስደፍር ሁኔታ ይፈጸማል:: በአምላክ እንዲሁም በቅዱሳን መላእክትና ጻድቃን ሰማዕታት ስም የታነጸውን ሕንጻ ባየነው ቊጥር፥ ሕንጻው፥ ስሙ የተጠራበትን አምላክ ወይም ፍጡር መልአክና ሰው እስኪመስለን ድረስ ዐሳባችን ተበላሽቷል::



በመሆኑም ሕንጻው ሕይወት እንዳለው ፍጡር ተቈጥሮ የተለያዩ ሙገሳዎችና ወደ እግዚአብሔር እንዲለምንልን የአማልደን ጥያቄ በመጽሐፈ ሰዓታት ቀርቦለታል::

> «ሰአሊ ለነ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊት ዐውድ፥ መዝገበ ስርናይ እንበለ ክርዳድ፥ ምስአል አንቲ ወምስጋድ ምጥባሐ ሥጋሁ ለወልድ::»
>
> ትርጓሜ: - «የወልድ የሥጋው መቈረሻ፥ መለመኛና መስገጃ፥ ክርዳድ ያልተቀላቀለበት የንጹሕ ስንዴ መዝገብ የሆንሽ መንፈሳዊት አደባባይ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሆይ! ለምኝልን፤ አማልጅን::»

እኛ ግን ከእግዚአብሔር ቃል እንዳነበብነው፥ ሕንጻ በእግዚአብሔር እንዲቀደስና እንዲባረክ ሲለመንለት እንጂ እርሱ ሲለምን አላየንም፤ አልሰማንም፤ (1ነገ. 8፥29፤ 2ዜና. 6፥20፤ 1ነገ. 9፥3፤ 2ዜና. 7፥12፤ 16)::

ከዚሁ ጋር አብሮ የእግዚአብሔርን መንፈስነት ባለመረዳት ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት፥ የመጸለያ /አቅጣጫ ተለይቶ እንዲቀመጥ ተደርጓል፤ ይኸውም የምሥራቅ አቅጣጫ ነው::

የምሥራቅ አቅጣጫ በተለይም በብሉይ ኪዳን ዘመን ብዙ ተግባራት የተከናወኑበትና የተገለጹበት አቅጣጫ ነው:: ዋናው የቤተ መቅደስ (የማደሪያው ድንኳን) በር በስተ ምሥራቅ አቅጣጫ ነበር:: በዚሁ አቅጣጫ ሰፍረው መቅደሱን ለእስራኤል ልጆች እንዲጠብቁ ለሙሴና ለአሮን፥ ለልጆቹም ከተሰጠው መመሪያ እንረዳለን (ዘኍ.3፥38)፤ ስለዚህ የመቅደሱ አቀማመጥ በስተ ምዕራብ በኩል ነበር ማለት ነው::

ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ያለው መቅደስ አቀማመጡ፥ ከአሪቱ መቅደስ በተቃራኒው አቅጣጫ በስተ ምሥራቅ በኩል ነው:: የአቅጣጫው መለያየት እንደ ልዩነት ቢታይም፥ አንድን አቅጣጫ የመለየቱ ሁኔታ በቀጥታ ከኦሪቱ የመቅደስ አሠራር ትውፊት የተወሰደ ለመሆኑ አንድና ሁለት የለውም::

በመሠረቱ ወደ ምሥራቅ ዞሮ መጸለይ በዐዲስ ኪዳን የሚያስከትለው ችግር የለም:: እግዚአብሔር የሚገኘው በስተ ምሥራቅ በኩል ብቻ ስለሆነ ወደ ሌላ አቅጣጫ ዞሮ መጸለይ ተገቢነት የለውም ወደሚል የተሳሳተ እምነት እንዳያመጣብን ግን ያሠጋል:: ወይም ደግሞ ነቢዩ ሕዝቅኤል ባየው ራእይ ውስጥ ጀርባቸውን ለእግዚአብሔር መቅደስ ሰጥተው ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አዙረው አምልኮተ ፀሓይን ይፈጽሙ እንደነበሩት ሃያ አምስት የሚያህሉ ሰዎች አምልኮ እንዳንሸጋገር መጠንቀቅ ያሻል፤ (ሕዝ. 8፥16-17)::

አቅጣጫን ለአምልኮ የመለየቱ ሁኔታ ከቀድሞ ጀምሮ እግዚአብሔር በእውነትና በመንፈስ እንደሚመለክ በተረዱትና

ባልተረዱት ወገኖች መካከል መነቃቀፍንና መተቻቸትን ያስከተለ ጉዳይ ሆኖ ቈይቷል፤ አሁንም ድረስ አለ።

ከመጽሐፈ መነኰሳት አንዱ በሆነው በአረጋዊ መንፈሳዊ መጽሐፍ ውስጥ እንደተጻፈው፥ ከመነኰሳት አንዱ ፊቱን ወደ ምሥራቅ ሳያዞር ሲጸልይ፥ ሌላው መነኩሴ አይቶ ምነው ወንድሜ ሆይ! የፀሐይ መውጫ እንጂ በምሥራቅ ነው፤ ፊትህን ወደ ሌላ አዙረህ ለምን ትጸልያለህ? አለው። እንዲህ የተባለውም ምላሽ ሲሰጥ «ለፀሐይከሰ ኢየአምሮ፤ ሊተሰ ፀሐይየ ኢየሱስ ክርስቶስ» ማለትም እኔ ያንተን ፀሐይ አላውቃትም፤ የኔ ፀሐይ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና በሁሉ ስፍራ ይገኛል ብሎ መልሶለታል። (ጕሐ ጽባሕ ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ገጽ 52)።

ዛሬም እግዚአብሔር ከአንድ አቅጣጫ ውጪ የሚገኝ ለማይመስላቸው አቅጣጫ አምላኪዎች ይኸው ተደግሞ ሊነገራቸው ይገባል።

አምልኮተ እግዚአብሔር በዐዲስ ኪዳን ከአቅጣጫ ጋር ግንኙነት የሌለው መሆኑን የተረዱት አባቶች ጽፈው ያለፉትን እውነት፥ በቃሉ ሽምድዶ የተጫነውን በድጋምና በዜማ ከሚያራግፍ በቀር አስተውሎ የሚሰማቸው ባያገኙም ብዙ ተናግረዋል።

አባ ስብሐት ለአብ የተባሉትና በ17ኛው ምእት ዓመት በጎንደር ተነሥተው የነበሩት የወንጌል አርበኛ፥ በዘመኑ የነበረውን ንጉሥ የኢያሱን የአምልኮ ሁኔታ፥ በዘመነ ብሉይ ከነበሩት ከአብርሃምና ከዳንኤል የተለየ መሆኑን ለመግለጽ፥ በድርሰታቸው ውስጥ የገለጹት ለዚህ ማስረጃ ይሆነናል።

> «ማያተ ኢያሱ ሥላሴ ዘትውኅዙ እምኅሊናሁ፤ እስመ በአፍኣሁ አንትሙ፤ ወአንትሙ በውሳጤሁ፤ ኢነጸረ ኀበ ኀይመት ከመ አብርሃም አቡሁ፤ ወመስኮተ ዳንኤል ነቢይ እፈቀደ ያርኁ።»
>
> ትርጓሜ: - «ሥላሴ! ከኅሊናው የምትመነጩ የኢያሱ ፈሳሽ ውሆች ናችሁ፤ በውስጡም በውጪውም እናንተ አላችሁና፥ እንደ አባቱ እንደ አብርሃም ወደ ድንኳን አልተመለከተም፤ እንደ ነቢዩ ዳንኤልም መስኮቱን ከፍቶ ወደ ኢየሩሳሌም ይመለከት ዘንድ አልፈቀደም።» (መልክዐ ሥላሴ ለሕፅንክሙ)።

ከቤተ መቅደስ ሌላም በምድራችን ሠልጥኖ ያለውና፥ ሕዝባችንን ጽድቅ ፍለጋ ከቦታ ቦታ፥ ከአገር አገር የሚያንከራትተው፥ በምድራችን የተተከሉ የሌሎቹ ኢየሩሳሌሞች ጉዳይ ነው።

በኦሪት እንዳየነው ሰው ሁሉ እግዚአብሔርን ለማግኘት ወደ ተመረጠችው ቅድስት አገር ወደ ኢየሩሳሌም ይወጣ ዘንድ የግድ ነበር። ይህንኑ የጥላውን ዘመን አሠራር በቀጥታ በመጠቀም ዛሬ በምድራችን በኢትዮጵያ ከኢየሩሳሌም ጋር ተመሳሳይነት አላቸው የሚባሉና ኢየሩሳሌምን እንደሚተኩ ጭምር የሚነገርላቸው መካናት (ቦታዎች) አሉ። በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ከሄድን መካናቱ በታሪካዊነታቸው የቱሪስት መስሕብ ሆነው ሊጐበኙ፥ በአገር ቅርስነታቸው ሊጠበቁ ከሚገባቸው በቀር፥



ለጽድቅም ሆነ ለሌላ መንፈሳዊ በረከት ምንም አስተዋጽኦ የላቸውም። እንኳንስ እነዚህ የምድራችን ገዳማት ይቅሩና፥ ዋናዋ ኢየሩሳሌምም ዛሬ ከዚህ ውጪ ሌላ የምታስገኘው ጥቅም የላትም።

ስለዚህ ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ እንደተሰበከላቸው ከአገር አገር በመንገዝ፥ ከቦታ ቦታ በመዟዟር፥ ጽድቅና ሌሎች መንፈሳዊ በረከቶችን እናጭዳለን ብለው የሚያስቡና፥ ለቦታዎቹ በተደነገገላቸው የበዓልና የመሳለሚያ ጊዜ፥ ወደ እነርሱ የሚጐርፉት ወገኖች ባለ ማወቅ ቱሪስት መሆናቸውን ሊያጤኑት ይገባል።

መቼም በዚህ አመለካከት ውስጥ ያሉት ወገኖቻችን ከጥላው ወደ አካሉ ዘወር እንዳላሉ ግልጽ ነው። እነርሱ እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አገላለጽ የጨዋይቱ ሳይሆን የባሪያይቱ ልጆች ናቸው። ባሪያዪቱ ምሳሌነቷ በዓራ ገረድ በአጋር የተገለጸ፥ በዐረብ ምድር ያለችው ደብረ ሲና ወይም ደግሞ አሁን ያለችው ኢየሩሳሌም ስትሆን፥ እርስዋም ልጆችን ለባርነት የምትወልድና አሁንም ከልጆቿ ጋር በባርነት ያለች ናት። ጨዋይቱና በሣራ የተመሰለችው ላይኛይቱ ኢየሩሳሌም ግን በክርስቶስ ሞት ነጻ ለወጡትና ለርስቱ ወራሾች እናታቸው ናት፤ (ገላ. 4፥22-31)።

የላይኛይቱ ኢየሩሳሌም ልጆች እርሷን ከመናፈቅና ወደርሷ ለመሄድ ከማሰብ በቀር፥ በባርነት ያላችውን ኢየሩሳሌምን ዐስበዋትም ተመኝተዋትም አያውቁም፤ (ፊልጵ. 3፥20፤ ዕብ. 11፥10፤ 12፥22-24፤ 13፥14፤ ራእ. 21፥1-4)።

ምድራዊቷን ኢየሩሳሌምን እናታቸው ያደረጉት ግን ሊያዩአትና ሊኖሩባት የሚመኟት እሷኑ ብቻ ነው። ሆኖም ወደ እርሷ በእግረ ሥጋ ለመሄድ ስለምትርቃቸውና ብዙ ገንዘብ ስለሚያስወጣም፥ ፈሊጠኞቹ ሌሎች ኢየሩሳሌሞቻቸውን በምድረ ኢትዮጵያ አዘጋጅተው እዚህ ገዳም የሄደ ኀጢአቱ ይሰረይለታል፥ ኢየሩሳሌም እንደ ሄደ ይቈጠርለታል፥ በጸበሉ የተጠመቀም፥ በዮርዳኖስ እንደ ተጠመቀ ይሆንለታል፥ በማለት ከእግዚአብሔር ባልተሰጠ ተስፋ የሕዝባችንን ልብ ሞልተው፥ ጽድቅንና በረከትን ፍለጋ ከአገር አገር ያንከራትቱታል፤ ጥሪቱንም ያሰጨርሱታል። እንዲህም ሆኖ ግን የጽድቅ ጥማቱ የረካለት የለም። የጽድቅ ጣሪያ ተደርጋ ወደምትቈጠረው ወደ ኢየሩሳሌም እንኳ ደርሶ የመጣው የተወራለትን ጽድቅ አግኝቶ የልቡ ስላልደረሰለትና ዛሬም ኅሊናው በኀጢአተኝነት ስለሚከሰው እንደ ገና ታች ወርዶ እንደ ኢየሩሳሌም ናቸው የተባሉትን ገዳማት ይጐበኛል። በዚህም ቢሆን የጽድቅ ጥያቄው ምላሽ አያገኝም።

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም አምኖ፥ በክርስቶስ ቤዛነት የተገኘውን ዘላለማዊ ሕይወት በእምነት የተቀበለ ሰው፥ እግዚአብሔርን በሥጋው ቤተ መቅደስነት ውስጥ እያከበረ ከሚኖር በቀር ሰዎች በፈቃዳቸው ወደከለሉት ቦታ መንከራተት ይቅርና፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ባለፈው ዘመን ታላላቅ ሥራዎችን ወዳከናወነባቸው ስፍራዎች መሄድ፥ ታሪካዊ ጕብኝት

እንጂ በሌላ አቅጣጫ መንፈሳዊ ትርፍ የማያስገኝ መሆኑን የተረዱት የመልክዐ ሥላሴ ደራሲ አሁንም የሚከተለውን ተናግረዋል: -

«ሥላሴክሙ ሥላሴ ይረስየኒ መካነ፤ ድኅረ ተዋሐድኩስ ዘሥላሴሁ ብርሃነ፥ ዮርዳኖስክሙ ዝየ እስመ ኮለንታየ ኮነ፤ ኢየኀሥሥ እምዮርዳኖስ ስማዕተክሙ ምእመነ፤ ወኢይትሜነዮ ለታቦር እስመ ታቦር አነ።»

ትርጓሜ: - «ሥላሴ! ሥላሴነታችሁ ማደሪያው ያድርገኝ፤ የሦስትነታችሁን ብርሃን ከተዋሐድኩኝ ዘንድ፥ ሁለንተናዬ እዚሁ ዮርዳኖሳችሁን ሆኗልና፤ ከዮርዳኖስ የታመነ ምስክርነታችሁን አልሻም፤ ታቦርንም እኔው ሆኛለሁና ታቦርን አልመኘውም።» (መልክዐ ሥላሴ)።

እንግዲህ በጥቅሉ ሰዎች ዐዲስ ኪዳን ላይ ቆመው፥ በኦሪቱ አምሳል የራሳችውን መቅደስ ቢያንጹ፥ የራሳቸውን ሌላ ኢየሩሳሌም ቢመሠርቱ፥ ያደረጉት ሁሉ ዘመን ያለፈበት የጥላው ነገር ከመሆኑም በላይ፥ በተሻረ ሕግ የሚከሰስ የለም እንጂ በኦሪት ሕግ መሠረት እግዚአብሔር ከመረጠው አገርና በታ ውጪ ይህን በማድረጋቸው ከተጠያቂነት አያመልጡም ነበር፤ (ከኢያ. 22፥9-34 ካለው ታሪክ ጋር ያነጻጽሩ)።



# ክፍል 10 - ካህናትና አገልግሎታቸው

## 10.1 የካህናት አገልግሎት በብሉይ ኪዳን

ሕዝበ እስራኤል እግዚአብሔር ለርስቱ የመረጣቸው ወገኖችና አገልጋዮች እንደመሆናቸው፥ ቅዱስ የሆነና ሥርዐት ያለው አምልኮ መፈጸም ይጠበቅባቸዋል።

«አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ፥ ኪዳኔንም ብትጠብቁ ምድር ሁሉ የኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ። እናንተም የካህናት መንግሥት፥ የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ።» (ዘፀ. 19፥5-6) ሲል እግዚአብሔር በቃሉ ያረጋገጠውም ይህንኑ ነው።

በዚህ ክፍል (ዘፀ. 19፥5-6)፥ አጠቃላዩ ሕዝበ እስራኤል ለካህናት መንግሥትነት እንደተመረጡ እናያለን። በተለይ ግን ግብጽን ለቅቀው በወጡባት ምሽት፥ የፋሲካ በግ ደም ቤዛ ተሰጥቶላቸው ሞተ በኩር ያለፋቸው የእስራኤል ልጆች በኩራት፥ ለእግዚአብሐር የተለዩ ነበሩ፤ (ዘፀ. 12፥12፤ 13፥1-2)።

ይሁን እንጂ እነርሱ የወርቅ ጥጃ አቁመው በማምለካቸው ምክንያት፥ እግዚአብሔር በእነርሱ ፈንታ ሌዋውያንን የእርሱ ካህናት አድርጎ ለያቸው፤ (ዘፀ. 32፥25-27፤ ዘኍ. 3፥5-13፤ 40-45)። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንግዲህ ነገደ ሌዊ ለክህነት የተለየ ወገን ሆኖ እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ ቆይቷል።

ታዲያ እዚህ ላይ አጠቃላዩ ነገደ ሌዊ ለክህነት አገልግሎት ተመረጠ ይባል እንጂ፥ በተለይም መሥዋዕት በማቅረብ በሚከናወነው የክህነት ሥራ አሮንና ልጆቹ ብቻ ተለይተዋል፤ (ዘፀ. 28፥1)። የተቀሩት ሌዋውያን ደግሞ ከዚህ ውጪ ያለውን የመቅደስ አገልግሎት በማገልገል ይተባበሩ ዘንድ ለአሮን የተሰጡ ነበሩ፤ (ዘኍ. 3፥5-10)።

ከካህናት አገልግሎቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ: - የቤተ መቅደሱን አገልግሎት በትእዛዙ መሠረት ማገልገል (ዘኍ. 16፥40፤ 18፥5)፥ የሕጉን መጽሐፍ ለሕዝቡ ማስተማር (2ዜና. 15፥3፤ ኤር. 18፥18፤ ሕዝ. 7፥26)፥ ኡሪምና ቱሚም በተባሉ ንዋያተ ቅድሳት የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅና (ዘፀ. 28፥30፤ ዕዝ. 2፥63) ሕጉ እንደሚያዝዘው ተላላፊ በሽታ ያላባቸውን መለየት ነበሩ፤ (ዘሌዋ. 13፥1-3)።

ካህናቱ በተለይም በቤተ መቅደሱ ውስጥ ይሰጡት የነበረው አገልግሎት ዕለታዊ፥ ሳምንታዊና ዓመታዊ ክፍፍሎሽ ነበረው።

በዕለታዊው የመቅደስ ውስጥ አገልግሎታቸው በነግህና በሠርክ ጊዜ (ጧትና ማታ) የሚቃጠል መሥዋዕት ይሠዋሉ (ዘፀ. 29፥38-39)፥ በቅድስት ውስጥ መብራቶችን ያበራሉ፥ ዕጣን ያጥናሉ (ዘፀ. 30፥7-8)፥

ከዚህ መደበኛ አገልግሎት ውጪም በየዕለቱ ሰው የሚያመጣውን ልዩ ልዩ መሥዋዕት በየይነቱ ያቀርባሉ።

ሳምንታዊው አገልግሎት ደግሞ 12 ኅብስተ ገጽ በየሰንበቱ በእግዚአብሔር ፊት በጥሩ ገበታ ላይ ማኖር ነው፤ (ዘሌ. 24÷5-8) ።

በዓመት አንድ ቀን በዕለተ አስተስርዮ የእስራኤል ሕዝብ በጾምና ሰውነታቸውን በማስጨነቅ ኀጢአታቸውን ሲናዘዙ÷ ሊቀ ካህናቱ በመጀመሪያ ለራሱ÷ ቀጥሎ ለካህናቱ በመጨረሻም ለሕዝቡ መሥዋዕት በማቅረብ ደሙን ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባል። ይህን ልዩ ሥርዐት መፈጸም ዓመታዊ አገልግሎት ነው፤ (ዘሌዋ. 16) ።

የብሉይ ኪዳን ካህናት አገልግሎት ከላይ እንዳየነው ዘርፈ ብዙ ቢሆንም÷ ተጠቃልሎ ሲታይ ግን በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል በመሆን በመሥዋዕትና በጸሎት ሕዝቡንና እግዚአብሔርን የማገናኘት አገልግሎት ነው።

በዚህ ክህነት የተሰጠው አገልግሎት በብዙ ሥርዐትና ጥንቃቄ የሚፈጸም አፍአዊ አገልግሎት ሲሆን÷ የአንድ ሥርዐት መዛነፍ በአገልጋዮቹ ላይ ቅጣትና ተግሣጽን ያስከትል ነበር። እንዲህም ሆኖ በዚህ አገልግሎት ዘላለማዊ ሕይወት አልተገኘም። ከእርሱ እጅግ በተሻለውና በሚበልጠው የዐዲስ ኪዳን አገልግሎት ዐይን ሲታይም÷ ይህ የቀድሞው አገልግሎት የሞትና የኵነኔ አገልግሎት ተብሏል፤ (2ቆሮ. 3÷7-9)።



## 10.2 የሊቀ ካህናትና የካህናት አገልግሎት በዐዲስ ኪዳን

ሰው ኀጢአትን ሠርቶ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን መልካም ግንኙነት ካበላሸ በኋላ÷ በአምላኩ ፊት የሚሰጠው አገልግሎት ፍጹምነት የጐደለው በመሆኑ÷ በአገልግሎቱ ከሞትና ከኵነኔ ሊድን ፈጽሞ አይችልም። ከዚህ አንጻር በፍጹም ታዛዥነቱና በብቁ አገልግሎቱ ይህን አሳዛኝ የሰው ልጆች ታሪክ ሊቀይር የሚችል እውነተኛ አገልጋይ ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ ከሰው መካከል እንዲህ ያለ ብቁ አገልጋይ ፈጽሞ አልተገኘም።

እግዚአብሔር ከፈርዖን አገዛዝ ሕዝቡን ነጻ ያወጣው እንዲያገለግለው መሆኑን÷ በአገልጋዩ በሙሴ አማካይነት ለፈርዖን ደጋግሞ ተናግሯል፤ (ዘፀ. 4÷22-23፤ 5÷1፤ 7÷16፤ 8÷1፤ 20፤ 9÷1፤ 13፤ 10÷3)። እንደተባለውም ያ ሕዝብ ነጻነቱን ከተጐናጸፈ ሰዓት ጀምሮ እግዚአብሔርን ማገልገል ቀጥሏል። አገልግሎቱ ግን ፍጹምነት ይጐድለው ስለነበር÷ ለሚበልጠው ሕዝብ የዘላለም ሕይወትን ለማስጠት ቀርቶ ምድረ ከነዓንን ለማስወረስ እንኳ አላበቃቸውም። ስለዚህ የቀደመው ያ አገልግሎት የሞትና የኵነኔ አገልግሎት ይባል ዘንድ ተገባው፤ (2ቆሮ. 3÷7-9)።

ክብር ምስጋና ይግባውና የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ÷ ፍጹምነት ለጐደለው የኦሪት ክህናት አገልግሎት ፍጹምነትን በመስጠት የተበላሸ ታሪኩን ሊያድሰውና ስለ ሰዎች ሆኖ በማገልገል የእግዚአብሔርን ልብ ሊያረካ ሰው ሆኖ መጣ። ወደዚህ ምድር ከመጣባቸው ዐላማዎች መካከል አንዱ÷ ለማገልገል እንደሆነ ራሱ በግልጽ ተናግሯል፤ (ማር. 10÷45)። ይህን ዐላማውንም ከግቡ ለማድረስ የሰዎችን የተለያየ ድካም እያገዘ÷ የመንግሥቱን ወንጌል እያስተማረ÷ አርአያውን በሚታይ ግብር እየተወና በመጨረሻም ስለ ብዙዎች ቤዛ ሆኖ በመሞት÷ አገልግሎቱን በሰውና በእግዚአብሔር ፊት ፈጽሟል፤ (ማቴ. 8÷16-17፤ 4÷17፤ ሉቃ. 4÷17-21፤ ዮሐ. 13÷4-16፤ 1ጴጥ. 2÷21-24)።

የከበረ አገልግሎቱ በምድር ላይ በዚህ ሁኔታ ሲፈጸም÷ ከቤዛነቱና ከመሥዋዕትነቱ ጋር የተያያዘውንና÷ በሊቀ ካህንነቱ በእግዚአብሔር ፊት የሚያገለግለውን ማገልገል የሚያከናውነው በሰማያዊቱ መቅደስ ውስጥ ስለሆነ÷ ወደዚያው ገብቶ በማገልገል በዚያው ይገኛል። በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የመቅደስና የእውነተኛይቱ ድንኳን አገልጋይ ነው።» ተብሏል፤ (ዕብ. 8÷8)።

በአገልግሎታችን ጒድለትና ባለመታዘዛችን ጠንቅ እግዚአብሔር ከእኛ ከሰዎች ዐጥቶ የነበረውን ጽድቅ÷ በክርስቶስ የጽድቅ አገልግሎትና መታዘዝ ስላገኘ÷ በክርስቶስ ያመነበት ሁሉ የጽድቁ ወራሽ እንዲሆን አደረገ፤ (ኢሳ. 53÷11፤ ሮሜ 5÷19፤ ዕብ. 5÷8-10)።

በዚህ ሁኔታ ክርስቶስ ፊት አውራሪ በሆነበትና በፈጸመውም የጽድቅ አገልግሎት መሠረት፥ አስቀድሞ የሞትና የኵነኔ የተሰኘው አሮጌው አገልግሎት ታሪኩ ተገልብጦ፥ ዐዲሱ የመንፈስና የጽድቅ አገልግሎት በስፍራው ተተካ። በዚህም ምክንያት የዐዲሱ ኪዳን አገልጋዮች ከእነርሱ ባልሆነ መንገድ ብቃትን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከእግዚአብሔር ስላገኙ፥ አስቀድሞ ወደ ሞትና ወደ ኵነኔ ያደርስ ከነበረው የፊደል አገልግሎት ወጥተው፥ የዘላለም ሕይወትን ወደሚያድለው የመንፈስ አገልግሎት ተሸጋግረዋል።

ይህ አገልግሎት ከቀድሞው እጅግ የበለጠና የከበረ እንደመሆኑ፥ ክብሩ ሊገለጽ የተገባው ለዚያኛው ፍጹም ተቃራኒ በሆነ አገላለጽና ሁኔታ ነው። የቀድሞው አገልግሎት የፊደል፥ የሞት፥ የኵነኔ፥ የሚሻር አገልግሎት ሲሰኝ፥ የአሁኑ ደግሞ የመንፈስ፥ የጽድቅ፥ ጸንቶ የሚኖር አገልግሎት ተሰኝቷል።

በተሻለ ክብር የሚገለጠው አገልግሎት እስኪመጣ ድረስ፥ የቀድሞው አገልግሎት በጊዜው ክብር የነበረው መሆኑ ባይካድም፥ እጅግ በሚበልጠው የዐዲስ ኪዳን አገልግሎት ክብር ምክንያት ያን የቀድሞ ክብሩን ዐጥቷል፤ (2ቆሮ. 3)።

ታዲያ የክብሩ ታላቅነት በቅዱሳት መጻሕፍት የተመሰከረለት የዐዲስ ኪዳን አገልግሎት፥ ከቀድሞ የተሻለ እንደሆነ ሁሉ በአገልግሎቱ ዐይነትና በአፈጻጸሙም ጭምር በአብዛኛው የተለየ መሆኑ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው።

ለዚህ አገልግሎት የብቃት ምንጭ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዋናውንና ስለ ኀጢአት ቤዛ ሆኖ የሚከፈለውን በቂ፥ ፍጹምና የማያዳግም መሥዋዕት አቅርቦ ስለኛ በማገልገሉ፥ እርሱ ባቀረበው መሥዋዕት ተቀድሰው የኀጢአታቸውን ስርየት የተቀበሉ ሁሉ፥ የዐዲስ ኪዳን አገልጋዮች (ካህናት) ተደርገዋል፤ (1ጴጥ. 2፥9፤ ራእ. 1፥6)።

የብሉይ ኪዳን መጋረጃ እስካሁን ድረስ በኅሊናቸው ጓዳ የተጋረደባቸው ክፍሎች ግን፥ በተራቀቀ መንገድ ሌላ የአሮን ቤት መሥርተው ከጥቂቶች በቀር አገልጋይ የሆኑ ካህናት የሉም ብለው ያስባሉ። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ጥንታዊው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት አይደግፏቸውም።

የቤተ ክርስቲያን ጸሎት የተሰኘውና በ1936 ዓም ታትሞ ዛሬም ድረስ ሥርዐተ ጸሎትን ለማካሄድ ቤተ ክርስቲያናችን የምትገለገልበት መጽሐፍ እንዲህ ይላል: -

> «ቤተ ክርስቲያን አንድ አካል አንድ መንፈስ ስለ ሆነች፥ በካህናትና በምእመናን መካከል መለያየት የለም። <u>ሁላችን የክህነትና የመንግሥት ልጆች ነን፤</u> ሁላችን አንዲት ሰማያዊት ጸጋን ቀምሰናል። ቅዱስ ጴጥሮስም እንዲህ ብሏል። "እላንት ግን የተመረጠ የመንግሥትና የክህነት ወገን ናችሁ፤ የተቀደሰች ዘር፤ ለርስት የተለየ ሕዝብ፤ ከጨለማ ወደማይነገር ወደ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን ሥራ ትገልጹ ዘንድ፤" (1ጴጥ. 2፥9)። <u>ስለዚህ በምእመናንና በካህናት መካከል ልዩነት የለም</u>። "ነገሥታትና ካህናት ያደረገን፥ ለአባቱ ለእግዚአብሔር፥ ለእርሱም ክብር ምስጋና ይሁን፤ ችሎታም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አሜን!" (ራእ. 1፥6)።» (መግቢያው ላይ ገጽ 12ን ተመልከት)።



እዚህ ላይ አገልግሎት ልዩ ልዩ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ምእመናን ሁሉ የክርስቶስ አካል በሆነችው አንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የአካል ክፍሎች እንደ መሆናቸው፥ በተጠሩበት መጠራትና በተሰጣቸው ጸጋ አንዲት አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን ያገለግላሉ። ይህም ሲባል እንደ ተሰጣቸው ጸጋ መጠን በተጠሩበት መጠራት ጸንተው ቤተ ክርስቲያንን ከመምራት ጀምሮ፥ በሰው ዐይን ትንሽ መስሎ እስከሚታየው ወይም እንደ አገልግሎት እስከማይቈጠረው የአንድ ምእመን አገልግሎት ድረስ ባለው የአገልግሎት ክፍል ውስጥ ተሰማርተው ያገለግላሉ ማለት ነው፤ (ሮሜ 12፥3-8፤ 1ቆሮ. 12፥4-27፤ ኤፌ. 4፥4-7፤ 11-14፤ 1ጴጥ. 4፥10-11)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዋናውን አገልግሎት አከናውኖ ስላጠናቀቀ በእርሱ ሥራ አገልጋዮች የተደረጉ ሁሉ፥ እርሱ እንዳቀረበው ያለ መሥዋዕት ከማቅረብ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ታላላቅ አገልግሎቶች ማገልገል አይፈለግባቸውም። ነገር ግን በእነርሱ እንዲከናወኑ በፈቃደ እግዚአብሔር የተወሰኑትን መንፈሳውያን አገልግሎቶች ያገለግላሉ። ዋናው የአገልግሎታቸው ግብ ክርስቶስ የጀመረውን የእግዚአብሔርን መንግሥት የማስፋፋት ሥራ በመሆኑ፥ ቃሉን በማዳረስ ዐዳዲስ ነፍሳት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲጨመሩ በማድረግና የተጨመሩትም ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት እስኪደርሱ ድረስ በቃሉ በማሳደግ አገልግሎት ላይ ያተኮረ ነው፤ (ማቴ. 28፥19-20፤ ኤፌ. 4፥11-14)።

የዐዲስ ኪዳን አገልጋዮችም ይተጉ የነበረው ለዚሁ አገልግሎት እንደነበር የእግዚአብሔር ቃል ይመሰክራል፤ (የሐዋ. ሥራ 6፥2-4፤ ሮሜ 15፥19-20)።

## 10.3 ጊዜ ያለፈበትና ያልታዘዘ አገልግሎት

በቤተ ክርስቲያናችን ከፊል ኦሪታዊ ሥርዐቶች ይንጸባለቃሉ ለማለት ከሚያስደፍሩን ምክንያቶች መካከል አንዱ፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ እየሰጠች ያለው የአገልግሎት ሁኔታ ነው። እርግጥ በአገልግሎቷ ውስጥ የወንጌል አገልግሎት ፈጽሞ የለም ማለት ትልቅ ስሕተት ነው። በሌላም በኩል አገልግሎቷ የኦሪት ጥገኛ አይደለም ብሎ ማስተባበል አይቻልም። ፈጥጠው የሚታዩትን ኦሪታዊ አገልግሎቶች መሸሸግ ፈጽሞ አይቻልምና።

አሰያየሙ የዐዲስ ኪዳን የማይመስል፥ እየሰጠ ያለው አገልግሎትም ሲታይ በይበልጥ ወደ ኦሪቱ ሥርዐት ያደላ የክህነት አገልግሎት በቤተ ክርስቲያናችን መኖሩ ይታወቃል።

ይህ የክህነት አገልግሎት ከሐዋርያት ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣ ብዙዎቹ ይናገራሉ። ሐዋርያት ግን ሁሉም ምእመናን ወንጌል በክርስቶስ ሿሚነት የተሾሙትን ክህነት፥ በተለይ የግል ሹመታቸው አድርገው ያዩበት ሁኔታ ፈጽሞ የለም። ጌታ ሕዝቡን በትምህርተ ወንጌል እንዲጠብቁ የሾማቸው እንደመሆናቸው ግን፥ ጳጳሳት (የሐዋ. ሥራ 20፥28)፥ ኤጲስ ቆጶሳት (1ጢሞ. 3፥1-7፤ ቲቶ 1፥7፤ ፊልጵ. 1፥1)፥ ቀሳውስት (ሽማግሌዎች) (1ጢሞ. 5፥17፤ ቲቶ 1፥5፤ ያዕ. 5፥14)፥ ዲያቆናት (1ጢሞ. 3፥8-13፤ ፊልጵ. 1፥1)፥ ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ እረኞች፥ ወንጌል ሰባኪዎችና አስተማሪዎች (1ቆሮ. 12፥28-29፤ ኤፌ. 4፥11) ሆነው በነገር ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል። ይኸው መንፈሳዊ ሹመት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ከዘመናችን ደርሷል።

በዚህ መንፈሳዊ ሹመትም ሐዋርያት ያገለገሉት የዐዲስ ኪዳንን አገልግሎት ብቻ ነው። አገልግሎታቸውም ልዩ ልዩ ሲሆን፥ በጥቅሉ ሲታይ ግን ቤተ ክርስቲያንን የሚጠቅምና ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት የሚያደርሳት ነበር። ሆኖም ከምንም በላይ ትኩረት የሰጡት በጸሎትና ቃሉን በማዳረሱ አቅጣጫ ያለውን ዋና አገልግሎት ነው፤ (የሐዋ. ሥራ 6፥2-4)።

ዛሬ በሐዋርያት እግር ተተክተናል፥ የእነርሱንም ሹመት ተሹመናል የሚሉ ሁሉ፥ በነዚሁ አገልግሎቶች በመጠመድ እውነተኛነታቸውን ሊያስመሰክሩ ይገባል። በቤተ ክርስቲያናችን የሚታየውን ሁኔታ ካየን ግን፥ በአብዛኛው የዚህ ተቃራኒ ነው። በሐዋርያት እግር ተተክተናል ማለት ያስፈለገው፥ ታማኝነትን አግኝቶ የግል ጥቅምን ለማሳደድ በሽፋንነት ስለሚያገለግል ካልሆነ በቀር፥ ትክክለኛውን ሐዋርያዊ አገልግሎት ለማገልገል ነው ለማለት ያስቸግራል።

በቤተ ክርስቲያናችን ከኦሪቱ አገልግሎት ጋር የተቈራኘ አገልግሎት መስጠታቸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ፥ ሐዋርያት ያገለገሉትን ዋና አገልግሎት የሚያገለግሉ አንዳንድ ታማኝ አገልጋዮች መኖራቸው እውነት ነው። የሚበዙቱ ግን ስሙን ብቻ ያዙ እንጂ የሚያገለግሉት ጊዜ ያለፈበትን የኦሪቱን አገልግሎት የሚመስል፥ ወይም ደግሞ ከእግዚአብሔር



ያልታዘዘውንና በራሳቸው ፈቃድ ያቋቋሙትን ሌላ የጥቅም አገልግሎት ነው እንጂ፥ የዐዲስ ኪዳንን አገልግሎት ነው ለማለት አያስደፍርም።

እኛ ብቻ ካህናት ከሚሉት ወገኖች አብዛኞቹ አገልግሎታቸው ለራስ እንጂ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም የቆመ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ወይም ምእመናን ተጠቀሙ የሚባለው፥ ድኅነት የሚያሰጠውን ወንጌል ተምረው ፈቃደ እግዚአብሔርን መፈጸም ሲችሉና፥ በሚሰጣቸው አገልግሎት ዕረፍተ ነፍስን ሲያገኙ ብቻ ነው። በዚህ በኩል የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት እንዳይቻል ግን አገልጋዮቹ ራሳቸው ብዙ ጕድለት አለባቸው።

ፍትሐ ነገሥት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በተለይም ቀሳውስት በአገልግሎት ከመሰማራታቸው በፊት፥ ሊያሟሉ ስለሚገባቸው ተገቢ መስፈርት እንዲህ ሲል ይደነግጋል: -

> «ወኢይኩን አሐደ ቀሲሰ፥ ዘኢየአምር ነገረ መጻሕፍት አምላካውያት ሠናያት፤ ፈድፋደሰ አርባዕተ ወንጌለ።»

> ትርጓሜ: - «በጎ የሆኑ የአምላካውያት መጻሕፍትን ምስጢር ጠንቅቆ ያልተማረ፥ ይልቁንም አርባዕቱ ወንጌልን ያልተረዳ ማንኛውም በቅስና የሚያገለግል አይሁን።» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ሳድስ)።

ቀኖናው ምንም እንከን የማይወጣለት ነው፤ ይሁን እንጂ ዛሬ በወረቀት ላይ የሰፈረ ሕግ ብቻ ከመሆን አላለፈም።

ችግሩ ከግራኝ መሐመድ ወረራ ወዲህ እየተከሠተ ያለ ችግር መሆኑን ብዙዎች ይናገራሉ። ከዚያ ወዲህ ባለው ዘመን ቀድሞ በቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት እየተመዘኑና መንፈሳዊነታቸው እየተመሰከረላቸው ወደ አገልግሎት የሚሰማሩ ቀሳውስት፥ ቤተ ክርስቲያን እንዳይዘጋ በሚል ውዳሴ ማርያምና የመሳሰሉትን የቃል ድግምቶች በሚያነበንቡና ቅዳሴ በሚቀድሱ ቀሳውስት እየተተኩ መጡ።

የአገልጋዮቹ ዋናው ችግር የእግዚአብሔርን ቃል ጠንቅቆ አለማወቅና ለማስተማር አለመብቃት፥ በቃሉም የተለወጠ ሕይወት አለማሳየት መሆኑ ሁሉም የሚስማማበት ነጥብ ነው።

በእግዚአብሔር ቃል ምትክ በልባቸው የሞላውና በአፋቸውም ተርፎ የሚነገረው፥ የአዋልድ መጻሕፍት የፈጠራ ድርሰት ነው። ከዚህ አንጻር በእነርሱ ዘንድ እንደ አገልግሎት የሚቈጠረው በአዋልዱ መጻሕፍት የሚስተጋቡትን ተግባራት መፈጸምና ማስፈጸም ነው።

እንደዚህ ያለውን አገልግሎት የሚያገለግሉ ክፍሎች በአገልግሎቱ ግላዊ ጥቅም ስለሚያገኙ፥ ዐውቀውም ይሁን ባለማወቅ አገልግሎታቸው በትክክለኛው የዐዲስ ኪዳን አገልግሎት እንዲተካ አይፈልጉም። በእነርሱ ዘንድ ይህ ተለወጠ ማለት ሃይማኖት ፈረሰ የማለት ያህል ይቈጠራል።

ኀላፊነት ተሰምቷቸውና የብዙ ሰዎች ደም ከእጄ ይፈለጋል ብለው በእውነት ከሚያገለግሉት ይልቅ÷ ጸበል በመርጨት÷ በመጐብኘት÷ እንዲሁም በጸሎት ርዝማኔ እያመካኙ አብያተ መበለታትን የሚበዘብዙ÷ የጥምጥም÷ የጠም ቆሎ... ወዘተ በሚሉ ደንቦቻቸው መሠረት ምእመናንን የሚያስቸግሩ እጅግ ብዙ ናቸው:: የእግዚአብሔርን ቃል አስተምረው እንዲህ ቢያደርጉ ባልከፋ ነበር፤ ነገሩ ከዚህ ውጪ ሆነ እንጂ::

በኦሪቱ ሥርዐት አምሳል ሰዎችን ንስሓ ማስገባት ሌላው የሚታየው ኦሪታዊ አገልግሎት ነው::

ኀጢአት ምንጊዜም ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑ ይታወቃል:: ለኀጢአት ሁሉ በቂ የሆነውን ዋጋ ደግሞ ክርስቶስ በመክፈሉ÷ ምንም እንኳ በሥጋ የዘራነውን በሥጋ ብናጭድም (ገላ. 6÷7-8፤ ኢዮ. 4÷8)÷ ስለ ነፍሳችን ስርየት ከኛ የሚጠበቅ ሌላ መሥዋዕት ወይም ቀኖና ግን የለም:: የኀጢአታችንን ስርየት ለመቀበል ክርስቶስ ካቀረበው መሥዋዕት በቀር ሌላ አያስፈልገንምና፤ (ዕብ. 10÷10-18)::

በቤተ ክርስቲያናችን ቀሳውስት ለነሳሒው (ንስሓ ለሚገባው) ምእመን ቀኖናን በመስጠት እያከናወኑት ያለው ተግባር÷ ራስን በክርስቶስ ስፍራ ከማስቀመጥ÷ የእርሱንም መሥዋዕትነት በቂ እንዳልሆነ ከመቍጠር ተለይቶ ሊታይ እንዴት ይችላል?

ቀሳውስቱ የነሳሒውን ኀጢአት ሰሚ በመሆን የክርስቶስን ስፍራ ሲይዙ÷ እንደ ኀጢአቱ ክብደትና ቅለት የኀጢአቱ ዕዳ በቀኖና እንዲወራረድለት የተለያዩ ትእዛዛትን በማዘዛቸው ደግሞ÷ የክርስቶስ መሥዋዕትነት በቂ እንዳልሆነ ወይም ብቻውን እንደማይጠቅም ነገር ተቈጥሯል:: ይህም የኦሪቱ ካህን በኀጢአተኛው እስራኤላዊ ላይ እንደ ግምጋሚው መጠን ስለ ኀጢአቱ ዕዳ በሚያስከፍለው አምሳል÷ የተሠራ ሥርዐት መሆኑ ነው፤ (ዘሌ. 5÷15፤ 18፤ 6÷6)::

ቀኖናው በተወሰነ መልኩ ለአንዳንድ ቀሳውስት በገቢ ምንጭነት እንደሚያገለግል ይታወቃል:: ለምሳሌ: - ከቀኖናዎቹ መካከል የምጽዋትን ትእዛዝ ካየን÷ ምጽዋቱ በቄስ እጅ ካልተመጸወተ ቅድመ እግዚአብሔር አይደርስም በሚል ዘዴ ራሳቸውን ለመጥቀም ምጽዋቱን የሚቀበሉ አንዳንዶች እንዳሉ ይነገራል:: በዚህ ተግባር የተሰማሩ ቀሳውስት ዛሬ ብቻ ሳይሆን ከቀድሞ ጀምሮ እንደነበሩና አድራጎታቸው ሁሉ የተሳሳተ መሆኑን÷ ተችተው የተከበሩ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ/ሥላሴ «ጐሐ ጽባሕ» በተሰኘው መጽሐፋቸው መጪው ትውልድ እንዲያስተውለው በሚል የሚከተለውን ጽፈዋል: -

> «ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ምጽዋታቸውን ... በእግዚአብሔር ፊት ምስክር እንዲሆን ቄስ ሳያይና ሳይሰማ መመጽወት ለማንም አይገባውም እያሉ ስላስተማሯቸው÷ በስውር በመጸወቱት ገንዘብ እንጸድቅበታለን ለማለት ይጠራጠራሉ::... ጌታ ግን የምጽዋትን ነገር እንኳን ለቄስ ማሳየትና ቀኝህ የሚሠራውን ግራህ አይወቅብህ ብሎ ተናግሯል::



> ይህን ለመጻፍ ያደረሰን ምጽዋት በቄስ እጅ ካልሆነ አይረባም፤ አይጠቅምም፤ እያሉ የሚያስተምሩ ሰዎች የራሳቸውን ጥቅም ፈላጊዎች መሆናቸውን ወደፊት ለሚነሣው ትውልድ ለማስረዳት ብለን ነው::» (ገጽ 53-54፤ 56)::

ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች በራሱ እጅ ለመመጽወት ያልተመቸው ሰው÷ ታማኝ በሆነ በሌላ ሰው ወይም በቄሱ እጅ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ሊያስመጸውት የሚችል መሆኑንም አክለው ጽፈዋል፤ (ገጽ 56)::

ውድ አንባቢ ሆይ! እዚህ ላይ ታዲያ ሁሉም ቀሳውስት እንዲህ ያለ መጥፎ ተግባር ይፈጽማሉ ማለት እንዳልሆነ በቅንነት ልትረዳ ይገባል:: ከዚህ ቤተ ክርስቲያንንና ደጋጎቹን ቀሳውስት ጭምር ከሚያስነቅፍ ወራዳ ግብር የራቁና የታመኑ ቀሳውስትም በቤተ ክርስቲያናችን አሉና::

እንግዲህ ቀኖናን አስመልክቶ ለምእመናን የሚሰበክላቸው የኀጢአት ዕዳ በቀኖና የሚወራረድ ተደርጎ ስለሆነ÷ የታዘዙትን ቀኖና ካልፈጸሙ በቀር ስርየት የሚያገኙ አይመስላቸውም::

ሌላው በዐዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንዲከናወን ያልታዘዘውና ለግል ጥቅም ሲባል ብቻ የቆመው አገልግሎት የፍትሐትና የተዝካር አገልግሎት ነው::

ምእመናን በየዋህነትና በተነገራቸው መሠረት÷ ከላይ በምሳሌነት ለተጠቀሱትና ለነፍሳቸው ድኅነት ለማይጠቅሟቸው አገልግሎቶች÷ በሕይወት እያሉ ገንዘባቸውን÷ ጕልበታቸውንና ጊዜያቸውን ሁሉ በከንቱ ማባከናቸው ሳያንስ÷ ከሞቱ በኋላም ቀሪ ጥሪታቸው ለቆመው ወገን መደጎሚያ እንዳይሆን በጸሎተ ፍትሐትና በተዝካር ስም ይበዘበዛል::

ይህ አገልግሎት ለግል ጥቅምና ለሆድ መሙያ ሲባል የተፈጠረ መላ እንጂ÷ ሰው ከሞተ በኋላ በተለያዩ መንገዶች ይግባኝ ተጠይቆለት የሞቱ ፍርድ ወደ ሕይወት ይለወጥለት ዘንድ አይቻልም:: በዚያውም ላይ ጸሎተ ፍትሐት የሚደርስላቸውም ሆኑ ተዝካር የሚደገስላቸው ገንዘብ ያላቸው ብቻ በመሆናቸው÷ ድኾች በገንዘብ ዕጦት ሳቢያ አገልግሎቱ አይፈጸምላቸውም:: ይህም አገልግሎቱ ለግል ጥቅም እንጂ ለምእመናን አገልግሎት እንዳልቆመ ያሳየናል:: ምክንያቱም በዚህ አሠራር መሠረት ገንዘብ ያላቸው ሊጸድቁ÷ የሌላቸው ደግሞ ሊኰነኑ ነው፤ የዘላለም ሕይወትም ለሀብታሞች ብቻ በገንዘብ ሊሸጥ ነው፤ እግዚአብሔርም አድሎኣዊ አምላክ ሊባል ነው::

አእምሮ ላለው ሰው የዚህ አገልግሎት ከንቱነት ግልጽ ነው:: አብዛኛው ሰው ይህን የተረዳ ቢሆንም ከሰው ላለመለየትና ይሉኝታን ከመፍራት የተነሣ አገልግሎቱን እንደሚፈጽምም ይታወቃል::

የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስም ለሰው ሁሉ አንድ ጊዜ መሞት÷ ከዚያም በኋላ ደግሞ ፍርድ ብቻ የተመደበበት መሆኑን ይናገራል:: ከዚህ ውጪ ከሞት በኋላ በሲኦል ሆኖ ንስሓ

መግባትም ሆነ ሌላ የመዳን ዕድል የለምና፥ ሁሉ ነገር ከሞት በፊት መጠናቀቅ ይኖርበታል፤ (2ነገ. 20፥1፤ መዝ. 6፥5፤ 29(30)፥9፤ 88 (89)፥10-11፤ መክ. 9፥10፤ ኢሳ. 38፥1፤ 18-19)።

ቤተ ክርስቲያናችን በዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ታምናለች። ሰው ከመሞቱ አስቀድሞ በንስሐ ሕይወቱን ማስተካከል ያለበት መሆኑንም አበክራ ከመናገር ወደ ኋላ ያለችበት ጊዜ የለም።

ይህ አቋሟ የተንጸባረቀበት አንድ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጽሐፍ ይገኛል። ጽሑፉ ክርስቶስ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል የወረደበትን ምክንያት ለማስረዳት የቀረበ ነው። በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆኖ ስለ ሙታን የሚደረገውን ተዝካርና ፍትሐት ፊት ለፊት ለመቃወም የማይቻል በመሆኑ፥ ጸሐፊው በሌላ ርእስ ጉዳይ ተነሥተው ሰው ከሞተ በኋላ ለማመንም ሆነ ንስሐ ለመግባት ዕድል የሌለው መሆኑን እግረ መንገዳቸውን ለማስገንዘብ ያሰቡ ይመስላል። ጽሑፉ እንዲህ ይላል: -

> «የክርስቶስ ሥጋው በመቃብር ሳለ፥ ቅድስት ነፍሱ ወደ ሲኦል ወርዳለች። ኤፌ 4፥8-9 ወደ ሲኦል መውረዱ ሥቃይ ለመቀበል አይደለም። <u>በሲኦል ለነበሩ ነፍሳት ወንጌልን ለመስበክና ለማዳንም አልነበረም። በሲኦል ያሉ ነፍሳት ለማመንና ንስሐ ለመግባት ዕድል የላቸውምና።</u> ነገር ግን ክርስቶስ ወደ ሲኦል የወረደው ሰው ሆኖ ለማዳን መምጣቱን ያምኑ ለነበሩ ጻድቃነ ብሉይ ድል አድራጊነቱን፥ ነጻ አውጪነቱን፥ በሲኦል ላይ ኀይል ያለው መሆኑን ለማወጅ፥ እነርሱንም ለማውጣት ነው፤ (1ጴጥ. 3፥18-20)።» (የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መሠረት ሃይማኖት እና የክህነት ተልእኮ ገጽ 27)።

በሌላ አቅጣጫ ግን ለሞቱ ሰዎች ተዝካር ከወጣላቸው ምሕረት አግኝተው፥ ከሞት ወደ ሕይወት ይሸጋገራሉ የሚለው ሌላው አስተምህሮዋ፥ የንስሐ መልእክቷን አደናጋሪ እያደረገው ይገኛል። አንዳንዶች እንዲያውም ልባቸው ለዚሁ ትምህርት በመከፈቱ፥ በሕይወት እያሉ ንስሐ ከመግባት ይልቅ ከሞቱ በኋላ ጥሩ ጸሎተ ፍትሐት እንዲደርስላቸውና ተዝካራቸው እንዲወጣላቸው አማጽነው ይሞታሉ።

አንዳንዶቹ ደግሞ ሳይሞቱ የቁም ተዝካራቸውን ደግሰው በማብላት በዚህ አገልግሎት ጽድቅን ለማግኘት ይሻሉ። ሁሉም ግን ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ውጪ የሆነና ለሞተ ሰው ምንም የማይጠቅም አገልግሎት ነው።



# ክፍል 11 - መሥዋዕት

## 11.1 መሥዋዕት በብሉይ ኪዳን

በተለያዩ ምክንያቶች ሰው ለአምላኩ የሚሰጠው ወይም የሚያቀርበው ነገር መሥዋዕት ተብሎ ይጠራል። ሰው በአምላኩ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘትና በቀጣይም ግንኙነቱን ለማጠንከር፥ በአምላኩ ላይ ያለውን ጽኑ እምነት ለመግለጽና ፍቅሩን ለማሳየት፥ ንስሓ ለመግባትና አምላኩን ለማመስገን በመፈለግ የተለያዩ መሥዋዕቶችን ያቀርባል።

መጽሐፍ ቅዱስን ስንገልጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ መሥዋዕት ተጽፎ የምናነበው በዘፍ.4፥4 ላይ ሲሆን፥ በዚህም ክፍል አቤልና ቃየን ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ያቀረቡበትን ታሪክ እናገኛለን። ይሁን እንጂ በግልጽ የተጻፈ ነገር ባናነብም፥ ሁለቱ ወንድማማቾች ስለ መሥዋዕት አቀራረብ ቀደም ብለው የተገነዘቡት ነገር መኖሩንና ለዚህም መነሻ የሆነው መሠረታዊ ሐሳብ በዘፍ. 3፥21 ላይ እንደ ተገለጠ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ያስረዳሉ።

በዚህ ክፍል እንደተጻፈው እግዚአብሔር ራቁትነታቸውን በበለስ ቅጠሎች ለሸፈኑት ለአዳምና ለሔዋን፥ የቁርበት ልብስን አልብሷቸዋል። ይህ ቁርበት ከወዴት መጣ? ቢባል አንድ የእነርሱን ራቁትነት ለመሸፈን ሲባል መሥዋዕት የሆነ ወይም የታረደ እንስሳ አለ ወደሚለው አስተሳሰብ ያመጣናል። በዚህ መነሻነት እንግዲህ ሰዎች ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረብን ተምረዋል ለማለት ይቻላል።

ከሙሴ በፊት በነበሩት ዘመናት የኖሩ አበው በተለያየ ምክንያት መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ያቀርቡ እንደነበር ተጽፏል፤ (ዘፍ. 4፥4፤ 8፥20፤ 12፥7)። እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክ እንደመሆኑ ቅዱስ ነገርን ይፈልጋልና፥ እነዚህ አባቶች ያቀረቡት በእጃቸው ከሚገኘውና ንጹሕ ከተባለው ነገር ነው። እግዚአብሔርም በዚህ ሁኔታ የቀረበለትን መሥዋዕት ተቀብሎታል፤ (ዘፍ. 4፥4፤ 8፥21)።

በሙሴ አማካይነት በተሰጠው ሕገ ኦሪት ውስጥ መሥዋዕትን የሚመለከት ድንጋጌ አለ። በድንጋጌውም ውስጥ ለመሥዋዕትነት ስለሚቀርቡት ነገሮችና ስለሚቀርቡበት ሥርዐት፥ መሥዋዕቱን ወደ እግዚአብሔር ስለሚያመጡት /ስለሚያቀርቡት/ ሰዎች ማንነት፥ መሥዋዕቱን በእግዚአብሔር ፊት የመሠዋት ሥልጣን ስለተሰጣቸው ክፍሎች፥ ስለ መሥዋት ዐይነቶችና ስለ መሳሰሉት ጉዳዮች በዝርዝር ተጽፏል። በዚሁ መሠረት ለመሥዋዕትነት የሚቀርቡት ነገሮች ነውር የሌላቸውና ንጹሓን የሚባሉ የእንስሳትና የአእዋፍ ሥጋ፥ ከእህልና ከመጠጥ ወገንም ይገኝበታል፤ (ዘሌ. 22፥17-25፤ 2፥1-16፤ 6፥14-23፤ ዘፀ. 29፥40-41)።

እስራኤላውያን እንዲያቀርቡ የታዘዙት አምስት ዐይነት መሥዋዕቶችን ነው፤ የመሥዋዕቶቹ ዐይነቶች፥ የሚቀርቡበት ምክንያት፥ መሥዋዕት ሆኖ ስለሚቀርበው ነገርና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃው እንደሚከተለው ቀርቧል: -

1. **የሚቃጠል መሥዋዕት** - እንዲሁ በፈቃድ የሚቀርብ ሲሆን፥ ራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛትንና ሙሉ በሙሉ መስጠትንም ለመግለጽ ይቀርባል:: ባለማወቅ ለተደረገ ኀጢአት ማስተስረያነትም ይቀርባል:: የሚቀርበውም ጠቦት፥ ወይፈን ወይም ተባዕት ወፍ ናቸው (ዘሌ. 1÷6፤ 8-13፤ 8÷18-21፤ 16÷24)::
2. **የእህል ቍርባን** - ፈቃዳዊ አምልኮን ለማቅረብና የእግዚአብሔርን ስጦታ ለማሰብ የሚቀርብ ነው:: የሚቀርቡትም እህል፥ ዱቄት፥ የወይራ ዘይት፥ ዕጣን፥ ኅብስት፥ ወይን ናቸው (ዘሌ. 2፤ 6÷14-23)::
3. **የደኅንነት መሥዋዕት** - ፈቃዳዊ አምልኮንና ምስጋናን ለመግለጽ የሚቀርብ ነው:: አቅራቢው ሰው ከዚህ መሥዋዕት ስለሚበላ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት ይገልጽበታል:: የሚቀርቡትም ከከብት መንጋ ውስጥ ተባዕትና እንስት፥ እንዲሁም ኅብስት ናቸው፤ (ዘሌ. 3÷7፤ 11-34፤ 9÷5-8፤ 22÷21-25)::
4. **የኀጢአት መሥዋዕት** - በማወቅ የተሠራ ኀጢአትን ስለማስወገድ የሚቀርብ ነው:: የሚቀርቡት መሥዋዕቶች እንደ ሰዎቹ ማንነት ይለያያል:: ለሊቀ ካህናቱና ለጉባኤው ከሆነ ወይፈን፥ ለሕዝቡ መሪ ከሆነ ተባዕት ፍየል፥ ለተራው ሕዝብ ከሆነ እንስት ፍየል ወይም በግ፥ ለድኻው ዋኖስ ወይም ርግብ፥ በጣም ድኻ ለሆነው የኢፍ መስፈሪያ አንድ ዐሥረኛ ዱቄት ይቀርባል፤ (ዘሌ 4÷1-5፤ 13፤ 6÷24-30፤ 8÷14-17፤ 16÷3-22)::
5. **የበደል መሥዋዕት** - ሆን ተብሎ በዕቅድ ለሚሠራ ኀጢአትም ይሁን ባለማወቅ ለተደረገ ኀጢአት ማስተስረያነት የሚቀርብ ነው፤ የሚሠዋውም አውራ በግ ነው፤ (ዘሌ. 5÷14-6÷7፤ 7÷1-6)::

እነዚህን መሥዋዕቶች እንዲሠዉ ሥልጣን የተሰጠው ለአሪቱ ካህናት ብቻ ነው፤ (ዘኍ. 3÷10)::

ከላይ ከተመለከትናቸው ከአምስቱ የመሥዋዕት ዐይነቶች መካከል ከእህል ቍርባን በስተቀር የተቀሩት አራቱ ሁሉ ደምን ማፍሰስ የሚጠይቁ ናቸው:: በተለይም የሚቃጠል፥ የኀጢአትና የበደል መሥዋዕቶችን ከተመለከትን፥ የኀጢአት ደመወዙ ሞት መሆኑንና፥ ከዚህ ሞት ለመቤዠት በምትክነት የሚሞት ሌላ ቤዛ ማስፈለጉን ያስገነዝቡናል:: «ደም ሳይፈስ ስርየት የለም» የሚለውም ዘላለማዊ ቃል በዚሁ እውነታ ወስጥ ይረጋገጣል፤ (ዘሌ. 17÷11፤ ዕብ. 9÷22) ::

እያንዳንዱ መሥዋዕት የሚቀርብበት የራሱ የሆነ ሥርዐት ነበረው:: በተለይም የእንስሳት መሥዋዕቶች ሲቀርቡ: -



ሀ. አቅራቢው እስራኤላዊ ነውር የሌለበትን የመሥዋዕቱን እንስሳ ይዞ ወደ መሠዊያው ያመጣል (ዘሌ. 1÷3)፤

ለ. ከዚያም ኀጢአቱን ለእርሱ ቤዛ ሆኖ ለሚሞተው እንስሳ ለማሸከም እጁን በእንስሳው ላይ ይጭንበታል (ዘሌ. 1÷4)፤

ሐ. አቅራቢው እንስሳውን ያርደዋል (ዘሌ. 1 ÷5)፤

መ.ካህኑ ደሙን ወስዶ በመሠዊያው ሥር ይረጨዋል (ዘሌ. 1÷5)፤

ሠ. አሁንም ካህኑ እንደ መሥዋዕቱ ዐይነት ሥጋውን በሙሉም ሆነ በከፊል በትእዛዙ መሠረት ያቃጥላል (ዘሌ. 1÷6-9)::

በዚህ ሥርዐት መሠረት ይቀርቡ የነበሩት መሥዋዕቶች ወደፊት ለሚገለጠውና ፍጹም ለሆነው ለክርስቶስ መሥዋዕትነት ጥላና ምሳሌ እንዲሆኑ የተሰጡ በመሆናቸው፥ ለሰው ጊዜያዊ ስርየትን ከማስጠትና ሥጋን ከማንጻት በቀር ኀጢአትን ለማስወገድ ወይም ፍጹም ድኅነትን ለማስጠት የማይችሉ ነበሩ፤ (ዘሌ. 9÷9-10፤ 13፤ 10÷4፤11)::

መሥዋዕቶቹ ተደጋግመው ይቀርቡ የነበረበት ዋናው ምክንያትም ዘላለማዊ ድኅነትን ለማስጠት የማይችሉ በመሆናቸው እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ነው፤ (ዘፀ. 29÷38-39፤ ዕብ. 10÷11)::

## 11.2 መሥዋዕት በዐዲስ ኪዳን

መሥዋዕተ ኦሪት ለክርስቶስ መሥዋዕትነት ጥላና ምሳሌ ሆኖ እንደ መስጠቱ÷ በአገልግሎት ላይ እንዲቆይ በእግዚአብሔር የታቀደለት ጊዜ ክርስቶስ እስከሚሠዋበት ዕለት ድረስ ነበር።

በዕለቱ ዋዜማ ምሽት ላይ ጌታ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን እራት ለመብላት በማዕድ ተቀምጦ ሳለ÷ ለሞቱና ለትንሣኤው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በኅብስትና በወይን ሥጋና ደሙን ሲሰጥ÷ መሥዋዕተ ኦሪት ማለፉን÷ ዐዲስ ኪዳን የሚጸናበት የእርሱ ክቡር ደም ለኀጢአት ስርየት የሚፈስ መሆኑንና ቅዱስ ሥጋውም እንደሚሰጥ አበሠረ፤ (ሉቃ .22÷19-20፤ 1ቆሮ. 11÷23-26)። ከዚህን ጊዜ አንሥቶ በጊዜያዊነት ተሰጥቶ የነበረው መሥዋዕተ ኦሪት ዐልፏል፤ ወይም በክርስቶስ መሥዋዕትነት ተተክቷል።

የኦሪቱ መሥዋዕት ቀድሞውንም ግዳጅ መፈጸም የማይችል በመሆኑ ከሌሎቹ መንፈሳውያን መሥዋዕቶች÷ በተለይም በዐዲስ ኪዳን ምእመናን ወንጌል ከሚያቀርቧቸው÷ ይልቁንም ደግሞ ከክርስቶስ መሥዋዕትነት ጋር ሲነጻጸር÷ እግዚአብሔር በእርሱ የማይደሰትበት መሆኑን ደጋግሞ ተናግሯል፤ (መዝ. 39(40)÷6፤ 49(50)÷7-14፤ 50(51)÷16-17፤ ሆሴ. 6÷6፤ ማቴ. 12÷7፤ ማር. 12÷33፤ ዕብ. 10÷5-10)።

ይሁን እንጂ በቅዱሳት መጻሕፍት የተሰጠውን ይህን ምስክርነት ያላስተዋሉትና የክርስቶስን መሲሕነት ያልተቀበሉት ወገኖቹ እስራኤላውያን÷ ዘመኑ ከተፈጸመ በኋላም÷ የኦሪቱን መሥዋዕት መሠዋት አልተዉም ነበር። በ70 ዓ.ም ሮማውያን የኢየሩሳሌሙን ቤተ መቅደስ ሲያፈርሱት ግን መሥዋዕታቸውም ቀርቷል። እስከ 70 ዓ.ም ያቀረቡትም ቢሆን ጊዜ ያለፈበትና እግዚአብሔር በመሥዋዕትነት ሊቀበለው የማይችል ነበር።

የዐዲስ ኪዳን መሥዋዕት ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ (ዕብ. 7÷27፤ 9÷13-14፤ 10÷3-14)። በዚህም ምክንያት «የዓለሙን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» «ፋሲካችን» ተብሎ ተጠርቷል፤ (ዮሐ. 1÷29፤ 36፤ 1ቆሮ. 5÷7) ።

የክርስቶስ መሥዋዕትነት እንደ ኦሪቱ ሥጋን የሚያነጻና ውጫዊ ስርየትን ብቻ የሚያሰጥ አይደለም። የኦሪቱ መሥዋዕት ሊያደርግ ያልተቻለውንና ከዐቅሙ በላይ የሆነውን÷ ኅሊናን ከሞተ ሥራ የማንጻትና ድኅነተ ነፍስን የማሰጠት ሥራን ለመሥራት ብቃት ያለው ሆኗል፤ (ዕብ. 10÷1፤4)።

የብሉይ ኪዳን ሰዎች በተደጋጋሚ ለብዙ ጊዜያት ባቀረቧቸው መሥዋዕቶች ስርየተ ነፍስን ስላላገኙ÷ በጊዜአዊ ስርየት ተከድኖ በዐዲስ ኪዳን መሥዋዕት ይነጻ ዘንድ የተጠበቀውን ኀጢአትም ለማንጻት ተችሎታል፤ (ዕብ. 10÷2፤ 11፤9÷23፤ 1ዮሐ .2÷2)።



ይህ መሥዋዕት ፍጹም በመሆኑ በተደጋጋሚ መቅረብ አላስፈለገውም፤ አንድ ጊዜ ለዘላላም የቀረበው ያመኑበትን ሁሉ የዘላለም ፍጹማን አድርጓቸዋል፤ (ዕብ. 7÷27፤9÷12፤ 25-26፤ 10÷10-14፤18)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕት አቅራቢ ሊቀ ካህናት ሲሆን÷ ወዲህም መሥዋዕት በመሆኑ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ሲያቀርብ÷ በኦሪቱ መሥዋዕት አምሳል ቤዛ ሆኖ የሚሞትላቸውን ሰዎች ኀጢአት በሥጋው ተሸክሞአል፤ (ኢሳ. 53÷6፤ 1ጴጥ. 2÷24፤ ሮሜ 6÷6)። የኀጢአት ደመወዝ ሞት በመሆኑም ስለ ኀጢአት ተሠውቶአል፤ (ሮሜ 6÷23፤ ዕብ. 9÷28)።

መሥዋዕት ሲቀርብ የመሥዋዕቱ ደም በእግዚአብሔር ፊት መቅረቡም የግድ ነውና÷ በሊቀ ካህንነቱ ስለ ኀጢአት ስርየት የፈሰሰውን ደሙን ይዞ ወደሚያገለግልባት መቅደስ ገብቷል። በዚያም ስለ እኛ ይታያል፤ (ዘሌ. 1÷5፤ 17÷11፤ ዕብ. 9÷12፤ 24፤ 28)።

እንግዲህ እኛ ነጻ የምንወጣውና የኀጢአታችንን ስርየት የምንቀበለው÷ ክርስቶስ አንድ ጊዜ በዚህ ሁኔታ ያቀረበልንን መሥዋዕት በእምነት ስንቀበለው ብቻ ይሆናል።

አንድ ጊዜ ለዘላለም አቅርቦ በአብ ቀኝ የተቀመጠው÷ እኛን ነጻ ሊያወጣ እንጂ÷ ለሰዎች እንዳዚህ ያለ የመሥዋዕት አቀራረብ ሥርዐትን አስተምሮ ለማለፍ አይደለም። ይህን የዐዲስ ኪዳን መሥዋዕት ለማቅረብ ብቸኛ ሥልጣን ያለው እርሱ ብቻ ነውና። ያቀረበው መሥዋዕትም ሁሉን ያነጻና ፍጹም በመሆኑ ድግግሞሽ ስለማያስፈልገው÷ እርሱን ተክቶም ሆነ በእርሱ አምሳል ይህን መሥዋዕት እንዲያቀርብ ማንንም አላዘዘም። የሚቀርብ ሌላ መሥዋዕትም የለም፤ (ዕብ. 7÷27፤ 9÷12፤ 26-28፤ 10÷12፤ 14፤ 1ጴጥ. 3÷18፤ ሮሜ 6÷10)።

እኛን ያነጻንና ያዳነን ከላይ የተመለከትነው የክርስቶስ መሥዋዕት አቀራረብ ሁኔታ እንጂ÷ ሌላ ሰው ሠራሽ ሥርዐት አለመሆኑን÷ በመጽሐፍ ቅዱስ የተመሠረተው የቤተ ክርስቲያን ትምህርትም ይመሰክራል።

> «ጥበብሰ መድኀኒነ ውእቱ፤ ዘቤዘወነ በጥብሐ ሥጋሁ÷ ወተሳየጠነ በንዝኀተ ደሙ÷ ወኀረየነ ለመንግሥቱ፤»
>
> ትርጓሜ: - «ጥበብ ግን መድኀኒታችን ነው፤ በሥጋው መሥዋዕትነት ያዳነን ÷ በደሙም ፈሳሽነት የተቤዠን÷ ለመንግሥቱ የመረጠን፤» (ቅዳ. ኤጲፋንዮስ ቍ. 86)።
>
> «በውኂዘ ደሙ ቅዱስ አንጽሖሙ ለመሃይምናን ወለሕዝብ ንጹሓን» ማለትም «በከበረ ደሙ መፍሰስ ያመኑትንና ንጹሓን የሆኑትን ወገኖች አነጻቸው።» (ውዳ. ማርያም ዘእሑድ)።

ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ከተረዳን ፥ ያን ጊዜ ክርስቶስ ሥጋውን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ወደ ቅድስት ይዞ የገባው ደሙ ዛሬም ሕያው ነው። ቤዛነታችን የተደረገውና ከከንቱ ኑሯችን የተዋጀነው በዚህ የክርስቶስ ክቡር ደም ነው (ኤፌ. 1፥7፤ 1ጴጥ. 1፥19)፤ በሌላ ሳይሆን አሁንም በዚያው ደም ጻድቃን ከቍጣው እንድናለን (ሮሜ. 5፥9)፤ በእምነት ተረጭተን እንቀደሳለን (1ጴጥ. 1፥1-2)፤ ወደ እግዚአብሔርም እንቀርባለን (ኤፌ. 2፥13)፤ ኀጢአታችንን ይቅር ይለን ዘንድ የታመነና ጻድቅ ለሆነው ለእርሱ ተናዝዘን በደሙ እንነጻለን (1ዮሐ. 1፥7-9)።

ይህ ደም እንደ አቤል ደም ክስን የሚናገር ሳይሆን፥ የተሻለውን ነገር በመናገር ዕርቅን የሚጠይቅና ስርየትን የሚያሰጥ የመርጨት ደም ነው፤ (ዕብ. 12፥24)። በቅዳሴ ሐዋርያት ቍ. 106 ላይ የሚከተለው ተጽፎአል፦

> «ወናሁ ደም መሲሕከ ንጹሕ ዘተክዕወ በእንቲአየ፥ ይኬልሕ ህየንቴየ፤ ዝንቱ ደም ነባቢ ይኩን ሰራዬ ኀጢአትየ ለገብርከ።»
>
> ትርጓሜ፦ «ስለኔ በቀራንዮ የፈሰሰው ንጹሕ የሚሆን የመሲሕም ደም፥ እነሆ ስለ እኔ ይጮሃል፤ ይህ የሚናገር ደም የኔን የባሪያህን ኀጢአት የሚያስተሰርይ ይሁን።»

በእውነትም ከዚህ፥ አንድ ጊዜ ብቻ ከቀረበ አማናዊ መሥዋዕት ውጪ ኀጢአት የሚሰረይበት ሌላ መሥዋዕት ፈጽሞ የለም! እግዚአብሔር በዚህ መሥዋዕት ስለረካ ኀጢአታችንንና ዐመፃችንን ደግሞ እንደማያስበው ቃል ገብቷል። «የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ኀጢአት ማቅረብ የለም፤» (ዕብ. 10፥17-18)።



## 11.3 ሥጋሁ ወደሙ

መሥዋዕት ከሰው ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ነገር መሆኑን የመሥዋዕትን ፅንሰ ሐሳብ በመመልከት ለመረዳት ይቻላል።

በዐዲስ ኪዳን የቀረበውን ፍጹምና አዳኝ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያቀረበው የዐዲስ ኪዳን ብቸኛ ሊቀ ካህናት የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም ያቀረበው ሌላውን እንስሳትንና አዕዋፍን ወይም የአዝርዕት ውጤት የሆነውን የእህልና የመጠጥ ቍርባን አይደለም። ለእግዚአብሔር ያማረና የተወደደ ቍርባን አድርጎ ያቀረበው ራሱን ነው፤ (ኤፌ. 5፥2፤ ዕብ. 9፥12)።

ቤተ ክርስቲያናችን ይህን እውነት ትቀበለዋለች። ሆኖም ግን በተጨማሪነት ክርስቶስ አንድ ጊዜ እንዳቀረበው ያለ መሥዋዕት ቀሳውስት ዛሬ እንደሚሠዉ፥ ይህም መሥዋዕት ሥጋና ደሙ እንደሆነ ይታመናል።

የቅዱስ ቍርባን ሥርዐት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ኀሙስ (ኀሙስ ምሽት ላይ) ለደቀ መዛሙርቱ ሲሰጥ ዋና ዐላማው፥ በማግስቱ ራሱን በመስቀል ላይ ቤዛ አድርጎ ማቅረቡ እንዲዘከርበት፥ ከዚህ የከበረ ምስጢር በመቀበል ምእመናን ከክርስቶስ ጋርና እርስ በርሳቸውም የሚኖራቸውን አንድነት ወይም ኅብረት እንዲያጠናክሩበት፥ እንዲሁም የኀጢአትን ዕንቅፋት ዘወትር ከሕይወታቸው አስወግደው በቅድስና እንዲኖሩ ለማድረግ ነው።

በመሆኑም ቅዱስ ቍርባንን፥ በእርሱ መንፈሳዊ ጥቅምን ለሚያገኙት ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ እንጂ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ አላቀረበውም፤ (ማቴ. 26፥26-28፤ ማር. 14፥22-25)። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቅዱስ ቍርባን በሚናገርባቸው ክፍሎች ሁሉ መሥዋዕት እንደሆነ ፈጽሞ አይናገሩም።

በማቴ. 26፥26-28፤ ማር. 14፥22-25፤ ሉቃ. 22፥19-20 ባለው ክፍል ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስቱን አንሥቶ፦ «ይህ ሥጋዬ ነው» የወይኑን ጭማቂ ይዞ ደግሞ፦ «ስለ ብዙዎች የሚፈስ የዐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው» ሲል ተናግሯል። እንዲህ ሲል ግን በመስቀል ላይ መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርበው ሥጋዬና ደሜ ይህ ነው ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። እንዲህማ ቢሆን አማናዊ የሆነው የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋ በተቀበለው ጸዋትወ መከራ መቈራረስና ክቡር ደሙም መፍሰስ ሳያስፈልገው፥ ድኅነታችን በቅዱስ ቍርባን ብቻ መፈጸም ይበቃው ነበር።

በኅብስትና በወይን የተሰጠው ቅዱስ ቍርባን ክርስቶስ መሥዋዕት ሆኖ ለመቅረቡ መታሰቢያ እንዲሆን መሰጠቱን፥ ቅዱስ ሉቃስ የጌታን ቃል ጠቅሶ፥ ቅዱስ ጳውሎስም ከጌታ የተቀበለውን ጽፈው አስተላልፈውልናል። «እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ፤ ቆርሶም ሰጣቸውና ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፥ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።» (ሉቃ. 22፥19)፥ «ለእናንተ ደግሞ

አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና፥ ጌታ ኢየሱስ ዐልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም እንካችሁ ብሎ፥ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው:: ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ:: እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ: - ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን ዐዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ::» (1ቆሮ. 11÷23-25)::

ቀደምት ኦርቶዶክሳውያን አባቶችም ከጌታ ወደ ሐዋርያቱ የተላለፈውንና በቅብብሎሽ ወደ እነርሱ የደረሰውን ይህን እውነት ደግመው አስተጋብተውታል::

> «ወለዝ ሶበ ትገብርዎ ተዝካረ ሞትየ ትገብሩ፤ ወተዝካረ ትንሣኤየ ትዜንዉ::» ማለትም «ይህን በምታደርጉበት ጊዜ የሞቴን መታሰቢያ ታደርጋላችሁ፤ የትንሣኤዬንም መታሰቢያ ትናገራላችሁ::» (ቅዳ. ማር ቍ. 110)::
>
> በቅዳሴ እግዚእም እንደዚሁ «ወሶበ ዘንተ ትገብሩ ተዝካረ ዚአየ ግበሩ» ማለትም «ይህን በምታደርጉበት ጊዜ የእኔን መታሰቢያ አድርጉ::» ይላል (ቍ. 42)::

ቅዱስ ቍርባንን «*መሥዋዕት*» በማለት የሚጠራው ቢሆንም፥ የሚቀርብበትን ዐላማ ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወርቅም በድርሳኑ በትክክል አስቀምጦታል::

> «እመቦ ዘይብል አኮኑ ንሕነ ናዐርግ *መሥዋዕተ* ኵሎ ዕለተ፥ ንብሎ ንሠውዕ ለተዝካረ ሞቱ ለልዑል፤ *መሥዋዕት* አሐተ ወአኮ ብዙኀ::»
>
> ትርጓሜ: - «እኛስ በየዕለቱ ሁሉ *መሥዋዕት* እንሠዋ የለምን? የሚል ሰው ቢኖር፥ እኛስ ለልዑል ጌታ ለሞቱ መታሰቢያ እንሠዋለን እንለዋለን::» (17ኛ ድር. ቁ.121-122)::

መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱስ ቍርባንን: - የክርስቶስ ሥጋና ደም (1ቆሮ. 11÷27-29)፥ እንዲሁም የጌታ እራት በማለት ይጠራዋል (1ቆሮ. 10÷20)::

እውነተኛ ክርስቲያ፥ ሥጋሁ ወደሙን እንደ ተራ ምግብና መጠጥ አይቈጥረውም:: ምንም እንኳ እኛ ዘወትር በተራ ምግብነት ከምንጠቀምባቸው ከስንዴና ከወይን የሚዘጋጅ ቢሆንም፥ በቅዱስ ቍርባንነት የሚቀርብ በመሆኑ፥ ተራ ምግብነቱ ቀርቶ ከክርስቶስ ሥጋና ደም ጋር ኅብረት ያለው መንፈሳዊ ምግበ ነፍስ ይሆናል፤ (1ቆሮ. 10÷16):: እንዲህማ ባይሆን ከእርሱ ለመብላትና ለመጠጣት ራስን መመርመር ባላስፈለገ፥ አለአግባብ በሚቀበሉትም ላይ ፍርድ ቅጣትን ባላመጣ ነበር፤ (1ቆሮ. 11÷27-30)::

የጌታ ሥጋና ደም ለምእመናን የሚሰጠው መንፈሳዊ ጠቀሜታ ላቅ ያለ ነው:: የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው: -



1. ይህ ምስጢር ከክርስቶስ ሥጋና ደም ጋር ኅብረት ያለው በመሆኑ፥ ምእመናንን በመጀመሪያ ከክርስቶስ ጋር፥ ቀጥሎም ከሌሎች ምእመናን ወይም እርስ በርሳቸው ኅብረት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤ (1ቆሮ. 10÷16-17)::
2. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ የሞቱ መታሰቢያ እንዲደረግ ባዘዘው መሠረት የሚቈርቡ ሁሉ፥ የኅብስቱ መቈረስና የወይኑ መቅረብ የክርስቶስ ሥጋ ስለ እነርሱ እንደ ተቈረሰና ደሙም እንደ ፈሰሰ በማስታወስና ጥልቅ በሆነ ፍቅር «በመስቀል ላይ ያኔ ያ ሥጋ የደቀቀው፥ ያም ደም የፈሰሰው ስለ እኔ ነው::» እያሉ ክርስቶስ በሞቱ እንዳዳናቸው ያስቡበታል::

   እንዲሁ ዐልፎ ዐልፎ በቅዳሴ ጊዜ የሚደገም ሥርዐት ብቻ ሆኖ ቢቀርም በትእምርተ ኅቡኣት የተጻፈውን ማስተዋል የሚችል ሰው ቢኖር እንዲህ ሲል ጥያቄ ይጠይቃል: - «መፍትው እንከ ነገረ ኅቡኣት መነሃ ትሳተፉ ለቅድሳት ወለመኑ ትገብሩ ተዝካሮ በአኰቴት» «በቅዱስ ቍርባን ከማን ጋር አንድ ትሆናላችሁ? በምስጋና የምታደርጉት መታሰቢያውስ የማን ነው?» ምእመናንም በሌላው ስፍራ የሚሰጡት ምላሽ የክርስቶስን ሞት ለማሰብ መሰብሰባቸውን የሚገልጽ ነው:: «ንዜኑ ሞተከ ወትንሣኤከ ቅድስተ» «አቤቱ ሞትህንና ቅድስት ትንሣኤህን እንናገራለን::» ይላሉ:: «ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ፥ ይህንንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና::» ተብሎ እንደተጻፈ (1ቆሮ. 11÷26)::
3. ቅዱስ ቍርባን ምእመናንን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ያደርጋቸዋል:: አንድ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ አደገ የሚባለው፥ የተቤዠውን አዳኙን ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ መከተል ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ በኑሮው ክርስቶስን ወደ መምሰል እስኪመጣ ድረስ፥ የኀጢአት ዕንቅፋቶችን ከመንገዱ በማስወገድ ቃሉን እየፈጸመ ሲኖር ነው:: ለዚህ ደግሞ ቅዱስ ቍርባን የሚኖረው ሚና በቀላሉ የሚታይ አይሆንም:: ምክንያቱም ምእመኑ ወደእርሱ ሲቀርብ የሚቀበለው ከበድ ያለ ታላቅ ምስጢር መሆኑን ስለሚገነዘብ፥ በቃሉ እንደተጻፈው ወደ ፍርድ እንዳይገባና ዕዳ እንዳይኖርበት ራሱን በመመርመር ስለ ኀጢአቱ ንስሐ ይገባል:: ከዚህ የተነሣ ቅዱስ ቍርባን ሁልጊዜ በንስሐ ሕይወት እንድንመላለስ ያደርገናል ማለት ነው::

   ሌላውና ትልቁ የመንፈሳዊ ዕድገት ምልክቱ ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን የተቀበለውን መከራና ሞት ዘወትር በማሰብ፥ ልባችን በእርሱ ፍቅር መሞላት መቻሉ ነው:: ይህ ከሆነ የክርስቶስ ምርኮኛ መሆን ስለሚቻል እርሱን ለመታዘዝ የተሰበረ ልብ ይኖረናል:: እርሱም (ቅ/ቍርባን) ይህንኑ ያሳስበናል::

የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ብቸኛው መንገድ በክርስቶስ ኢየሱስ አዳኝነት ማመን መሆኑ ጊዜ የማይሽረውና የማያሻሽለው፥ ቅዱስ ቍርባንም ሆነ ሌላው መሰል ምስጢርና ሥርዐት የማይተካው

እውነት መሆኑ ምስክር የማያሻው ጉዳይ ነው:: ሐቁ ይህ ሆኖ ሳለ ክርስቶስን አምኖ መዳን ሥጋሁ ወደሙን በመቀበል ተተክቶ መሰበኩና ሁለቱም እውነታዎች መምታታቸው፥ በቤተ ክርስቲያናችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ሥር እየሰደደ የመጣ ትምህርት ነው::

በዚህ አመለካከት መሠረት የእውነታው ቅደም ተከተል ተቀዳድሞና አንዱ የሌላውን የማንነት ስፍራ ቀምቶ ይታያል:: ይህ ግን ትልቅ ስሕተት ነው:: ስለሆነም በክርስቶስ አምኖ መዳንንና ቅዱስ ቍርባን የሚሰጠንን መንፈሳዊ ጥቅም በሰዎች የአሰባበክ መስፈርት በመለካት ሳናቀዳድምና ሳናምታታ፥ የእግዚአብሔር ቃል በሚለው መሠረት አግባብነት ባለው ሁኔታ በሕይወታችን ልናስተናግዳቸው ይገባል::

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቅዱስ ቍርባን የሚናገረው እስካሁን በማብራሪያ ተደግፈው ከተጠቀሱት የማይወጣ ቢሆንም በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ውስጥ «ሥጋዬ ... ደሜ» በማለት ክርስቶስ በምስጢራዊ አነጋገር የገለጸውን ከቅዱስ ቍርባን ጋር ማያያዝ የተለመደ ነገር ሆኗል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ማመን ይህን ምስጢር በመቀበል እንዲተካ እየተደረገ ያለው ጥረትም ተቀባይነትን እያገኘ የመጣው፥ ይህንኑ የወንጌል ክፍል ስለ ቅዱስ ቍርባን እንደ ተነገረ አድርጎ በመተርጐም መሆኑ ግልጽ ነው::

ይህን ክፍል በማስተዋል የምናጠና ከሆነ፥ ጌታ ክርስቶስ ስለ ቅዱስ ቍርባን ወይም ስለሚበላና ስለሚጠጣ ሥጋና ደም እንዳልተናገረ እንረዳለን:: በዚህ ክፍል በመብልና በመጠጥ መስሎ የተናገረው በእርሱ ስለ ማመን ጉዳይ ነው::

ነገሩን ከሥረ መሠረቱ እንመልከት ካልን እንዲህ ነው፥ ጌታ በገሊላ ባሕር ማዶ አምስቱን የገብስ እንጀራና ሁለቱን ዓሣ አምስት ሺህ ለሚያህሉ ሰዎች በተኣምራት መግቦ ዐሥራ ሁለት መሶብ ፍርፋሪ እንዲነሣ ባደረገበት ወቅት፥ ተመጋቢዎቹ ኢየሱስ ሥጋዊ ፍላጎታቸውን በማሟላት ሊጠቅማቸው እንደሚችል ስለተገነዘቡ ሊያነግሡት ፈለጉ:: እርሱም ይህን ሐሳባቸውን ዐውቆ ከእነርሱ ዘንድ ዘወር አለ:: እነርሱም ኢየሱስን መፈለጋቸውን ቀጠለው ከብዙ ፍለጋ በኋላ ሲያገኙት፥ «መምህር ሆይ ወደዚህ መቼ መጣህ?» የሚል ጥያቄ አቀረቡለት:: እርሱም መልሶ እንዲህ አጥብቀው የፈለጉት በልተው ስለጠገቡ እንጂ፥ የበሉት እንጀራ በድንቅና በተኣምራት የተገኘ መሆኑን ስላስተዋሉ አለመሆኑን ገልጾ፥ ኀላፊ ለሆነው መብል ሳይሆን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል እንዲሠሩ ነገራቸው::

እነርሱም በማስከተል ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል መሥራት፥ ወይም የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ጠየቁት:: ጌታም ሲመልስ «ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው::» አለ (ቍ. 29):: ከዚህ ምላሽ የምንረዳው ጌታ ገና ከመጀመሪያው በመብል መስሎ የተናገረው በእርሱ ስለማመን መሆኑን ነው::

ለዓለም ሕይወት የሚሰጥና ከሰማይ የወረደ እንጀራ ራሱ ጌታችን ነው:: እርሱን መብላትና መጠጣት ማለትም ሰዎች እንደ ሰጡት ትክክለኛ



ያልሆነ ትርጓሜ ሳይሆን፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠው ትርጓሜ መሠረት ለመረዳት ቢያስፈልግ ቍጥር 35ን ይመለከቷል:: «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በኔ የሚያምንም ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም::» ይላል:: መብላትን: - ወደ እርሱ በመምጣት፥ መጠጣትን ደግሞ በእርሱ በማመን ተረጒመው ማለት ነው::

ዝቅ ብለው ባሉት ቍጥሮች ውስጥም ንግግሩን በመቀጠል ይህን ከሰማይ የወረደ የራሱን እንጀራነት «ሥጋዬ ... ደሜ» በማለት ይጠራዋል:: በወቅቱ ታዳያ ይህን ትምህርት የሰሙ ንግግሩ የሚያስጨንቅ ሆኖባቸው ክርስቶስን ከመከተል ወደ ኋላ አፈግፍገዋል:: ለዚህም ምክንያቱ ክርስቶስ ሥጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ ብሎ መናገሩን፥ የራሱን የሰውነቱን ሥጋ ከመብላትና ደሙን ከመጠጣት ጋር አያይዘው ስለ ተረጐሙት ነው:: በእርግጥም እንዲህ ከሆነ ንግግሩ ሊያስጨንቅ ይችላል:: እርሱ ግን ለማለት የፈለገው ይህን አይደለም፤ ለሰው ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ እንጂ በአፍ ጎርሰውት፥ በጥርስ አድቅቀውት፥ በመላስ አላምጠውት ወደ ሆድ የሚገባው ሥጋና ደም አለመሆኑን ቍጥር 63 ላይ በግልጽ አስቀምጦታል:: «ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤ እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው::» ::

በዚህ ንግግር ተሰነካክለው ብዙዎቹ ወደ ኋላ ሲያፈገፍጉ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት: - «እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን?» በማለት ጠየቃቸው:: ከደቀ መዛሙርቱም ክርስቶስ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መንፈሳዊ ነገር የተረዳው፥ ስምዖን ጴጥሮስ ንግግሩን እንዳላስተዋሉት አይሁድ «ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል?» (ቍ. 52) ብሎ ሳይከራከር፥ እንደ ብዙዎቹ ደቀ መዛሙርትም «ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው ማን ሊሰማው ይችላል?» ሳይል (ቍ. 60) በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት፥ ክርስቶስን መንፈሳዊ መብል አድርጎ በእምነት መብላትና መጠጣት የሚቻል መሆኑን ባገናዘበ ሁኔታ «ጌታ ሆይ! ወደ ማን እንሄዳለን አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤ እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ አምነናል፤ አውቀናልም::» በማለት መለሰ (ቍ. 68-69):: ስለሆነም ይህ ክፍል የሚናገረው ክርስቶስን ስለ ማመን እንጂ ስለ ቅዱስ ቍርባን አለመሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል::

እውነታውንም የተመለከትን እንደ ሆነ የክርስቶስ የሞቱ መታሰቢያ የሆነውን ሥጋሁ ወደሙን የሚቀበል ሰው፥ በቅድሚያ ከሰማይ የወረደውን የሕይወት እንጀራ ክርስቶስን የሕይወቱ ምግብና መጠጥ አድርጎ በእምነት ሊበላውና ሊጠጣው ይገባል:: ከዚህ በኋላ ነው ክርስቶስን በእምነት ምግብና መጠጥ አድርጎ ለተመገበው መንፈሳዊ ምግብ ማኅተምና ምልክት የሆነውን ቅዱስ ቍርባንን መቀበል ያለበት::

## 11.4 መንፈሳውያን መሥዋዕቶች

ብዙ ጊዜ የመሥዋት ነገር ሲነሣ በቶሎ የሚታሰበው ኀጢአትን ለማስተስረይ የሚያበረክተው ትልቅ ድርሻ ነው:: በእርግጥም እንዲህ ማሰብ ስሕተት አይደለም፤ እስካሁን ድረስ እንደ ተመለከትነው በዐዲስ ኪዳን ስለ ኀጢአት መሥዋዕት እንዲያቀርብ በእግዚአብሔር የተወሰነው ፍጹሙ ሊቀ ካህናት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: በዚሁ አምላካዊ ውሳኔና ፈቃድ፥ የዐዲስ ኪዳን መሥዋዕት የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል፤ አንድ ጊዜ የሚቀደሱትንም የዘላለም ፍጹማን አድርጓቸዋል፤ (ዕብ. 10÷10-17):: በዚህ መሥዋዕት ኀጢአት ይቅር ስለ ተባለና ዳግመኛም ለዘላለም ስለማይታሰብ፥ ሌላ ተጨማሪ መሥዋዕት አላስፈለገም:: «የእነዚህ ስርየት ባለበት ዘንድ፥ ከዚህ ወዲህ ስለ ኀጢአት ማቅረብ የለም::» (ዕብ. 10÷18)::

ምእመናን ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ፥ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕት ማቅረብ እንዳለባቸውና፥ ለዚህም ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ መታዘዛቸውን የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል:: «በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ፥ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ::» (1ጴጥ. 2÷5)::

በዐዲስ ኪዳን ዘመን ክርስቲያን መሆን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው ታላቅ ዕቅድ ነው:: ክርስቲያን ማለት ክርስቶሳዊ፥ የክርስቶስ ወገን፥ በኑሮው ሁሉ ክርስቶስን የሚመስል የሰማያዊ አገር ዜጋ ማለት ነው::

አንድ ሰው ክርስቲያን የሆነው ማመኑን በስምና በንግግር ብቻ ሊገልጽ ሳይሆን፥ የክርስቶስን የኑሮ ፈለግ በመከተል ክርስትናን በመኖር ሊመሰክር ጭምር ነው:: አንድ ሰው ወይም ክርስቲያን በትክክል አምኖ ድኗል የሚሰኘው ቅሉ፥ በእግዚአብሔር ጸጋ በመታገዝ ከኀጢአት ሕይወት ርቆ መልካም ሥራን ሁሉ ሲሠራ ነው (ማቴ. 5÷16፤ ገላ. 5÷6፤ ኤፌ. 4÷28፤ ያዕ. 2÷14-26፤ 1ዮሐ.2÷6)::

ምእመናን የሚያቀርቧቸው መንፈሳውያን መሥዋዕቶች የዚሁ መልካም ሥራ አካል ናቸው ለማለት ይቻላል:: በእነዚህ መሥዋዕቶች እግዚአብሔርን ይታዘዙታል፤ ያገለግሉታል፤ ያመልኩታልም:: በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም በዐዲስ ኪዳን ክፍል ከምናገናቸው መንፈሳውያን መሥዋዕቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል: -

1. የግል ሕይወትን ወይም ሁለንተናን ለእግዚአብሔር አገልግሎት ማዋል (ሮሜ 12÷1-2)፤
2. ለመንፈሳዊ አገልግሎት ወይም ለወንጌል ሥራ የሚውል ስጦታ (ፊልጵ. 4÷18)፤
3. ምስጋናና ስለ ጌታ የመመስከር መሥዋዕትን ማቅረብ (ዕብ. 13÷15)፤
4. ካለን ነገር ላይ ለሌሎች ማካፈል (ዕብ. 13÷16)፤
5. ጸሎት መጸለይ (ራእ. 8÷3-4)፤



6. ለሰዎች ወንጌልን ሰብኮ ወደ እምነት ማምጣት (ሮሜ 15÷15-16)፤
7. ምሕረትን ማድረግ (ማቴ. 12÷7)፤

ከላይ እንደ ተገለጸው እነዚህ ሁሉ መሥዋዕቶች እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ መልካም ምግባሮች ናቸው እንጂ፥ ለሰው ድኅነትን የሚያስጡ ነገሮች አይደሉም::

ምእመናን በዐዲስ ኪዳን እንዲያቀርቧቸው የታዘዙት መሥዋዕቶች እነዚህና የመሳሰሉት ቢሆኑም፥ በኦሪቱ ዘመን ለእግዚአብሔር ይቀርቡ ከነበሩት ነገሮች መካከል ለምሳሌ ዕጣን፥ መብራት፥ ወዘተ ... ዛሬም በቤተ ክርስቲናችን እንደ መሥዋዕት ተቈጥረው እየቀረቡ ነው:: በዐዲስ ኪዳን ዘመን ግን እነዚህን ነገሮች በመሥዋዕት ስም እንዲያቀርቡ ክርስቲያኖች አልታዘዙም:: ታዲያ ቤተ ክርስቲያናችን ከየት አምጥታ ነው ዕጣንና መብራትን (ጧፍና ሻማን) መሥዋዕት አድርጋ የምታቀርበው ቢባል፥ መጽሐፍ ቅዱስ ባይልም እርሷ ይጠቅሙኛል ብላ ከያዘቻቸው ከሌሎቹ የኦሪት ነገሮች ጋር የተቀበለቻቸው ሊሆኑ ይችላሉ::

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው የጥንታውያን አባቶች ትምህርት ግን ምእመናን ወንጌል፥ ከኦሪቱ መሥዋዕቶች መካከል ዛሬ የሚሠዉት ምንም ምን እንደሌለና፥ መሥዋዕታቸው ሁሉ ከላይ የተዘረዘሩትን የመሰለ መንፈሳዊ መሥዋዕት መሆኑን መስክረዋል::

ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወርቅ: -

> «መሥዋዕት ዘይቤ ፍሬ ከናፍር ውእቱ እለ ይትአመኑ በስሙ፥ ወእሉሰ አቅረቡ አባግዐ ወአልህምተ፥ ወንሕነኒ ኢናበውእ ምንተኒ እምእሉ ግብራት፥ አላ አኰቴተ፤ ከመትጸናዕ ከናፍሪነ ዘከመዝ ጽንዐ:: እስመ እግዚአብሔር ይሠምር በዘከመዝ መሥዋዕት፥ መፍትው ለነ ናብእ ሎቱ ዘከመዝ መሥዋዕተ»
>
> ትርጓሜ: - «መሥዋዕት የሚለው በስሙ የሚታመኑ የከንፈሮችን ፍሬ ነው፤ እነርሱም (ካህናተ ኦሪት) በጎችንና ላሞችን መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ፤ እኛ (ካህናተ ወንጌል ምእመናን) ግን ከእነዚህ ነገሮች መካከል ምንም ምን አንሠዋም፤ ምስጋናን መሥዋዕት አድርገን እናቀርባለን እንጂ፤ አንደበታችን እንደዚህ ባለ ምስጋና እግዚአብሔርን በማመስገን ትጸና ዘንድ፤ እግዚአብሔር እንደዚህ ያለውን መሥዋዕት ቢያቀርቡለት ይወዳልና፤ ስለዚህ እኛም እንደዚህ ያለ መሥዋዕት እናቀርብለት ዘንድ ይገባል፤»::

# ክፍል 12 - ዕጣን

## 12.1 ዕጣን በብሉይ ኪዳን

ዕጣን በብሉይ ኪዳን ዘመን ጣፋጭና የተወደደ መዓዛ ኖሯቸው፥ በእግዚአብሔር ፊት እንዲቀርቡ ከታዘዙት መሥዋዕቶች መካከል አንዱ ነው፤ (ዘፀ. 30፥34-36፤ ዘሌ. 16፥12-13)።

ዕጣን እንደ ሌሎቹ መሥዋዕቶች ሁሉ ራሱን ችሎ በነግህ እና በሠርክ (ማለዳና ማታ) የሚቀርብ የዘወትር መሥዋዕት በመሆኑ (ዘፀ. 38፥7-8)፥ የተለየ መሠዊያ እንዲዘጋጅለት አስፈልጓል። ስለ መሠዊያው አጠቃላይ አሠራር በኦሪት መጻሕፍት ውስጥ ተገልጿል፤ (ዘፀ. 30፥1-10፤ 37፥25-28)።

በነዚህ ክፍሎች እንደ ተገለጸው በተዘረዘሩት መለኪያዎችና መስፈርቶች መሠረት ከግራር ዕንጨት፥ ከቀንድና ከወርቅ የተሠራው የዕጣን መሠዊያ፥ በቅድስት ውስጥ ከቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ለፊት ከሚገኘው መጋረጃ አጠገብ እንዲሆን ታዟል፤ (ዘፀ. 30፥6)።

የዕጣን መሥዋዕት ከላይ በተገለጸው ሁኔታ በተሠራ መሠዊያ ላይ ብቻ የሚቀርብ አልነበረም። በጥና ወይም በማዕጠንት ውስጥም ከመሠዊያው ላይ የተወሰደ የእሳት ፍሕም ተጨምሮበት በካህን አማካይነት ይታጠን ነበር፤ (ዘሌ. 16፥12፤ ዘኍ. 16፥46፤ ዕብ. 9፥4)።

ለመሥዋዕት የሚሆነው ዕጣን የሚቀመምባቸው ነገሮች ጣፋጭ ሽቱ፥ የሚንጠባጠብ ሙጫ፥ ከዛጎል የሚገኝ ሽቱ፥ የሚሸትት ሙጫና ጥሩ ዕጣን ናቸው። እነዚህ ቅመሞች በእኩል መጠን ተወስደው በብልህ ቀማሚ በጨው ይቀመማሉ። ከዚያም እስኪልም ድረስ ተወቅጦ ይዘጋጃል። ይህ ነው እንግዲህ መሥዋዕት ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት ይቀርብ የነበረው ዕጣን (ዘፀ. 30፥34-36፤ ዘሌ. 16፥12)።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ይህን የዕጣን መሥዋዕት እንዲሳያርጉ የተፈቀደው እግዚአብሔር እንዲያገለግሉት መርጦ ለሾማቸው ካህናት ብቻ ነበር። በመሆኑም በቅንአትና በትዕቢት መንፈስ ተነሣሥተው ሳይፈቀድላቸው ጥና ይዘን ካላጠንን ያሉት ቆሬና ልጆቹ፥ የእግዚአብሔር ቁጣ ነድዶባቸው ምድር ተከፍታ ውጣቸዋለች፤ (ዘኍ. 16፥16-35)። በተመሳሳይ ሁኔታም የይሁዳ ንጉሥ ዖዝያን ሳይገባው ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ በማጠኑ ተቀሥፏል፤ (2ዜና. 26፥16-20)።

ዕጣን እንዲያጥኑ የተፈቀደላቸው ካህናትም ቢሆኑ እንደሌላው ሥርዐት ሁሉ ዕጣኑንም በልዩ ጥንቃቄ ማጠን ይገባቸዋል። ይህ ሳይሆን ቢቀርና ከሥርዐቱ ቢያዛንፉ የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ላይም ነድዶ ይቀሠፋሉ። የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ ከዕጣኑ መሠዊያ እሳት ወስደው በጥናው ውስጥ መጨመር ሲገባቸው፥ ያልተፈቀደ ሌላ እሳት ጨምረው ለማጠን በመነሣታቸው እሳት ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥቶ በልቷቸዋል፤ (ዘሌ. 10፥1-2)።



በጥቅሉ ሲታይ ዕጣን በአንድ በኩል ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ የሚችል ጸሎትን የሚያመለክት መሥዋዕት ነው (መዝ. 140(141)፥2፤ ራእ. 5፥8፤ 8፥3-4)።

በብፁዕ አቡነ ሺኖዳ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ተጽፎ፥ በዲያቆን ያየህ ይራድ አስናቀ በተተረጐመውና «አንጻራዊ ትምህርተ መለኮት» በተሰኘው መጽሐፍ ገጽ 132 ላይ፡ - «ዕጣን በራሱ እንደ ጸሎት ይታሰብና ይተረጐም ነበር።» ይላል።

ዕጣን በሌላም በኩል በሕዝቡ በደል ምክንያት ከእግዚአብሔር ዘንድ ለመቅሠፍት የወጣውን ቁጣ ለማብረድና ለማስተስረይ የሚቀርብ የማስተስረያ መሥዋዕትም ሆኖ አገልግሏል፤ (ዘኍ. 16፥46-48)።

## 12.2 ዕጣን በዐዲስ ኪዳን ዘመን

ዕጣን ቁጥሩ ከመሥዋዕት እንደ መሆኑ መጠን፥ ወደፊት በዐዲስ ኪዳን ለሚገለጸው አማናዊ፥ የተወደደና የመዓዛ ሽታ ለሚሆነው መንፈሳዊ ዕጣን ጥላና ምሳሌ ሆኖ በሕገ ኦሪት መሰጠቱን፥ ኦሪትና ወንጌልን ያደበላለቁ ክፍሎች ካልሆኑ በስተቀር ለሁሉም ግልጽ ነው፡፡

ሐዋርያው በዕብራውያን መልእክቱ በኦሪቱ መቅደስ ውስጥ አገልግሎት ይሰጡ ከነበሩት ንዋያተ ቅድሳት መካከል፥ የወርቅ ማዕጠንት እንደ ነበረች ጽፏል፤ (ዕብ. 9፥4)፡፡ በመቀጠልም የወርቅ ማዕጠንቷም ሆነች የተዘረዘሩት ሌሎቹ ንዋያተ ቅድሳት ለዘመነ ኦሪት አገልግሎት ብቻ የተመደቡ በመሆናቸው፥ ዛሬ በክርስትና ዘመን ቀድሞ በነበሩበት ሁኔታም ይሁን አሻሽለን ልንገለገልባቸው ቀርቶ፥ ስለያንዳንዳቸው ትኩረት ሰጥተን የምንናገርበት ወቅት ላይ አለመሆናችንን ገልጿል (ቍ. 5)፡፡ ይህም እንደ ሌሎቹ ጥላና ምሳሌ ነገሮች የዕጣን አገልግሎት ማክተሙን ያመለክታል፡፡

መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትምህርት እንዲህ ቢልም፥ ወንጌልን ይዛ ወደ ፊት መራመድ የሚገባት ቤተ ክርስቲያን የተሰጣትን መንፈሳዊ አገልግሎት ወደ ጎን ጥላ ባልታዘዘችበትና የአገልግሎቱ ዘመን ባበቃበት የኦሪት አገልግሎት ተጠምዳ ትታያለች፡፡

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና፥ መጽሐፍ ቅዱስ በሃይማኖት መሪዎች እጅ ብቻ መገኘቱ ባበቃበትና፥ ምእመናን ሁሉ የማግኘቱ ዕድል ገጥሟቸው መጽሐፍ ቅዱስን ገዝቶ ማንበብና የእግዚአብሔርን ሐሳብ መረዳት በቻሉበት ዘመን ላይ እንገኛለን!

በዚህ ወርቃማ ዘመን ላይ የተገኙ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ምእመናን ታዲያ፥ ቤተ ክርስቲያን በኦሪት ነገሮች መጠላለፏን በመገንዘብ ከኦሪት ጥገኝነት ተላቅቃ፥ በስም ብቻ ሳይሆን በተግባርም ወንጌላዊት እንድትሆን የሚችሉትን ከማድረግ አልተቆጠቡም፡፡ በዚህም ተቃዋሚ አተረፉ እንጂ ተቀባይ አላገኙም፡፡ በዐዲስ ኪዳን ዕጣን የመታጠኑን አላስፈላጊነት ሲናገሩ፥ ይህ ትክክለኛ ሐሣባቸው ይነቀፋል፡፡ ከመነቀፍ ዐልፎ ተርፎም እንደ ኦሪቱ ሁሉ ዕጣን በወንጌል ዘመንም የሚያገለግል መሥዋዕት መሆኑ በአፍም በመጣፍም ይታወጃል፡፡

«አንጻራዊ ትምህርተ መለኮት» የተሰኘው መጽሐፍ፥ ዕጣን በኦሪት የራሱ የሆነ መሠዊያ የነበረውና ራሱን ችሎ የሚቀርብ መሥዋዕት በመሆኑ፥ እንደሌሎቹ የሚቃጠሉ መሥዋዕቶች የተሻረ ሳይሆን፥ ዛሬም በዐዲስ ኪዳን ቀጣይነት ያለው የእምነት ሥርዐት መሆኑን አስፍሯል (ገጽ 132)፡፡

ዕጣን በኦሪት የራሱ የሆነ መሠዊያ የነበረውና ራሱን ችሎ የሚቀርብ መሥዋዕት ስለነበረ፥ እንደ ሌሎቹ አልተሻረም ከተባለ፥ ሌሎቹ የራሳቸው የሆነ መሠዊያ የነበራቸው መሥዋዕቶችስ ለምን ተሻሩ ይባላል?

በእርግጥ ይህ አባባል ዐውቀንም ይሁን ሳናውቅ የዕጣን መሥዋዕት ማቅረብ በቤተ ክርስቲያናችን የቆየ ሥርዐት በመሆኑ፥ ዛሬ ልንለውጠው



አንችልም፤ ወይም አይገባም፤ ከሚል የአልረታ ባይነት መንፈስ የመነጨ አመለካከት ነው እንጂ አሳማኝ እውነትም ሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የለውም፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያቱ፥ በዐዲስ ኪዳን ሥርዐት ውስጥ ዕጣን ስለ ማጠን በቃል ያስተማሩት ትምህርትም ሆነ በተግባር ያሳዩት አርአያነታቸው፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈጽሞ አልተመዘገበም፡፡ የዕጣን ምሳሌነቱ በምን እንደተፈጸመ ግን ያስረዳሉ፡፡

በዘመነ ኦሪት ለእግዚአብሔር የተወደደና ያማረ መዓዛ የሚሆነው የዕጣን ጢስ እንደነበረ ሁሉ፥ በዐዲስ ኪዳን ዘመን ደግሞ የኦሪትን መሥዋዕቶች ሁሉ በመተካት በሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ፥ የቀረበው የራሱ የክርስቶስ መሥዋዕትነት፥ እንደ ዕጣኑ በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ የመዓዛ ሽታ ያለው መሥዋዕት ሆኗል፤ (ኤፌ. 5፥2)፡፡

ምእመናንም ሁለንተናቸውን በመቀደስ የተወደደና መልካም መዓዛ ያለው ሕያው መሥዋዕት ሆነው ለእግዚአብሔር ይቀርባሉ፡፡ መዓዛነታቸውም ለሌላው ተርፎ በሚያምኑት ዘንድ ለእግዚአብሔር የክርስቶስ መዐዛ ይሆናሉ፤ (ሮሜ 12፥1፤ 2ቆሮ. 2፥14፤ ሕዝ. 20፥41)፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በተቀደሰ ሕይወት ሆነው የሚያቀርቡት ሌላው መንፈሳዊ መሥዋዕትም፥ በጌታ ፊት እንደ ዕጣን የመዓዛ ሽታና የተወደደ መሥዋዕት ሆኖ ይቈጠራል፤ (ፊልጵ. 4፥18)፡፡

ለዕጣን እንጂ እንደዚህ ላለው ሕያውና የተወደደ መሥዋዕት ብዙም ግድ የሌላቸው ወገኖች፥ የኦሪቱን ዕጣን መሥዋዕት ዛሬም በቀጣይነት እንዲያገለግል ለማድረግ ሲሉ፥ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሻቸው በመተርጐም የቻሉትን ሁሉ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

ለእንደዚህ ዐይነቱ ተግባራቸው ብዙ ጊዜ የሚጠቅሱት በትንቢተ ሚልክያስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 11 ላይ ያለውን ቃል ነው፡፡ ቃሉ እንዲህ ይላል: - «ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ፥ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና፤ በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ፤ ንጹሕም ቍርባን ያቀርባሉ፤ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤» ፡፡

ለዚህ ቃል በነዚሁ ወገኖች: - «ከክርስትና ውጪ አሕዛብ ሁሉ እግዚአብሔርን ያመለኩበት ዘመን የለም፡፡ ስለዚህ ጌታ ዕጣንን በክርስትና እምነት ሥርዐት ውስጥ አጠቃልሎታል፡፡» የሚል ማስተማመኛ ይሰጠዋል (አንጻራዊ ትምህርተ መለኮት ገጽ 133)፡፡

ትንቢታዊ ቃሉን በዚህ ሁኔታ መተርጐም ብዙ ሊያስኬደን አይችልም፡፡ ምክንያቱም በሌሎቹም የትንቢት ክፍሎች፥ ዕጣንን ጨምሮ ሌሎቹንም የሚቃጠሉ መሥዋዕቶችና ቍርባኖች አሕዛብ ለእግዚአብሔር እንደሚያቀርቡ ተጽፏል፤ (ኢሳ. 56፥7፤ 60፥6)፡፡ በዚህ መሠረት እንግዲህ ዕጣንን ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም የሚቃጠሉ

መሥዋዕቶች ማቅረብ ሊጠበቅባቸው ነው። ታዲያ ይህ ዛሬ ሊፈጸም ይችላልን? ከሌሎቹ መካከል ዕጣን ብቻስ እንዲቀርብ ለምን አስፈለገ?

በመሠረቱ «ከክርስትና ውጪ አሕዛብ ሁሉ እግዚአብሔርን ያመለኩበት ዘመን የለም።» የሚለው አባባል፥ የዕጣንን መሥዋዕት ዛሬም ለማቅረብ ታስቦ የተሰጠ ትርጉም ካልሆነ በቀር፥ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን ትክክለኛ አይደለም።

ዛሬ አስቀድሞ ለአይሁድ ብቻ የነበረው የተስፋው ቃል በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ለአሕዛብም በመድረሱ፥ ፈቃደኛ የሆኑና ለዘላለም ሕይወት የተዘጋጁ ሁሉ በእምነት በኩል የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆነው መቈጠራቸው እውነት ነው። ከዚህ የተነሣም እግዚአብሔርን ማምለክ ችለዋል። ይህ ግን አሕዛብ ሁሉ አመለኩ አያሰኝም።

ወደ መጀመሪያው ሁኔታ ተመልሰን ከተመለከትን ደግሞ፥ አምልኮተ እግዚአብሔር አስቀድሞ አሕዛብ ለሆኑት ተከልክሏል። በአይሁድ ሕዝብ መካከል ለመኖር የመጡ አሕዛብ እንኳ፥ በአምልኮተ እግዚአብሔር ለመሳተፍ የሚችሉት ቢያንስ ሦስትና አራት ትውልድ ካለፈ በኋላ ነበር፤ (ዘፀ. 12፥43፤ 45፤ ዘዳ. 23፥3፤ 7-8)።

ይሁን እንጂ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ባለው ዘመን፥ የክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት ይህን ሁኔታ የሚለውጠው መሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረ ዘላለማዊ ዕቅድ በመሆኑ፥ ወደ እግዚአብሔር መጠጋት ለሚሹ አሕዛብ፥ መጻተኞችና ጃንደረቦች የተዘጋው በር በዚያው በኦሪቱ ዘመን መከፈት ጀመረ፤ ከእስራኤላውያን ጋርም እግዚአብሔርን የማምለክ መብት ተሰጣቸው፤ (ኢሳ. 56፥1-6፤ 14፥1)።

ስለሆነም አሕዛብ በዐዲስ ኪዳን ዘመን ብቻ ሳይሆን፥ በብሉይ ኪዳን ዘመንም በተከፈተላቸው በዚህ በር እግዚአብሔርን ከማምለክ ስላልተከለከሉ፥ መሥዋዕት እየሠዉ ያመልኩት ነበር። የትንቢተ ሚልክያስ ትንቢትም በዚሁ መሠረት የሚታይ ይሆናል። አሊያም አሕዛብ እንደ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን የሚያመልኩበትና ወደ እርሱ የሚጸልዩበት ይህ ያለንበት ዘመን እንደሚመጣ የሚያመለክት ትንቢት ሊሆን ይችላል።

ዕጣን ስለማጠን ሌላ ማስረጃ ብለው የሚጠቅሱት ደግሞ፥ ጌታ በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል አምኀ ይሆን ዘንድ ዕጣን መስጠታቸውን ነው፤ (ማቴ. 2፥11)። ነገር ግን ሰብአ ሰገል በስጦታ መልክ ዕጣን ማምጣታቸው፥ ዕጣን ዛሬ በቤተ ክርስቲያን እንዲታጠን የተፈቀደ መሆኑን ሊያመለክት አይችልም።

በሌላ በኩል ዕጣኑን የሰጡት ስለ ክህነቱ እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ቢናገሩም እንኳ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በሊቀ ካህንነቱ ራሱን ብቻ መልካም መዓዛ ያለው የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ እንጂ፥ ዕጣን ፈጽሞ አላሳረገም፤ (ኤፌ. 5፥2)።

እግሯ ወንጌል ላይ የቆመ ቢመስልም ልቧን ግን ከኦሪት ጋር ያደረገችው ቤተ ክርስቲያናችን፥ በአንድ በኩል አማናዊው ዕጣን ክርስቶስ



መሆኑን ከማወጅ ወደ ኋላ ያለችበት ጊዜ የለም። መጽሐፈ ቅዳሴ እንዲህ ይላል፡ -

«አንቲ ውእቱ ማዕጠንት ዘወርቅ እንተ ጾርኪ ፍሕመ እሳት፤ ቡሩክ ዘነሥአ እመቅደስ ዘይሰሪ ኀጢአተ ወይደመስስ ጌጋየ፤ ዝ ውእቱ ዘእግዚአብሔር ቃል ዘተሰብአ እምኔኪ፤ ዘአዕረገ ለአቡሁ ርእሶ፤ ዕጣነ ወመሥዋዕተ ሥሙረ።»

ትርጓሜ፡ - «ቡሩክ ከቤተ መቅደስ የወሰዳት፥ የእሳት ፍሕምን የተሸከምሽ የወርቅ ጥና አንቺ ነሽ፤ ራሱን ለአባቱ የተወደደ መሥዋዕትና ዕጣን አድርጎ ያሳረገውም፥ ኀጢአትን የሚሰርይ፥ በደልንም የሚያጠፋ፥ ይኸውም ካንቺ ሰው የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ነው።» (ሥርዐተ ቅዳሴ ቍ. 122)።

እንዲሁም፡ - «ዕጣን አ! መድኃኒነ እስመ መጻእከ ወአድኀንከነ ተሣሃለነ።»

ትርጓሜ፡ - «መድኃኒታችን ሆይ! ዕጣን አንተ ነህ፤ መጥተህ አድነኸናልና ይቅር በለን።» (ቍጥር 172)።

ቤተ ክርስቲያናችን በአንደበቷ እንዲህ ባለ ምሳሌ እውነቱን ብትገልጽም፥ «መጥተህ አድነኸኛል» በማለት የመሰከረችለትን የክርስቶስን መዓዛ ዕጣንነት በእምነት ማሽተት ትታ፥ ዛሬም እንደ ዘመነ ኦሪት ዕጣን እያጠነች መገኘቷ ያስገርማል! ያሳዝናልም!

# ክፍል 13 - የመንጻት ሥርዐት

## 13.1 የመንጻት ሥርዐት በብሉይ ኪዳን

የኦሪት ሕግ ሲሰጥ፥ ሰው በኀጢአተኝነት የሚከሰሰው የትኛውን ሕግ ሲጥስ እንደሆነና፥ ከሶ የሞት ፍርድ ሊያስፈርድበት ከተዘጋጀው ኀጢአትም ነጻ ለመውጣት እንዴት ያለ መሥዋዕት እንደሚያቀርብ፥ በተለይ በኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ ውስጥ በስፋት ተገልጿል።

ዐሠርቱ ቃላትን ከመተላለፍ ውጪም በአፍኣዊ ሥርዐቶች ላይ የሚያተኩሩትን ሌሎቹን የሕዝቡን መተዳደሪያ ሕጎች፥ እያንዳንዱ እስራኤላዊ ዐውቆም ይሁን ሳያውቅ፥ ወይም ደግሞ አስገዳጅ ሁኔታ ተፈጥሮ ጥሶ ቢገኝ እንደ ርኩስ ይቈጠራል። ሴት ስትወልድ (ዘሌ. 12)፥ ሰው በገላው ላይ ተላላፊ የቆዳ በሽታ ወይም ለምጽ ሲወጣበት፥ እንዲሁም በልብሱ ላይ ተመሳሳይ የተላላፊ በሽታ ምልክት ሲታይበት (ዘሌ. 13-14)፥ በሕመም ምክንያት የተለያየ ፈሳሽና ዘር ጭምር ከሰውነቱ ቢፈስስ (ዘሌ. 15፥1-18)፥ በሌሎችም ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሁሉ በኦሪት ሕግ መሠረት ርኩሳን ናቸው።

ሌላው ቀርቶ ከእነርሱ ጋር ንክኪ ያለው መገልገያ ዕቃም ይሁን ሰው፥ በሕጉ መሠረት ርኩሳን ናቸው። የሞተን ሰው በድን፥ ከሞተ የቆየውን ሰው ዐፅም ወይም መቃብር የነካም ቢሆን ርኩስ ነው፤ (ዘኍ. 19፥11-16)።

በዚህ መንገድ የረከሰ አይሁዳዊ፥ ከርኩሰቱ የሚነጻው በሕጉ እንደተጻፈው፥ ለተወሰነው ጊዜ ገለልተኛ በመሆን፥ በውሃ በመታጠብ የሚከናወነውን የመንጻት ሥርዐት በመፈጸምና፥ መሥዋዕት ማቅረብ ለሚጠይቁትም ርኩሰቶች መሥዋዕት በማቅረብ ይሆናል። በተለይ ግን ከርኩሰት የመንጻት ሥርዐትን በተመለከተ በዘኍልቍ ምዕራፍ 19 ውስጥ የተደነገገውን የመንጻት ሕግ እናገኛለን።

ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ለመቅረብ የሚፈልግ ሁሉ ለእግዚአብሔር ቅድስና ተቃራኒ ከሆነ ርኩስ ነገር ሁሉ ራሱን ሊጠብቅ ይገባዋል።

በኦሪት ሕግ መሠረት ከላይ በተዘረዘሩት ርኩሰቶች ውስጥ፥ የሚገኝ ማንኛውም እስራኤላዊ እግዚአብሔርን ለማምለክ መቅረብ አይችልም። ስለዚህ ለመቅረብ ርኩሰቱ የሚነጻበትን የመንጻት ሥርዐት መፈጸም የግድ ይኖርበታል።

ለዚህ የመንጻት ሥርዐት እንከንና ነውር አልባ የሆነችና ቀንበር ተጭኖባት የማያውቅ ቀይ ጊደር ለመሥዋዕት ትቀርብ ነበር። በሥርዐቱ መሠረት ይህች ቀይ ጊደር ከሰፈር ውጭ ታርዳ እንድትቃጠል ከተደረገ በኋላ፥ ዐመዷ ታፍሶ ከሚያነጻው የምንጭ ውሃ ጋር ይበጠበጥና የረከሱ ሰዎችን ለማንጻት ይውላል፤ (ዘኍ. 19፥1-10፤ 17)። በዚህ መሠረት እንግዲህ የነጻ እስራኤላዊ ሁሉ የተቀደሰ ስለሚሆን እግዚአብሔርን ለማምለክ መቅረብ፥ መሥዋዕቶችንም መሠዋት ይችላል።



## 13.2 የመንጻት ሥርዐት በዐዲስ ኪዳን

ቀድሞ የነበረው የኦሪቱ የመንጻት ሥርዐት አፍኣዊ እድፍን በማንጻት የሚከናወን ውጫዊ ሥርዐት ብቻ ነበር። በመሆኑም ሥርዐቱን የፈጸመውን ሰው ውጫዊ ነገር ብቻ እንጂ፥ ኅሊናውን በማንጻት ከኀጢአት ክስ ነጻ የሆነ አምልኮ ለእግዚአብሔር እንዲያቀርብ አያስችለውም።

እንዲህ ያለው የመንጻት ሥርዐት፥ ነገሮች ሁሉ እስከሚታደሱበት እስከ ክርስቶስ ዘመን ድረስ ብቻ እንዲያገለግል የተሰጠ የሥጋ ሥርዐት ብቻ ነው፤ (ዕብ. 9፥9-10)።

አስቀድሞ በመያዝ፥ በመንካትና በመቅመስ መርከስ ነበር። ዛሬ በዐዲስ ኪዳን ግን እነዚህ አትያዝ፥ አትንካ፥ አትቅመስ የሚሉት ትእዛዛት በፈጸማቸው ሰው ላይ ርኩሰትን ሊያመጡ የማይችሉና፥ በመደረግም ሊጠፉ ወይም ሊሻሩ የተወሰኑ ናቸው፤ (ቈላ. 2፥22)።

የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የኦሪቱን የማንጻት ሥርዐት ደካማነት በዚህ ሁኔታ ስለሚያብራሩ፥ ያ ሥርዐት በዐዲስ ኪዳን ዳግም እንደማያገለግል የታመነ ነው። ስለሆነም ለክርስቲያኖች በምትኩ እጅግ የተሻለና ሥጋን ብቻ ሳይሆን ኅሊናን ጭምር ማንጻት የሚቻለው ሌላ መንፈሳዊ የማንጻት ሥርዐት ይኖራቸው ዘንድ ተገቢ ሆኗል።

የኦሪቱ የማንጻት ሥርዐት በዐዲስ ኪዳን ለሚገለጠው መንፈሳዊ የመንጻት ሥርዐት ጥላና ምሳሌ ነውና (ዕብ. 9፥9-10)፥ የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቀድሞውን አሳልፎ ዐዲሱን መንፈሳዊ ሥርዐት አቁሞልናል። ይህም አንድ ጊዜ በመሞት ባፈሰሰው ክቡር ደሙ አማካይነት በእምነት የሚከናወን መንፈሳዊ የመንጻት ሥርዐት ነው፤ (ሮሜ 3፥25፤ ዕብ. 9፥14፤ 1ዮሐ. 1፥7)።

የዚሁ መንፈሳዊ የመንጻት ሥርዐት አካል የሆኑት ሌሎቹ ደግሞ፥ የእግዚአብሔር ቃልና በዐይን በማይታይ ሁኔታ፥ በእምነት ብቻ የተከናወነውን ከኀጢአት የመታጠብና ዳግም የመወለድን መንፈስ የምንመሰክርበት የጥምቀት ውሃ ናቸው።

የእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለሕይወታችን ሲብራራልን፥ ኀጢአተኝነታችንን በማሳየት ወደ ንስሓ ውሳኔ አምጥቶና ውስጣችንን ዐጥቦ ያጠራል፤ (ዮሐ. 15፥3፤ ኤፌ. 5፥26፤ 1ጴጥ. 1፥23)።

በእምነት ያገኘነውንና የልብ ለውጥ የሆነውን ዳግም ልደት፥ በውሃ በመጠመቅ ሥርዐት እንመሰክራለን። ይህም ማለት በክርስቶስ ሥራ የተከናወነልንንና በእምነታችን መሠረት ለያንዳንዳችን የሚቈጠርልንን ከኀጢአት ታጥቦ የመንጻትን ሥርዐት ሁሉ ያጠቃልላል ማለት ነው። እንዲህ ዐይነቱ የዐዲስ ኪዳን የመንጻት ሥርዐት ለአንዳንዶች እንደሚመስላቸው አፍኣዊ ርስሐትን (እድፍን)

ከማንጻት ጋር ተያያዥነት የለውም፤ ውስጥን ከማጠብና ከማንጻት ጋር ግን የበለጠ ትስስር ያለው ሥርዐት ነው፤ (ዮሐ. 3÷5፤ የሐዋ. ሥራ 22÷16፤ ኤፌ. 5÷26፤ ቲቶ 3÷5፤ 1ጴጥ. 3÷21)።

መቼም ውሃ በመረጨትና በውሃ በመታጠብ ውጫዊ ሰውነት ካልሆነ በቀር፥ ልባችን ከክፉ ኅሊና ሊነጻ ከቶ አይችልም። በኦሪቱ የመንጻት ሥርዐት ሥጋን እንጂ ኅሊናን ማንጻት እንዳልተቻለ የታወቀ የተረዳ ነውና፤ (ዕብ. 9÷13)።

ስለዚህ ዛሬ ልባችንን ተረጭተንና ሰውነታችንን ሁሉ ከኀጢአት እድፍ ታጥበን የምንቀርብበት ውሃ፥ በሚታየው ፈሳሽ ውሃ ሊተካ የማይቻል ነው። ምናልባት የሚታየው ውሃ በምሳሌነት ሊያብራራው ይችላል፤ (ዕብ. 10÷22)።

ይሁን እንጂ ነጻነታችን የሆነ ወንጌልን አስጥለው እንደ ገና ወደ ባርነት ሊመልሱን የሚፈልጉ ወገኖች (ገላ. 5÷1)፥ ከኦሪት የቀዱትንና እነርሱም በዐዲስ መልክ የደነገጉትን የሥጋ ሥርዐት መተላለፍ ያረክሳል በማለት፥ ልባችንን ሳይሆን ሥጋችንን ውሃ ይረጫሉ። በዚህ ሥርዐት ታዲያ ሥጋችን እንጂ ሕያው እግዚአብሔርን እናመልክ ዘንድ ኅሊናችን አልነጻም።

ከኦሪት ከተወሰዱት የሥጋ ሥርዐቶች መካከል የወሊድን ሕግ የሚመለከተው አንዱ ነው። በአሁኑ ጊዜ እንዳለው የቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ መሠረት፥ ሴት ልጅ በወለደች ጊዜ እንደረከሰች ያህል ትቈጠራለች። ቄሱ መጥቶ በሥርዐቱ መሠረት የማንጻቱን ጸበል ከመርጨቱ አስቀድሞ፥ ሊጠይቋት እርሷ ወዳለችበት ክፍል የገቡም ሁሉ እንደ ረከሱ ስለሚቈጠሩ ጸበል በመረጨት መንጻት ይኖርባቸዋል።

ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ ነገሩን አሻሽለው በማቅረብ፥ እንደረከሱ የሚቈጠሩት እሷና በማዋለድ ጊዜ ከአራስነት ደሟ ጋር ንክኪ ያላቸው ናቸው ይላሉ። በዚህም ተባለ በዚያ በወሊድ ጊዜ መርከስ እንዳለ ስለሚሰበክና ስለሚታመንም፥ በሚያነጻው ጸበል ውሃ ካልተረጨ በቀር ወደ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን መግባት ይከለከላል።

ሌላው በቤተ ክርስቲያናችን የሚታየው ኦሪታዊ የሥጋ ሥርዐት የሚበሉና የማይበሉ እንስሳት ጉዳይ ነው። በዐፄ ገላውዴዎስ የሃይማኖት ውሳኔ መሠረት ማንኛውንም መብል የመብላትም ሆነ ያለመብላት ጉዳይ፥ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ እንጂ ከሕግ አንጻር የተወሰነ አይደለም። የሃይማኖት ውሳኔው እንዲህ ቢልም ማን ተመልክቶት! ስለዚህ በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 11 ላይ በታዘዘው መሠረት ከተከለከሉት እንስሳት መካከል በማወቅም ይሁን ባለማወቅ፥ ወይም በሁኔታዎች አስገዳጅነት አንድ ሰው ቢበላ፥ እንደ ረከሰ ስለሚቈጠር ወደ ቄስ መጥቶ መጽሐፈ ቄደር የተደገመበት ዐመድ በውሃ ተበጥብጦ እንዲነከርና እንዲነጻ ይደረጋል።

በሌላም በኩል የጾም ምንነት ትርጉሙ ስለተዛባ፥ ጾም ቤተ ክርስቲያናችን ባወጣችው የራሷ ቀኖና መሠረት ሲፈጸም የሚያጸድቅ፥ ሲጣስ ደግሞ የሚያስኰንን ሕግ ሆኖ መታየት ከጀመረ ዘመናት ተቈጥረዋል።



በቅዱስ መጽሐፍ እንደተገለጸው ጾም ምእመናን ሁሉ በማኅበርም ሆነ በግላቸው ራሳቸውን በማዋረድ የፈጣሪያቸውን ፊት የሚፈልጉበትና ሊፈጽሙት የሚገባ የአምልኮአቸው ክፍል ነው።

ከጥቂቶች ምእመናን በቀር ግን በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ፥ ጾም ከተወሰኑ የምግብ ዐይነቶች (ጥሉላት) የመከልከል ተግባር ሆኗል፤ ነገር ግን ምግብን ከመተው ጋር ራስን በማዋረድ የአምላክን ፊት በትሕትና የመፈለጉ ጉዳይ ትኩረትና ቅድሚያ ቢሰጠው የቤተ ክርስቲያናችን የጾም ሥርዐት መልካም ነበር፤ ነገር ግን ይህ ሊሆን አልቻለም። በመሆኑም በተወሰኑት የጾም ወቅቶች እንዳይበሉ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ከተከለከሉት የጥሉላት ምግቦች፥ ዐውቆም ይሁን ተሳስቶ የበላ ማንኛውም እንደረከሰና ከባድ ኀጢአት እንደሠራ ራሱን ይቈጥራል። ክርኵሰቱ ለመንጻትም ይህን ኀጢአቱን ለንስሓ አባቱ ተናዝዞ ጸበል በመረጨት የመንጻት ሥርዐት ይፈጸምለታል።

ይህ ሁሉ የሚያሳየው ቤተ ክርስቲያናችን በክርስትና ዘመን ላይ ያለች ቢሆንም፥ እየፈጸመች ያለው ተግባር ግን ኦሪታዊ መሆኑን ነው። ክርስቶስ በቤዛነቱ እንደነዚህ ካሉትና፥ ለጽድቅ ቀድሞውንም ምንም ጥቅም ከሌላቸው የሥጋ ሥርዐቶች የዋጃት ብትሆንም፥ ከሕግ እርግማን እንዳልተዋጀች በመሆን በኦሪት የባርነት ቀንበር ውስጥ ያለች ትመስላለች፤ (ገላ. 3÷11-13)።

ስለሆነም ከወንጌል ወደ ኦሪት ተመልሰው ለነበሩት፥ የገላትያ አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን የተላለፈው የነጻነት ወንጌል፥ ዛሬም በኦሪት የባርነት ቀንበር ውስጥ ለሚማቅቁ ወገኖች ተደጋግሞ ሊስተጋባላቸው ይገባል።

«በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ! እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።» (ገላ. 5÷1)።

# ክፍል 14 - በዓላት

## 14.1 በዓላት በብሉይ ኪዳን ዘመን

ሕዝበ እስራኤል ከግብጽ ወጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመግባቱ አስቀድሞ÷ ከግብጻውያን የአኗኗር ዘይቤ ነጻ በመሆን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በተዘጋጀለት ዐዲስ አኗኗር ይኖር ዘንድ አስፈላጊው ነበር:: ስለዚህ ሕዝቡ በምድረ በዳ በጉዞ ላይ ሳሉ÷ እግዚአብሔር በተለያየ ፈተና እየፈተነ የሕዝቡን ሕይወት ለዐዲሱ ኑሮ ማዘጋጀቱን ቀጠለ፤ (ዘፀ. 16÷4፤ ዘዳ. 8÷2፤ ዕብ. 3÷8-9)::

ከፈተናው ባሻገር ለእግዚአብሔር ለመገዛት÷ እርሱንም ብቻ ለማምለክ የሚያስችሉ ሕግና ሥርዐቶችን በመስጠት ያ ሕዝብ የእርሱ ብቻ መሆኑን አመለከተ::

እግዚአብሔር ለዚያ ሕዝብ ያደረገውንና ወደፊትም የሚያደርገውን አስደናቂ የሆነ የፍቅርና የቸርነት ሥራ በማሰብ እንዲያመልኩት የሚያደርጉ በዓላትን ሠርቷል:: በዓላቱ የተቀደሱ ጉባኤዎች ሲሆኑ÷ የእግዚአብሔር በዓላትም ተብለው ተሰይመዋል:: እስራኤላውያንም በዘመናቸው ሁሉ ሲያከብሩ የኖሩት የእግዚአብሔርን በዓላት ነው፤ (ዘሌ. 23÷2፤ 4፤ 37፤ 44፤ ሕዝ. 44÷24)::

እነዚህን በዓላት የሚከበሩበትን ምክንያትና እስራኤላውያን በዓላቱን በማክበር እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚያመልኩት ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው:: በተለይም ለኛ ለኦርቶዶክሳውያን አስፈላጊነቱ የላቀ ነው:: ስለምናከብራቸው አያሌ በዓላት ቆም ብለን እንድናስብ ያደርገናልና:: ስለሆነም ለእስራኤላውያን ስለተሰጡት በዓላትና ስለሚከበሩበት ምክንያት ቀጥሎ በዐጭሩ እንመልከት: -

1. **ሰንበት** - ሰው የእግዚአብሔርን የፈጣሪነት ሥራ አስታውሶ÷ የእርሱን አርአያ በመከተል እንዲያርፍ የተሠራ በዓል ነው:: በዚህም መሠረት ሰውና እንስሳት ከስድስት ተከታታይ ቀናት በኋላ በሰባተኛው ቀን ያርፋሉ:: ጌታ ሕዝቡን የሚቀድስ ለመሆኑ በእርሱና በሕዝቡ መካከል ሰንበት የቃል ኪዳን ምልክት ሆኖ ተሰጥቷል፤ (ዘፍ. 2÷1-3፤ ዘፀ. 20÷8-11፤ 31÷12-17፤ ዘሌ. 23÷3፤ ዘዳ. 5÷12-15፤ ኢሳ. 56÷2-4፤ 58÷13-14፤ ማቴ. 12÷1-8፤ ቈላ. 2÷16፤ ዕብ. 4÷1-11)::
2. **ፋሲካ** - እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት ነጻ መውጣታቸውን ለማሰብ ነው፤ (ዘፀ. 12÷1-14፤ ዘሌ. 23÷5፤ ዘኍ. 9÷1-14፤ 28÷16፤ ዘዳ. 16÷1-7፤ ማቴ. 26÷17፤ ማር. 14÷1፤ 12-26፤ ዮሐ. 2÷13፤ 11÷55፤ 1ቆሮ. 5÷7)::
3. **የቂጣ በዓል (በዓለ ናእት)** - ከፋሲካ በዓል ጋር ተያይዞ የሚከበር በዓል ሲሆን÷ የሚከበረውም እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከምድረ ግብጽ እያስቸኰለ ማስወጣቱን ለማሰብ ነው፤ (ዘፀ. 12÷15-20፤ 13÷3-10፤ 23÷15፤ 34÷18፤ ዘሌ. 23÷6-8፤ ዘኍ. 28÷17-25፤ ዘዳ. 16÷34፤ 8፤ ማር. 14÷1፤ የሐዋ. ሥራ 12÷3፤ 1ቆሮ. 5÷6-8)::



4. **የመከር በዓል (በዓለ ሠዊት) ወይም በዓለ ኀምሳ** - ስለ ተሰበሰበው መከርና ስለተገኘው ምርት ደስ በመሰኘት እግዚአብሔርን ለማመስገን ይከበራል፤ (ዘፀ. 23÷16፤ 34÷22፤ ዘሌ. 23÷15-21፤ ዘኍ. 28÷26፤ 31፤ ዘዳ. 16÷9-12፤ የሐዋ. ሥራ 2÷1-4፤ 20÷16፤ 1ቆሮ. 16÷8)::
5. **የዳስ በዓል (በዓለ መጸለት)** - እስራኤላውያን እህላቸውን ሰብስበው ካከማቹ በኋላ÷ ከቤታቸው ወጥተው÷ ዳስ ሠርተው÷ በመቀመጥ ከግብጽ ወደ ከነዓን ባደረጉት ጉዞ በምድረ በዳ ውስጥ መቀመጣቸውንና በዚያም እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ጥበቃና እንክብካቤ እያሰቡ እግዚአብሔርን ለማመስገን የሚያከብሩት በዓል ነው፤ (ዘፀ. 23÷16፤ 34÷22፤ ዘሌ. 23÷33-36፤ 39-43፤ ዘኍ. 29÷12-34፤ ዘዳ. 16÷13-15፤ ነህ. 8÷14-18፤ ዘካ. 14÷16-19፤ ዮሐ. 7÷2፤37)::
6. **የመለከት በዓል** - እግዚአብሔር ያደረገውን ቸርነት በማሰብ እስራኤላውያንን ወደፊቱ ለማቅረብ ሲባል የሚከበር በዓል ነው፤ (ዘሌ. 23÷23-25፤ ዘኍ. 29÷7-11)::
7. **የማስተስረያ በዓል** - ካህናቱና ሕዝቡ ራሳቸውን አዋርደው ኀጢአታቸውን በመናዘዝና በመሥዋዕቱ ደም በማንጻት የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለመለመን የሚከበር ቀን ነው፤ (ዘሌ. 16፤ 23÷26-32፤ ዘኍ. 29÷7-11፤ ሮሜ 3÷24-26፤ ዕብ. 9÷7፤ 10÷3፤ 19-22)::
8. **ፉሪም** - በአስቴር ዘመን ለእስራኤላውያን የተደረገላቸውን ትድግናና የኀዘናቸውን ወደ ደስታ መለወጥ ለማሰብ÷ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሚከበር በዓል ነው፤ (አስ. 9÷18-32)::
9. **የመቅደስ መታደስ በዓል** - በመቃብያን ዘመን መከበር የተጀመረ በዓል ሲሆን÷ አንጥያኮስ ቤተ መቅደሱን ካረከሰ በኋላ እንደ ገና መቀደሱን ለማሰብ የሚከበር በዓል ነው፤ (ዮሐ. 10÷22)::
10. **የበኵራት በዓል** - በዕርሾች ላይ እግዚአብሔር የሰጠውን በረከት ለማሰብ የሚከበር በዓል ነው፤ (ዘሌ. 23÷9-14፤ ሮሜ 8÷23፤ 1ቆሮ.15÷20-23)::
11. **የሰባተኛ ዓመት በዓል** - ከስድስት የሥራ ዓመታት በኋላ በሰባተኛው ዓመት ራስን ጨምሮ÷ በገንዘብ የተገዙ ባሮችንና የተቀጠሩ አገልጋዮችን÷ እንዲሁም ምድሪቱን ዕርሻ ከማረስ÷ ምርትን ከመሰብሰብ ለማሳረፍ የሚከበር በዓል ነው፤ (ዘፀ. 23÷10-11፤ ዘሌ. 25÷1-7)::
12. **የኢዮቤልዩ በዓል** - ከሰባት ጊዜ ሰባት ዓመት በኋላ በ50ኛው ዓመት ዕዳን በመሠረዝ÷ ባሮችና ቅጥር ሠራተኞችን ነጻ

በማውጣት÷ ርስት ለተያዘባቸው ሰዎች በመመለስ ድኾችንና የተጠቁ ሰዎችን ለመርዳት ሲባል የሚከበር በዓል ነው፤ (ዘሌ. 25÷8-55፤ 27÷17-24፤ ዘኍ. 36÷4)::

ከእነዚህ በዓላት በተጨማሪም «መባቻ» በመባል የሚታወቀውንና በወር መጀመሪያ ቀን የሚከበረውን በዓል እናገኛለን (ዘኍ. 10÷10፤ 1ዜና. 23÷31፤ ዕዝ. 3÷5፤ ነህ. 10÷33፤ መዝ. 80(81)÷3፤ ኢሳ. 1÷13-14፤ 66÷33፤ ቈላ. 2÷16)::

በጥቅሉ ስንመለከት እነዚህ በዓላት እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ባለው ታሪክ ለእነርሱ ያሳየው ምሕረትና ቸርነት÷ የሰጣቸው በረከት÷ ያደረገላቸው ጥበቃና እንክብካቤ ሁሉ በሕዝበ እስራኤል ዘንድ ታውቆ እርሱ እንዲመለክበት የተሰጡ እግዚአብሔር በዓላት ናቸው::

ስለ በዓላቱ መከበር በተሰጠው ሕግ ውስጥ÷ በዓሉን ሲያከብሩ እግዚአብሔርን እንዴት ባለ ሁኔታ ሊያመልኩ እንደሚገባ የሥርዐቱ አፈጻጸም ሁሉ÷ ካለይ በተገለጹት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች ውስጥ ተዘርዝሯል::

እነዚህ በዓላት ለአይሁድ ሕዝብ ብቻ የተሰጡ ነበሩ፤ ምክንያቱም በዓላቱ እንዲከበሩ ያስገደዱት መነሾዎች በዚያ ሕዝብ ሕይወት ውስጥ ብቻ ተከናውነው ያለፉና÷ ለወደፊቱም የሚከናወኑ አምላካዊ ሥራዎች በመሆናቸው ነው::

ከበዓላተ አይሁድ መካከል አንደኛውም ቢሆን በዐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ዘንድ እንዲከበር ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትእዛዝ የለም:: ካላይ ስለ በዓላቱ ከሚናገሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል÷ በተለይ ከዐዲስ ኪዳን ክፍል የተጠቀሱት አንዳንዶቹ÷ ያ የቀድሞው የአይሁድ በዓል በክርስትና ዘመን ሌላ መንፈሳዊና ሰማያዊ ትርጉም ተሰጥቶት እናገኛለን:: ይህም በዓላቱ ለሚመጣው አካል ጥላ የነበሩ መሆኑን አስረጂ ነው፤ (ቈላ. 2÷17)::

በታሪክ ሂደት ዘመናት እየጨመሩ÷ ትውልድም በሌላ ዐዲስ ትውልድ እየተተካ በሄደ ቁጥር÷ ሁኔታዎችም በዚያው መጠን ይለዋወጣሉ:: ከመነሻው የነበሩ ነገሮች ቅርጻቸው እየተቀያየረ÷ ስማቸው ብቻ ለመቅረት የሚገደድበት አጋጣሚም ብዙ ነው::

ይህ በተለይ በአይሁድ ታሪክ ውስጥ የታየ ክሥተት ነው:: በክርስቶስ ዘመን የነበሩትን አይሁድና የሰንበት አከባበር ሁኔታቸውን ብንመለከት እንኳ ለአባባላችን በቂ ምስክር ሊሆነን ይችላል::

በዘመኑ የነበሩት አይሁድ ሰንበትን ያከብሩ የነበረው÷ በሙሴ አማካይነት ከእግዚአብሔር በተቀበሉት ሥርዐት መሠረት ሳይሆን÷ የራሳቸውን ብዙ ወግና ሥርዐት ጨምረውበት ነው:: ለምሳሌ: - በሰንበት እሸት እንዳይቀጠፍ÷ ድዉይ እንዳይፈወስ የሚከለክል ብዙ ወግ ነበራቸው:: የሚጨነቁትም ለእግዚአብሔር ሕግ መከበር አልነበረም፤ ቀንን ብቻ በማክበር ላይ ለተመሠረተው ለራሳቸው ወግና ሥርዐት ብቻ ነበር እንጂ::



ከጌታ ጋርም ብዙ ጊዜ ያጣላቸው የነበረው ይኸው የእግዚአብሔርን ሕግ ለማስከበር ያልቆመው ወጋቸው ነው::

በመሠረቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አይሁድ ይከስሱት እንደ ነበረው ሰንበትን አልሻረም:: ሰንበትን መከበር በሚገባው ሁኔታ አከብሯል፤ (ሉቃ. 4÷16፤ 6÷6፤ 13÷10)::

እርሱ የተቃወመው በሰው ወግና ሥርዐት ተተብትቦ የነበረውንና በሰንበት መልካም ነገር ከማድረግ የሚከለክለውን የፈሪሳውያንን የአከባበር ወግና ሥርዐት ነው፤ (ማቴ. 12÷1-8፤ ሉቃ. 6÷6-11፤ 13÷10-17፤ 14÷1-6፤ ዮሐ. 5÷5-16)::

አይሁድ ሰንበትን እንዲያከብሩ ከእግዚአብሔር የታዘዙ ቢሆንም ጥፋት የሆነባቸው የራሳቸውን ወግና ሥርዐት ጨምረው እናክብር ማለታቸው ነው:: በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር የሚፈልግባቸውን ዋና ነገር ሊያደርጉ ካለመቻላቸውም በላይ የራሳቸው ወግና ሥርዐት ለብዙ ጉዳት ዳርጓቸዋል::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል: -

> «ስለ ቀዳም ሰንበት ክብር የአይሁድ ሊቃውንት ብዙ ዐይነት አተረጓጐም ነበራቸው:: «አክብር» የሚለውንም ቃል ለእግዚአብሔር እንደሚስማማ አድርገው ለመተርጐም ያላዩት መዝገበ ቃላት የለም:: ካህናቱም ሆኑ ሕዝቡ በዚህች በዕለተ ሰንበት ሥር መማስ÷ ቅጠል መበጠስ ይቅርና የዘሩትንም አያጥፉም፤ ያጠፉትንም አይዘረጉም፤ የዘጉትን አይከፍቱም፤ የከፈቱትንም አይዘጉም ነበር:: ዜና አይሁድን የጻፈው ራሱም አይሁዳዊ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን: - "አይሁድ በዕለተ ሰንበት ወደ ሽንት ቤት እንኳ አይሄዱም ነበር::" ብሏል:: ከዚህም ጋር ቤት ቢቃጠል÷ ሰው ቢሞት÷ ጦር ቢመጣ በዕለተ ሰንበት ከሆነ መንቀሳቀስ ክልክል ነው:: ለምሳሌ: - በመቃብያን ታሪክ እንደሚታወቀው 36 ሺህ አይሁዳውያን በወራሪ ጦር በአንድ ቀን ያለቁት÷ በዚህች በዕለተ ሰንበት ነበር:: 1966 ዓ.ም (በፈረንጆቹ በ1973) ግብጻውያን ያጠቋቸው በበዓሉ ምክንያት ተዘልለው ሳሉ ነው::» (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 122-123)::

## 14.2 በዓላት በዐዲስ ኪዳን

ስለ በዓላትና አከባበራቸው በዐዲስ ኪዳን ዘመን በጌታም ሆነ በደቀ መዛሙርቱ የተሰጠ ትእዛዝ ስለመኖሩ መጽሐፍ ቅዱስ፥ በተለይም የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የሚናገሩት የለም። ክርስቲያኖች የአይሁድን በዓላት ያክብሩ የሚል ግዴታም አልተላለፈም። ይልቁንም እንዲህ ያለ አስገዳጅ ሁኔታ በክርስቲያኖች ላይ እንዳይኖር የሚከለክል መመሪያ ተሰጥቷል።

«እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ፤ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፤ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው።» (ቈላ. 2፥16-17)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው በአይሁድ ዘንድ እንዲከበሩ የታዘዙትን በዓላት ለማክበር ከ12 ዓመቱ ጀምሮ ወደ ኢየሩሳሌም ይወጣ ነበር፤ (ሉቃ. 2፥42፤ ዮሐ. 2፥13፤ 5፥1፤ 7፥10፤ 10፥22-23፤ 12፥12)።

በእርግጥ ጌታ ከአይሁድ ወገን በመሆኑ በዓል ለማክበር በኢየሩሳሌም ቢገኝ አያስደንቅም። ወዲህም ሕግን ለመፈጸም የመጣ እንደ መሆኑ በዚያ መገኘት ተገቢው ነበር። ይሁን እንጂ በዓልን ለማክበር በዚያ ቢገኝም፥ በሌላ በኩል አጋጣሚውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት ሥራ ተጠቅሞበታል። ወደ በዓል ለወጣው ሕዝብ ወንጌልን በማስተማር ያሳምን ነበር፤ (ዮሐ. 2፥23፤ 7፥37)።

ሐዋርያትና ተከታዮቻቸውም ጌታ ከሙታን ተለይቶ በተነሣባት ዕለት እየተሰባሰቡ እግዚአብሔርን ያመልኩ፥ ቅዱስ ቍርባንን ይቀበሉ፥ ሌሎችንም መንፈሳዊ ተግባራት ያከናውኑ ነበር፤ (ሉቃ. 24፥1፤ የሐዋ. ሥራ 20፥7፤ 1ቆሮ. 16፥2)። በመሆኑም ይህች ዕለት የጌታ ዕለት ተብላ ተጠርታለች፤ (ራእ. 1፥10)። እስካሁንም ድረስ ክርስቲያኖች ሁሉ ይህችን ዕለት ዐርፈውና በቤተ ክርስቲያን ተሰባስበው እግዚአብሔርን በማምለክ ያሳልፋሉ። እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አጠራር ይህች ዕለት ሰንበተ ክርስቲያን ትባላለች።

ይሁን እንጂ የጌታን ቀን እንደ አይሁድ የአከባበር ሥርዐት ያክብሩ ዘንድ፥ ለክርስቲያኖች የተሰጠ የተለየ ትእዛዝ የለም። በፍትሐ ነገሥት የሚከተለው ተደንግጓል።

> «ኢይደልዎሙ ለክርስቲያን ከመ ያፅርዑ ተገብሮ በዕለተ ሰንበት ከመ አይሁድ፥ አላ ይተገበሩ በውእቱ ዕለት ከመ ክርስቲያን።»
>
> ትርጓሜ: - «ክርስቲያኖች እንደ አይሁድ በሰንበት ቀን ተግባርን ማጕደል (ሥራ መፍታት) አይገባቸውም። በዚህች ዕለት እንደ ክርስቲያን ይሥሩ እንጂ።» (አንቀጽ 19 ቍጥር 724)።

ይህን ድንጋጌ ባለማወቁ ይሁን ወይም የኦሪት ሥርዐቶችና ልማዶች ማነቆ ሆነውበት ምክንያቱ ባይታወቅም፥ ሕዝባችን ሰንበትንም ሆነ ሌሎች በዓላትን የሚያከብረው እንደ አይሁድ ነው ለማለት ይቻላል። ይህንኑ ሁኔታ ሲገልጹ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ አሁንም እንዲህ ብለዋል: -



> «ሕዝቡ ከብሉይ ኪዳን በወረሰው ትውፊት መሠረት በዕለተ ሰንበት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም በዓላት ማናቸውንም ሥራ ቢሆን አይሠራም። ሌላው ቀርቶ ቅዳሜና እሑድ የተቀዳ ውሃ፥ የተወቀጠ ቡና የማይጠጡ፥ ወንዝ የማይሻገሩ ክርስቲያኖች አሉ። በሌሎችም በዓላት እንደ ሰንበት አይጸናም እንጂ ሥር መማስ፥ ቅጠል መበጠስ፥ መጽሐፍ መጻፍ፥ መደጐስ፥ ልብስ ማጠብ ሁሉ በዓል እንደመሻር ይቈጠራል። ይህ ሁሉ ከሕዝቡ ልማድ ጋር የተያያዘ ስለሆነ እንጂ፥ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት የተደነገገ አይደለም።» (የኢ/ቤ/ክ/ ታሪክ ገጽ 125)።

ሐዋርያት ካለፉ ከብዙ ዘመን በኋላ የተነሡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሲመላለስ ያከናወናቸው ዐበይት ተግባራት እንዲዘከሩበት የበዓላትን ሥርዐት ሠርተዋል። በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት እነዚህ የጌታ ዐበይት በዓላት 9 ናቸው። እነርሱም: -

1. **ብሥራት** - የጌታ መፀነስ የሚታሰብበት፥
2. **ልደት** - የጌታ መወለድ የሚታሰብበት፥
3. **ጥምቀት**- የጌታ መጠመቅ የሚታሰብበት፥
4. **ደብረ ታቦር** - ብርሃነ መለኮቱን ሙሴና ኤልያስ ባሉበት ለሦስቱ ደቀ መዛሙርት መግለጹ የሚታሰብበት፥
5. **ሆሳዕና** - በአህያ ውርንጭላ ተቀምጦ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም፥ መግባቱ የሚታሰብበት፥
6. **ስቅለት** - ጌታ ለቤዛነት መሰቀሉ የሚታሰብበት፥
7. **ትንሣኤ** - የጌታን ከሙታን ተለይቶ መነሣት ለማሰብ፥
8. **ዕርገት** - የጌታን ወደ ሰማይ ማረግ ለማሰብ፥
9. **ጰራቅሊጦስ** - የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ለማሰብ፥

በተጨማሪም ሌሎች 9 የጌታ ንኡሳን በዓላትም አሉ (የኢ/ቤ/ክ ታሪክ ገጽ 125-132)።

እነዚህ በዓላት ጌታ የሠራውን ሥራ በማስታወስ በምስጋናና በአምልኮ እንዲከበሩ የተገባ ነው። በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያናችን ዕድለኛ ናት። ቅዱስ ያሬድ ለቤተ ክርስቲያናችን ያበረከተው አስተዋጽኦም ፈጽሞ የሚረሳ አይደለም። የዓመቱን ቀናት ሁሉ በወቅቶች ከፋፍሎ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸው የእግዚአብሔር ሥራ እየተዘከረ ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔር እንዲሰጥ አድርጓል።

ከላይ ለተገለጹት የጌታ በዓላትም ተስማሚ የሆኑ ዝማሬዎችን ከቅዱሳት መጻሕፍት በማውጣታት በዓላቱ በምስጋናና በዝማሬ እንዲከበሩ አድርጓል። በተለይም «የጌታ ቀን» በመባል በምትታወቀዋ ዕለተ እሑድ፥ በያንዳንዱ እሑድ ተነግሮ ከማያልቀው የአምላክ ሥራ ዐበይት የሆኑትን ለማሰብ፥ ኀይለ ቃላትን ከቅዱሳት መጻሕፍት በመውሰድ በዜማ አቀናብሮ የተለያዩ መዝሙራትን ደርሷል። ቤተ ክርስቲያናችንም እየተጠቀመችበት ትገኛለች።

በዓላቱ እንደዚህ ባለ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዐት እየተከበሩ ክብሩ ሁሉ ለእግዚአብሔር እንዲሰጥ የታዘዘ ቢሆንም፥ በተለያዩ ምክንያቶች የበዓሉ መንፈሳዊ ውበት በሌላ ሥጋዊ ሥርዐት እየተተካ መጥቷል። ዛሬ አብዛኛው ሰው በዓሉን የሚያከብረው ከበዓሉ በስተጀርባ ስለእርሱ የተደረገለትን አምላካዊ ፍቅር በማሰብ አይደለም። ከዚያ ይልቅ ለበዓሉ የተሠራውን ሥርዐት በመፈጸም ብቻ፥ በመብል፥ በመጠጥ፥ በጭፈራና በስካር ሥጋዊ ተድላ ደስታ ለማድረግ ነው። ቤተ ክርስቲያን ይህ እንዳይሆን በቃል ማስተማሯ ባይቀርም ሰሚ ግን አላገኘችም።

ይህም ብቻ አይደለም፤ በቀደሙት አበው የጌታ ሥራ እንዲታሰብ በበጎ ዐላማ የተጀመረው የበዓል አከባበር ሁኔታ፥ መልኩን ቀይሮና አድማሱን እያሰፋ በመሄድ፥ አሕዛባዊው ልማድ መንፈሳዊ የሚመስል ጭንብል አጥልቆ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብቷል።

እነዚህ አሕዛብ ወደ ክርስትና ሲመጡ፥ የወንጌልን መልእክት በግል አምነው በመቀበል የሕይወት ለውጥ ሳያደርጉ ይሁን፥ ወይም ደግሞ በዐዋጅ መልክ ነገሥታቶቻቸው ክርስቲያን ሁኑ ብለው ስላስገደዷቸው፥ ብቻ ምክንያቱ ባይታወቅም ካመኑ በኋላ የቀደመ ልማዳቸውን ለማስተው መሞከርም፥ በዚያን ዘመን ለነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከባድ ፈተና ነበር። በመሆኑም ቀድሞ በጣዖታቱ ስም ተሰይመው ይከበሩ የነበሩት በዓላት በቅዱሳን ስም ተሰይመው እንዲከበሩ አደረጉ።

ብዕፁነታቸው አሁንም ስለዚሁ ጉዳይ የሚከተለውን ጽፈዋል: -

> «ከአረማዊነት የተመለሱት ደግሞ እንደዚሁ የክርስቶስን አዳኝነት አምነው ከተቀበሉና ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ፥ ልማደ አረማውያንን አልተዉም። ሊቃውንቱና መምህራኑ የሕዝቡን የረጅም ዘመን ፍቅረ ጣዖት ለማስተው ስላቃታቸው፥ በጣዖታቱ ተሰይሞ ይከበር የነበረውን ሁሉ በቅዱሳን ስም እየለወጡ ያከብሩታል። ለምሳሌ: - በጣዖታዊት በነበሩበት ጊዜ «ፓሲዶን» የሚባለው ጣዖት የባሕር አምላክ ነበር። በክርስትና ዘመናቸው ግን ሊቃውንቱ «ኒኮላዎስ» የሚባለውን ቅዱስ የባሕር ጠባቂ ብለው በየመቱ ያከብሩታል። የመርከበኞች በዓል ነው። «አሬስ» ወይም «ማርስ» የጦር አምላክ ተብሎ ሲመለክ የኖረ ጣዖት ነው። በእርሱ ምትክ ዛሬ ቅዱስ ጊዮርጊስን የወታደሮች ጠባቂ ብለው በየመቱ ያከብራሉ።
>
> በጠቅላላው አረማውያን ለእያንዳንዱ ድርጊት (ፍጥረት) መድበውለት ስለነበር፥ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናቸው የሚከበሩት ቅዱሳን መላእክት፥ ጻድቃን ሰማዕታት ሁሉ የአንዳንድ ነገር ጠባቂዎች እየተባሉ ተሰይመዋል።» (የኢ/ቤ/ክ/ታሪክ ገጽ 123-124)።

መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት የተሰኘው ሌላው የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ደግሞ፥ በተመሳሳይ ሁኔታ ኅዳር 12 ቀን የሚከበረው የሚካኤል በዓል፥ በግብጾች ዘንድ አስቀድሞ ይከበር በነበረው «ዙሐል» በተባለው ጣዖት በዓል ምትክ መከበር መጀመሩን ይተርክልናል። ይህም የሆነው ሕዝቡ በክርስቶስ አምኛለሁ ካለ በኋላ፥ የቀደመውን ጣዖት አምላኪነቱንም አደበላልቆ በመያዙ ምክንያት በወቅቱ የነበረው ሊቀ ጳጳስ እለ እስክንድሮስ



ባንድ ወገን ዙሐልን ለማጥፋት በማሰብ፥ በሌላ ወገን ደግሞ ሕዝቡን ለማስደሰት ሲል ይህን እንዳደረገ መጽሐፉ አክሎ ይናገራል (ገጽ 152-153)።

እዚህ ላይ መቼም ለመንፈሳዊ ነገር የዋህ ነኝ የሚል ሰው የጣዖታቱ በዓል በቅዱሳን በዓል የመለወጡን ነገር እንደ ትክክለኛ እርምጃ ሊቈጥረው ይችላል። ሆኖም በማስተዋል ሁኔታዎችን ለመረመረ ሰው የስም ለውጥ ብቻ ከመደረጉ በቀር የሚፈለገው መንፈሳዊ ለውጥ አልተደረገም። ምናልባትም ባለማወቅ ከድጡ ወደ ማጡ ሆኖብናል።

ይህ ልማደ አሕዛብ ሥር ከሰደደባቸው ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ አንዷ ናት። በቤተ ክርስቲያናችን የያንዳንዱ ወር 30 ቀናት ሁሉ በዓላት ናቸው። በያንዳንዱ ቀንም ጥቂቶች በዓላት በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ የታወቁ ይሁኑ እንጂ፥ የማይታወቁና ተደራርበው የተዳበሉ የብዙ ቅዱሳን መታሰቢያ በዓላት እንዳሉ ግልጽ ነው። የጻድቃንና የሰማዕታትን የተጋድሎ ዜናና ታሪክ የያዘውና ስንክሳር የተባለው ግዙፍ መጽሐፍ እንደሚያቀርበው ከሆነ፥ የዓመቱ ቀናት በሙሉ በዓላት ናቸው። በአንድ ቀን የሚከበሩትም ሦስትና አራት፥ ከዚያም በላይ ሊሆን ይችላል።

አሁን በቤተ ክርስቲያናችን የሚታየውን ይህን ሁኔታ ከአይሁድ የበዓላት አከባበር ሥርዐት ጋር ካስተያየነው፥ ምንም ግንኙነት የለውም። መሠረታዊው ልዩነት ደግሞ የአይሁድ በዓላት በእግዚአብሔር የታዘዙና የእግዚአብሔር ሥራ እየታሰበ እግዚአብሔር ብቻ እንዲመሰገንባቸው የተሠሩ በዓላት መሆናቸው ሲሆን፥ አሁን በተለይም በቤተ ክርስቲያናችን የሚታየው ሁኔታ ግን የዚያ ተቃራኒ ነው። ጥቂት የአምላክ ሥራ የሚታሰብባቸው በዓላት ቢኖሩም የሚበዙት ግን ፍጡራንን ለማወደስና ለማምለክ የተሠሩ በዓላት ናቸው።

በሕዝቡ ዘንድ እጅግ ታውቀው በልዩ ሁኔታ በሚከበሩት የቅዱሳን በዓላት ዕለት፥ እንደ ጸሎት ተቈጥረው የሚነበቡ ድርሳናትና ገድላት የሚያስተላልፉትን መልእክት ካየን፥ የመልክዐ ድርሰቶችም የሚያስነብቡንን ካስተዋልን፥ በእርግጥም ፍጡራን በፈጣሪ ስፍራ ሆነው፥ በተለይም በተሠራላቸው የበዓል ቀን እየተመለኩ መሆናቸው በግልጽ ይገባናል።

በዓላቱ የአምላክ ብቻ ሆነው፥ አምላክ ብቻውን ቢወደስና ቢመለክ ነገሩን ማንም በመጥፎ ሊመለከተው አይገባም ነበር። እንደ እምነቱ መጠን የእግዚአብሔርንም ቃል ድጋፍ ሊያገኝ ይችል ነበር። «ቀንን የሚያከብር ለጌታ ብሎ ያከብራልና» (ሮሜ 14፥6)።

## ማጠቃለያ

በመጻሕፍት ዕውቀትና እንዲሁ ሲወርድ ሲዋረድ በሚሉት ፈሊጥ የተያዘ ልማዳዊ ሃይማኖተኝነት በእጅጉ የተለያዩ ናቸው።

ሃይማኖታቸውን በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ላይ የመሠረቱ ሰዎች በእልከኝነት መንፈስ ካልተያዙ÷ ወይም ደግሞ የሚያነቧቸውን መጻሕፍት ማስተዋል ካልቻሉ በቀር÷ የእግዚአብሔርን እውነት መቼም ቢሆን ሳይረዱት አይቀሩም።

ከዚህ ውጪ በሆኑና በልማዳዊ ሁኔታ ብቻ «ሃይማኖተኛ» ነን በሚሉ ወገኖች ዘንድ ግን በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ አለ። በእነርሱ ዘንድ እውነት እንደ ሐሰት÷ ሐሰት እንደ እውነት÷ ብርሃን እንደ ጨለማ÷ ጨለማ ደግሞ እንደ ብርሃን÷ አማኝ የሆነው እንደ መናፍቅ÷ መናፍቅ የሆነው ደግሞ እንደ አማኝ ይቈጠራል። ለዚህም ዋናው ምክንያት ሃይማኖታቸው በልማድ ላይ ብቻ እንጂ÷ በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ላይ ስላልተመሠረተ ነው።

በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በነዚህ ሁለት ወገኖች መካከል ያለውን የኀይል ሚዛን ከተመለከትን÷ በመጻሕፍት ዕውቀት ላይ የተመሠረተ ሃይማኖት ካላቸው ይልቅ÷ ልማዳዊ ሃይማኖተኞች ይበዛሉ። ቤተ ክርስቲያን ስሕተቶችን አስተካክላ÷ ችግሮችን አስወግዳ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት እንዳትመራ በማድረግ÷ ወደባሰ ጥፋት እየወሰዳት ያለውም የነዚሁ ወገኖች ጭፍን አመለካከት ነው።

እነዚህ ወገኖች ባላቸው ልማዳዊ ሃይማኖተኝነትና በደረሱበት ዕውቀት ለቤተ ክርስቲያናቸው ያላቸው ቅንአት በእጅጉ የሚደነቅ ነው። ቢሆንም ያለ ዕውቀት የሆነ ባዶ ቅንአት ነውና እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኝ አይችልም፤ (ሮሜ 10÷2-3)። ምክንያቱም እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙ እየመሰላቸው÷ እውነተኛውን ትምህርት ይቃወማሉ፤ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ እምነት ያላቸውን አባቶችና ወንድሞች በመናፍቅነት ጎራ በመፈረጅ ያሳድዳሉ፤ ሌላም ይህን መሰል እኩይ ተግባር ይፈጽማሉ።

በዚህ መጽሐፍ ጥላና አካል የሆኑት ኦሪትና ወንጌል በራሳቸው ዘመን የሰጡትንና እየሰጡ ያሉትን አገልግሎት በንጽጽር ለማሳየት ተሞክሯል። ልማዳዊው ሃይማኖተኝነት ሳይሆን በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ላይ የተመሠረተው ሃይማኖት ይህን ይመስላል።

ይህን መጽሐፍ ያነበበ÷ ይልቁንም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመን የሆነ ወገኔ÷ አንድ ነገር ሳይገነዘብ እንደማይቀር የታመነ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን ኦሪትና ወንጌልን አደበላልቃ ያየዘች መሆኗን፤ ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያኑ ወደ ቀደመው እውነተኛ መሠረቷ እንድትመለስ ተጋድሎ ለማድረግ ዐዲስ ራእይና ሸክም በሕይወቱ ውስጥ ሊጨመርለት ይገባል እንጂ÷ ቤተ ክርስቲያኒቱን በመጥላት ለጥፋቷ ሊተጋ÷ ለመጥፎና እግዚአብሔር ለማይደሰትበት ዐላማም ልቡን ሊያነሣሣ ፈጽሞ አይገባውም።



ስለዚህ ለሕዝባችን መዳን የምንቈረቈር ወገኖች ሁሉ÷ ሕዝባችን ከኦሪት ወደ ወንጌል ፊቱን የሚመልስበትን÷ ቤተ ክርስቲያናችን የምትፈርስበትን ሳይሆን÷ የማንነቷ መለያዎች የሆኑትንና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይጋጩትን መንፈሳዊ ዕሴቶቿን ጠብቃ÷ በወንጌል መሠረት ላይ ጸንታ ለመቆም የሚያስችላትን መልካም አገልግሎት ለማገልገል እንነሣ።

**ስብሐት ለእግዚአብሔር ስዘሐወፀነ እምአርያም**
**ከአርያም ለገበኘን ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን!**

ተፈጸመ